# አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ፤ ትናንትም ዛሬም ነገም!

ሚያዝያ 6 ቀን 2003 ዓመተ ምሕረት
ከሞቱ፡ 143 ዓመት ሆናቸው!

ለ143ኛ ዓመት መታሰቢያ

የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው!
All rights reserved

መጀመሪያ ታትመ ሚያዝያ 2003 ዓም
ሁለተኛ ታተመ ሰኔ 2003 ዓም
ሲያትል ዋሽንግተን
አሜሪካ

Copyright 2011 Amare Afelae Bishaw.
Published by Gugsa Magazine
First edition Apirl 2011
Second edition Juen 2011
Printed in U.S.A

P.O.BOX 492
Seattle WA 98111
U.S.A

የደራሲው መልእክት ማተን ቁጥር
P.O.BOX 492
Seattle WA 98111
U.S.A

ከአማረ አፈለ ብሻው!
Amare Afelae Bishaw

## ክፍል አንድ

### ማውጫ

ማውጫ መታሰቢያ ምስጋና ማብራሪያ ገጽ 2-10
ምዕራፍ 2 አጤ ቴዎድሮስን በጠቢባን አወቅናቸው ገጽ 11-23
ምዕራፍ 3 ለመጽሐፉ ጥቅስ የተጠቀምኩበት ፊሊጥ ገጽ 23-34
ምዕራፍ 4 ፊር አስጨባጭ ገጽ 34-41
ምዕራፍ 5 መግቢያ በሻለቃ ግርማ ይልማና ባረሙት ገጽ 42-54

## ክፍል ሁለት

ምዕራፍ 1 ኢትዮጵያ በዘመነ መሳፍንት ሥርዓት ገጽ 55-60
ምዕራፍ 2 ቤተ ክርስቲያን በዘመነ መሳፍንት ገጽ 60-66
ምዕራፍ 3 የኢትዮጵያ ሕዝብ በዘመነ መሳፍንቱ ገጽ 66-74
ምዕራፍ 4 ዘመነ መሳፍንቱ ከውጭ መንግሥታት ጋር! ገጽ 74-79
ምዕራፍ 5 የኢትዮጵያ ሕዝብ እንባ ፊሶ አልቀረም ገጽ 79-87

## ክፍል ሦስት

ምዕራፍ 1 የካሣ ኃይሉ ትውልድ ገጽ 88-97
ምዕራፍ 2 የካሣ ኃይሉ እድገት ገጽ 98-104
ምዕራፍ 3 ልጅ ካሣ ገጽ 104-108
ምዕራፍ 4 ካሣ ኃይሉ የኮሶ ሻጭ ልጅ አልነበሩም? ገጽ 108-117
ምዕራፍ 5 ደጃዝማች ካሳ ገጽ 118-124
ምዕራፍ 6 የጃዝማች ካሣ ዘመቻ ወደ ሰሜን ገጽ 125-128
ምዕራፍ 7 ከደጃዝማችነት ወደ አጤነት ገጽ 128-1332
ምዕራፍ 8 አጤ ቴዎድሮስ የነገሡበት ዓመት መለያየት ገጽ 132-140

## ክፍል አራት

ምዕራፍ 1 የአጤ ቴዎድሮስ ሕግ አዋጅ ገጽ 1341-144
ምዕራፍ 2 የያዝከውን ሃይማኖት አትቀይር ገጽ 145-150
ምዕራፍ 3 የአጤ ቴዎድሮስ ዘመቻ ወደ ወሎ ገጽ 150-154
ምዕራፍ 4 የአጤ ቴዎድሮስ ዘመቻ ከወሎ ወደ ሸዋ ገጽ 1546-160
ምዕራፍ 5 የአጤ ቴዎድሮስ ራእይ ለኢትዮጵያ ገጽ 161-163
ምዕራፍ 6 የአጤ ቴዎድሮስ የውጭ ግንኙነት ገጽ 164-167
ምዕራፍ 7 ወታደር ደመወዝተኛ ሆነ ገጽ 168-172
ምዕራፍ 8 የጋፋት እንዱስትሪና በጣና ባሕር መርከብ ሥራ ገጽ 172-186



ምዕራፍ 9 የኢትዮጵያ ባል የኢየሩሳሌም ውሽማ ገጽ 187-196
ምዕራፍ 10 አዳሪ ትምህርት ቤት ጅመራ ገጽ 197-201
ምዕራፍ 11 የባህል ልብስ፣ቁንጅና ውድድር፣ ሥነ ጽሑፍ ገጽ 202-211

## ክፍል አምስት

ምዕራፍ 1 እቴጌ ተዋበችና እቴጌ ጥሩወርቅ ገጽ 212-218
ምዕራፍ 2 አጤ ቴዎድሮስ የጨከኑበት ምክንያት ገጽ 219-222
ምዕራፍ 3 አጤ ቴዎድሮስ ሕግ በጣሱት ላይ ጨክነዋል ገጽ 222-227
ምዕራፍ 4 የአጤ ቴዎድሮስ የማይዛባ ፍርድ ገጽ 228-238
ምዕራፍ 5 የአጤ ቴዎድሮስ ደግነት ገጽ 239-243

## ክፍል ስድስት

ምዕራድ 1 የግብጽ ፓትርያርክ መታሰር ገጽ 244-252
ምዕራፍ 2 አጤ ቴዎድሮስና አቡነ ሰላማ ገጽ 253-263
ምዕራፍ 3 ቤተ ክህነትና አጤ ቴዎድሮስ ገጽ 264-269
ምዕራፍ 4 አጤ ቴዎድሮስና ደብተራ ገጽ 269-272
ምዕራፍ 5 አጤ ቴዎድሮስ መነከሳትና ካህናት ገጽ 273-287
ምዕራፍ 6 አጤ ቴዎድሮስና ሸህ ሁሴን ጅብሪል ገጽ 287-292
ምዕራፍ 7 "እንዳይርቅህ መንፈስ ቅዱስ ብዙ ጊዜ አትቅረብ ክቄስ" ገጽ 292-297
ምዕራፍ 8 አጤቴዎድሮስን ቀድሞም ዛሬም የሚወዱ ካህናት አሉ ገጽ 298-304


## ክፍል ሰባት

ምዕራፍ 1 "አጤ ቴዎድሮስ የአሜሪካ ጦርነት አበቃ ወይ" ገጽ 2305-318
ምዕራፍ 2 በአጤ ቴዎድሮስ ዘመን የተሾሙ ሹማምት ገጽ 318-324
ምዕራፍ 3 አጤው ለእድገት ሲሯሯጡ መኳንንቱ አፈነገጡ ገጽ 325-332
ምዕራፍ 4 የደጃዝማች ንጉሤ መሸፈትና አገር መሸጥ ገጽ 333-338
ምዕራፍ 5 የደጃዝማች ካሣ ምርጫ መሸፈት ገጽ 338-341


## ክፍል ስምንት

ምዕራፍ 1 የኢትዮጵያና የአውሮፓውያን ግንኙነት ገጽ 342-347
ምዕራፍ 2 እንግሊዝ እና የኢትዮጵያ ግንኙነት ገጽ 347-352
ምዕራፍ 3 የጉዳይ ፈጻሚ ካሜሮን መምጣትና መታሰር ገጽ 352-358
ምዕራፍ 4 የውጭ ሃይማኖተኞችና አጤ ቴዎድሮስ ገጽ 359-368
ምዕራፍ 5 እንግሊዞች ጦር ወደ ኢትዮጵያ አዘመቱ ገጽ 368-372
ምዕራፍ 6 እንግሊዞችና ደጃዝማች ካሳ ምርጫ ገጽ 372-379

## ክፍል ዘጠኝ



የዐፄ ቴዎድሮስ ዘውድ
(ከሮጀር አክቶን መጽሐፍ)



ዐፄ ቴዎድሮስ ለንግሥት ቪክቶሪያ የጻፉት ደብዳ
(እነአቶ ግርማ ሥላሴ ካሳተሙት መጽሐፍ)

የአጤ ቴዎድሮስ ዘውድና ማህተማቸው! ምንጩ



የአጤ ቴዎድሮስ ኒሻን ምንጩ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ አጤ ቴዎድሮስ እና የኢትዮጵያ አንድነት ገጽ 501



# መታሰቢያ

መጽሐፈ ነገሥት 1ኛ ምዕራፍ 3 ቁጥር 12 "እነሆ ማንም የሚመስልህ ከአንተ በፊት እንደሌለ ከአንተም በኋላ እንዳይነሣ አድርጌ ጥበበኛና አስተዋይ ልቡና ሰጥቼሃለሁ" ይላል:: ለእኔ ከዚህ በፊት ሊቀ ጠበብት ተሾመ ሀብተ ገብርኤልን፣ የሚመስል ወንድም ኑሮኝ አያውቅም:: ለወደፊቱም እርሳቸውን የመሰለ ወንድም እማገኝ መስሎ አይታየኝም:: ሊቀ ጠበብት ተሾመ፣ ቅድሚያ የተዋወቅንበት ምክንያት እንዲህ ነው:: አሰብን አስመልክቶ በላንዳፍታ መጽሔት የጻፍኩትን መጣጥፍ ተመልክተው ደስ አላቸው::

ከእኔ ጋር በሊቅ ዶ/ር ስብሐት መርስዔ ኀዘን፣ አማካኝነት ተዋወቅን:: ስለ አሰብ ጉዳይ የጀመርኩትን በርትቼ መጻፍ እንዳለብኝ እርሳቸው የሠነድ አቅርቦት በገፍ ማምጣት ጀምሩ:: እኔ ኋላ ጉማሣ መጽሔትን ሳዘጋጅ ሲተባበሩኝ ቆዩ:: መጽሔቱን ትቼው መጽሐፍ ወደማሳተሙ ስጀምር አሰብን አስመልክቶ ለመጻፍ ጀምሬአለሁ ስላቸው የመጽሐፉን ከበር ራሳቸው አሠሩና ላኩልኝ:: መጽሐፉ እንደታተመ 40 መጽሐፍ ኢትዮጵያ በእርሳቸው ወጭ አስገብተዋል::

መጽሐፉ ተወዳጅነት ማግኘቱን ከተረዱ በኋላ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲታተም ጥረት አደረጉ:: ነገር ግን የተገኙት አታሚዎች "ይህ መጽሐፍ ያለውን መንግሥት የሚያስቆጣ በመሆኑ ማረም አለብን" አለበለዚያ ሊታተም አይችልም ሲሉአቸው ጥረታቸው ሳይሳካ ቀረ:: አንድ ቀን የአጤ ቴዎድሮስን ታሪክ በተመለከተ ለመጻፍ ማሰቤን ሥነግራቸው "ሕዝብ የዚህን መጽሐፍ ማተሚያ የምሸፍነው እኔ ነኝ በርታ:: በኢትዮጵያ ያሉትን የጀግኖች ታሪክ የዛሬው ትውልድ ካወቀ ኢትዮጵያ አንድ ቀን እንደነበረች ትሆናለች" በማለት ጥሪል ሰጥተውኝ ነበር:: ታዲያ ምን ያደርጋል ሲኀዝበት የነበረው መጽሐፍ ለንባብ ሳይበቃ እርሳቸው ሰኔ 9 ቀን 2002 ዓም ማረፋቸውን ስሰማ አዘንኩኝ:: እኔም አስከሬናቸው ፊት እንባየን ሳላፈስ ቀረሁ:: የምሠራበት መሥሪያ ቤት ፈቃድ አልሰጠኝ አለ:: ሳምንቱ የአባቶች ቀን ማለትም "ፋዘርስ ደይ ዊኬንድ" በመሆኑ በመሥሪያ ቤቱ ሕግ መሠረት "ብሎክ አውት ውኬንድ" ይባላል:: በዚህ ምክንያት እኔ እርሳቸውን ሳልሸኛቸው ቀረሁ::

1ኛ ጢሞ 6፡18 "እውነተኛውን ሕይወት ይይዙ ዘንድ ለሚመጣው ዘመን ለራሳቸው መልካም መሠረት የሚሆንላቸውን መዝገብ እየሰበሰቡ መልካምን እንዲያደርጉ በበጎም ሥራ ባለ ጠጎች እንዲሆኑ ሊረዱና ሊያካፍሉም የተዘጋጁ እንዲሆኑ ምከራቸው" ይላል:: ልክ ሊቀ ጠበብት ይህን ሲፈጽሙ ኑረው አልፈዋል:: ስለዚህ ይህን አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ ትናንም ዛሬም ነገም የተባለውን መጽሐፍ መታሰቢያነቱን ለሊቀ ጠበብት ፕሮፌሰር ተሾመ ሀብተ ገብርኤል እና ለክቡር ሐኪም ሊቀ ጠበብት ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስና ለተዋናይ ታማኝ በየነ መታሰቢያ ይሆናቸው ዘንድ አበረክታለሁ::

ምዕራፍ 1 የአጤ ቴዎድሮስ ጉዞ ወደ መቅደላ ገጽ 380-382
ምዕራፍ 2 የእንግሊዞች እና የኢትዮጵያ ጦርነት በመቅደላ ገጽ 383-389
ምዕራፍ 3 አይ መቅደላ ልጆችዋን የምትበላ ገጽ 390-395
ምዕራፍ 4 ወይዘሮ ምንትዋብ "ዘውድ ለባለ ዘውድ" አሉ ገጽ 396-399
ምዕራፍ 5 እንግሊዞች የኢትዮጵያን ቅርሳቅርስ ዘረፉ ገጽ 400-405

## ክፍል አሥር

ምዕራፍ 1 የአጤ ቴዎድሮስ ልጆቻቸውና የልጅ ልጆቻቸው ገጽ 406-414
ምዕራፍ 2 አጤ ቴዎድሮስ በሕዝብና በጥበብ ሰዎች ዓይን፣ ገጽ 414-431
ምዕራፍ 3 የአጤ ቴዎድሮስ ገብርዬዎች አልቀዋል የሉም ገጽ 431-439
ምዕራፍ 4 የአጤ ቴዎድሮስ አካልዬዎች ጥቂት አሉ ገጽ 440-444

## ክፍል አሥራ አንድ

ምዕራፍ 1 ተሾሩ ገብረ ሥላሴ በአጤ ቴዎድሮስ ላይ ገጽ 445-457
ምዕራፍ 2 በተአምረ ማርያም የተሸፈነ ደባ ገጽ 457-461
ምዕራፍ 3 የተሾሩ ገብረ ሥላሴ ትረካ ገጽ 462-472
ምዕራፍ 4 እውነት የማርያም ጽላት አሰብ ላይ ተይዟልን? ገጽ 473-477
ምዕራፍ 5 ቅድስት ማርያም አዲስ አበባ ታይታ ነበር?ገጽ 477-481

## ክፍል አሥራ ሁለት

ምዕራፍ 1 አጤ ቴዎድሮስ ፀረ እስላም አይደሉም ገጽ 482-502
ምዕራፍ 2 አጤ ቴዎድሮስ ጸረ ኦሮሞ አልነበሩም ገጽ 503-518
ምዕራፍ 3 ወያኔዎች በአጤ ቴዎድሮስ ታሪክ ላይ ገጽ 518-532
ምዕራፍ 4 ሊቀ ጠበብት ትክክል አይደሉም ገጽ 532-537
ምዕራፍ 5 ታሪክን ያላገናዘቡ ሊቅ ዶ/ር ናቸው ገጽ 538-545
ምዕራፍ 6 አጤ ቴዎድሮስ የኢትዮጵያ ጠላት አይደሉም ገጽ 546-552
ምዕራፍ 7 ደጃዝማች ዘውዴ ምን ነካቸው? ገጽ 553-565
ምዕራፍ 8 አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ በአጤ ቴዎድሮስ ታሪክ ገጽ 565-578


## ክፍል አሥራ ሦስት

ምዕራፍ 1 የአጤ ቴዎድሮስ አጽም የት ደረፍ? ገጽ 579-591
ምዕራፍ 2 አባሪ ገጽ 592-631
ምዕራፍ 3 ጠቅላላ ዋቢ መጻሕፍት ገጽ 632-640
ምዕራፍ 4 የሥዕል ፎቶ መግለጫ ገጽ 641-655





አጤ ቴዎድሮስ በሕይወት ዘመናቸው ሳሉ! ምንጩ ከንግረስ ላይብረሪ የተገዛ ሲሆን ሁለተኛው ምስል ፎቶ ደግሞ እንደ ፖስት ካርድ የተሠራ ነው።




ይህ የአጤ ቴዎድሮስ ምስል ፎቶ በሰዓሊ እስክንድር ስዩም የተሳለ ነው።

ብጣሪ ብጣሪ አጣሁት ወንድሜን
መቼ መሠለኝና የምትርቅ እኔን
ጳግም ሳንትያይ በቃ ተለየየን
አትጨክን ተሾመ እንግባ አገራችን
እንደወጡ ቀሩ አደበል ጠላታችን
ሀብታም ነው ድሀ ነው ብሎ ሰው የማይንቅ
ከልጅ ጋር እንደልጅ ከትልቅ ጋር ትልቅ
ከአዘነ ጋር ማዘን ከሳቀው ጋር መሳቅ
ከደግነት በቀር ክፉ ቃል የማያውቅ
መቸም ኢትዮጵያ በልጅ አልተባረክሽ
ሊቀጠበብት ተሾመን አምላክ ወሰደብሽ::



ገደል ተወርውረው ቢጣሉ ወደአለት
ቁሱም ከመቅደሱ ቢቃጠሉ በሳት
እያሉ ታረዱ ኢትዮጵያ እንዷት ናት
የትኛው ምሁር ነው ለሕዝብ የታመመ
በሐቅ የሚሰራ ለአንድነት የቆመ
እውነትን ማነው የሚያስተምረን
በአንድ ሠንደቅ ሥር የሚያደራጀን
መስሎ መኖር ትቶ መሆንን አሳይቶ
የጎዳ ዱለታን ቆሻሻ ውስጥ ከቶ
ከደግነት ጋር የስጠው አሚልቶ
አንድ ዓሥራት እሳቸው ነበሩ
ሕይወታቸውን ለአንድነት ገበሩ::

ሊ.ቀ ጠበብት ተሾመ ሀብተ ገብርኤል



ሊ.ቀ ጠበብት ሐኪም ዓሥራት ወልደየስ!

በቀልድ የጀመረው በቃ ለቁም ነገር
ተረክቦ ሲዞር እምነትና ሀገር
ተሸከሚት አየን ተረኛዋን ቀንበር
ያች የክብር ማተብ ተጣብቃ ከንገቱ
ትከለተዋለች በየሄደበቱ
መስቀል አደባባይ መሰከረች ቁማ
ሳትፈራ በድፍረት ምንም ሳታቅማማ
እንዲህ ሲል አሰማ
ወጥቶ ከመድረክ ላይ ከትልቁ ማማ
አንድ አገርና ሕዝብ አንድ ሠንደቅ ዓላማ
መስሎ መገኘትን ማደርን የጠላው
ንዋይ ያልደለለው
በፌሪቃ ሳይሆን ፀሐይ እየሞቀው
አተረፋት ስሙን አገርም አወቀው::



ተዋናይ ታማኝ በየነ!




# ምስጋና

ከሁሉ አስቀድሜ የማሰብ ችሎታ ሰጥቶ መጽሐፍ መርምሬ እንድጽፍ የረዳኝ አምላክ ልዑል እግዚአብሔር ለዘላለም ስሙ የተመሰገነ ይሁን:: አንድ ሰው መጽሐፍ ለመጻፍ የሚነሣው የመጻፍ ፍላጎት ሲኖረው ነው! ከቤቱ ሰላም ሲያገኝ ያሰበውን መጽሐፍ ለመጻፍ ይችላል:: ዋቢ የሚሆን ሠነድ መጻሕፍት ማግኘት ሲችል ነው:: "አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ ትናንትም ዛሬም ነገም" የተባለውን መጽሐፍ ለመጻፍ ስጀምር ከላይ የጠቀስኳቸው ሁሉ ተሟልተው በማግኘቴ እነሆ ይህን መጽሐፍ ለመጻፍ ቻልኩኝ:: 1ኛ ጴጥ 1፤22"ለእውነት እየታዘዛችሁ ግብዝነት ለሌለበት ለወንድማማች መዋደድ ነፍሳችሁን አንጽታችሁ እርስ በርሳችሁ ከልባችሁ አጥብቃችሁ ተዋደዱ"ይላል:: እነዚህ"ለእውነት" የቆሙ ወገኖቼን ስላደረጉልኝ ሁሉ አመሰግናለሁ::

ወይዘሮ የካባ ሲሳይ አምባው መጽሐፍ ለመጻፍ ጉንብስ ቀና ስል ስሜቴን የሚነካ ቃላት ስለማትናገሪ አመሰግናለሁ:: ጸባይሽ እንዳይቀየር ለወደፊቱም በዚህ እንድትቀጥይ በእግዚአብሔር ስም ከአደራ ጋር እማጸናለሁ::

መጻሕፍትን መጣጥፎችን፤ ጋዜጣዎችን በራሪ ወረቀቶችን ተውኔት ክሮችን በመስጠትም፤በማዋስም የተባበሩኝ ስማቸውን እጠቅሳለሁ:: አቶ አሰግድ ድሌና አቶ ፈንታሁን ጥሩነህ ሊቀ ጠበብት ተሾመ ኃብተ ገብርኤል፤አቶ ሰሎሞን አምባው፤ሊቀ ማዕምራን አበባው ይግዛው፤ሊቅ ዶ/ር ጌቱ ገላዩ፤አቶ ተክሌ የኋላ፤ አምሳ አለቃ አባይነህ መሸሻ፤ ሊቀ ካህናት ምሳሌ እንግዳ፤አቶ ወልደ ገብርኤል አሰጌ፤አቶ ነቢዩ እንግዳ ወርቅ፤አቶ መልኩ በላይነህና ዲያቆን አቢይ መኮንን፤ አቶ መላኩ ዳንኤል፤አቶ ጸጋ ጣሰው፤አቶ ጸጋው ደምሌ፤ ለዚህ መጽሐፍ ጥቅስ የምወስድበት ሠነድ ሰጥተውኛል:: ሻለቃ ግርማ ይልማና ወይዘሪት ደንበርነሽ ደበብ መጽሐፍ አውሰውኛል::

አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ ትናትም ዛሬም ነገም፤የተባለውን መጽሐፍ ያረሙልኝ ሻለቃ ግርማ ይልማ፤ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛውና አቶ ዘርፉ ታከለ (ታያቸው) ሲሆኑ ፊደሉን የለቀሙልኝ ኢትዮጵያዊ ስማቸው እንዲገለጽ አልፈለጉም:: ባለንበት በስደቱ ዓለም የአንድን ሰው መጽሐፍ ረቂቅ ታምኖ ተቀብሎ ማረም ትልቅ የሀገር አላፊነት የሚሰማው ሰው ነው:: በስደቱ ዓለም ባለው የጊዜ እጥረትና ሩጫ ወቅት የሌላ ሰው የመጽሐፍ ረቂቅ ተቀብሎ ማረም የሀገር ፍቅር የሚሰማው ሰው ብቻ መሆን አለበት:: ሊቅ ዶ/ር ስብሐት መርስኤ ኀዘንና ሠዓሊ ኪሩቤል፤ አቶ ሹመት ጉዳይ አቶ ጌታቸው ረዳ፤አቶ ዋለ አዲስና አቶ ስለሽ ዘመነ፤አቶ በለጠ ወርቁ፤ ከልብ አመሰግናለሁ:: ከእንግሊዘኛ መጻሕፍት ጥቅስ የተወሰደውን ሻለቃ ግርማ መተርጎም ጀምረው ሳለ ጊዜው በማለቁ ምክንያት ሳላስጨርሳቸው ቀርቻለሁ:: ሻለቃን በድጋሚ ከልብ አመሰግናለሁ:: እንዲሁም የመጽሐፉን ሽፍን ያስተካከሉልኝ ሰዓሊ እስክንድር ስዩምን ከልብ አመሰግናለሁ::



ት

ት ጠበብት ተሾመ ሀብተ ገብርኤል



ነት ሐኪም ዓምራት ወልደየስ!



## ሁለተኛ እትም ማብራሪያ፤

*ከአንባብያን በብዛት የመጣ ጥያቄ "የተሥፋ ገብረ ሥላሴ ተአምረ ማርያም መጽሐፍ አባሪ ሁኖ ለምን አልወጣም:: ሁለተኛ ሲታተም መውጣት አለበት" ስላሉ አባሪ ቁጥር አምስትን ላይ ወጥቷል::*

*ሌላው ከመጀመሪያው እትም የፊደል ግድፈት ይህ ሁለተኛው እትም በመጠኑ ተለቅሟል:: ፊደሉን የለቀሙልኝ ሊቅ ዶ/ር ስብሃት መርስኤ ኀዘንና አቶ ሞገስ መርስኤ ኃዘን ሁለቱን ወዳጆቼን በጣም አመሰግናለሁ::*

አጤ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን አንድ ለማድረግ ሲነሡ የመሳፍንት ገዥዎችና ካህናቱ ሕዝቡን እየቀሰቀሱ ሲያስቸግሯቸው ጭካኔ አበዙ:: መሳፍንቱና ካህናቱ "ጨካኝ" እያሉ ሲያስወሩባቸው ይበሽቃቸዋል:: ታዲያ ቀን የሸፈተውን መሳፍንት ሲያባርሩ ይውሉና ማታ ደግሞ ከድንኳናቸው ሲገቡ በገና አንሥተው ይደረድራሉ::

"ይሉኛል ይሉኛል ጨካኝ
ሀሳቤን ሳያውቁ ምክሬን ሳይሰሙኝ" ይሉ ነበር::

አጤ ቴዎድሮስ ያለ ጊዜያቸው የተወለዱና ለኢትዮጵያ ሥልጣኔ ጮራ እንዲበራ ለማድረግ ታጥቀው የተነሡ ነበሩ:: የአጤ ቴዎድሮስን የአገር ግንባታ ዓላማ ሊቀ ጠበብት አጼኛው ወርቁ እንዲህ ይኳቸዋል::

"የሚያስተውለው ሰው የሚያውቅለት ጠፍቶ
ያለ ጊዜው ሄደ ያለ ጊዜው መጥቶ" ይላሉ::

አዎ አጤ ቴዎድሮስ ያለ ጊዜው የተወለዱና ያለ ጊዜያቸው የሞቱ ኢትዮጵያን አንድ ለማድረግ የታገሉ ጀግና ነበሩ:: አገራቸውን ለማሳደግ የነበራቸውን ዓላማ በራሳቸው አባባል ገልጸውታል::

"ይሉኛል ይሉኛል ይሉኛል ጨካኝ
ሀሳቤን ሳያውቁ ምክሬን ሳይሰሙኝ" ብለዋል::



# ምዕራፍ 1

## አጤ ቴዎድሮስን በጠቢባን አወቅናቸው!

አጤ ቴዎድሮስን ያሳወቁን ባለሞያዎች ናቸው:: ባለሞያ ማለት ደራሲ፤ሠዓሊ፣ ተዋናይ፤ድምጻውያን፡ ሌላም ሌላ ሞያ ያለው ሰው ነው:: ለዚህ መጽሐፍ መነሻ የሆኑት ከፍ ተብሎ ከተጠቀሱት ባለሞያወች የተገኙት ሠነዶች ናቸው:: የአጤ ቴዎድሮስን ምስል በሕይወት እያሉ ፎቶ መኖሩ ታውቋል:: ለዚህ ዋቢ የሚሆነው ምስል ፎቶ አንድን በጥሞና ማስተዋል ይጠቅማል::

ምስል ፎቶ ሁለት በይሆናል ሳይሆን በትክክል መንገድ በማሠራት ላይ እያሉ የተነሡት ነው:: ሌላው የእንግሊዝ ጦር ወደ ኢትዮጵያ ከመምጣቱ በፊት የአጤ ቴዎድሮስን ምስል ፎቶ ይዘው መጥተዋል ተብሎም ተጽፏል:: ይህ ማለት የአጤ ቴዎድሮስ ምስላቸው እንግሊዝ አገር ገብቶ ነበር ማለት ነው:: ለዚህም ዋቢ የሚሆን ቀደም ሲል አለቃ ተክለ ኢየሱስ የኢትዮጵያ ታሪክ ሐተታ ብለው ጽፈው የተውትን ዶ/ር ሥርግው ገላው ያሳተሙት መጽሐፍ ይሆናል::

አሳታሚ ዶ/ር ሥርግዉ ገላው አለቃ ተክለ ኢየሱስ የኢትዮጵያ ታሪክ ሐተታ በተባለው መጽሐፍ ገጽ 134 "አጤ ቴዎድሮስ በገዛ ጠበንጃው ሞቶ ባዩት ጊዜ አላመኑም ነበር:: ግን ቀድሞ በሕይወት ሳለ የኢትዮጵያ ንጉሥ ተብሎ መልኩ በፎቶግራፍ ሥዕል ተነሥቶ ከንግሥቲቱ ዘንድ ኢየሩሳለም ይኖር ነበርና ያንን ያዩ ፈረንጆች አወቁት:: ያ ሥዕል ባይኖር የአጤ ቴዎድሮስ መሞት አይታመንም ነበር" ሲሉ ጽፈዋል:: አለቃ ተክለ ኢየሱስ ሁሉንም "አንተ"እያሉ የጻፉ በመሆናቸው አንባብያን አክብሮት አልሰጡም ብላችሁ እንዳትነቅፏቸው::

አጤ ቴዎድሮስ ከመሞታቸው በፊት ትክክለኛ ምስላቸው ፎቶአቸው ነበር ማለት ነው:: ለዚህም ብዙ የተለያዩ ምስል ፎቶ ቢኖርም ምናልባት በአቶ ፈንታሁን ጥሩነህ አማካኝነት ከኮንግረስ ላይብረሪ የገዛሁት ከውጭ በጀርባ ያሉት ሁለት ሳይሆኑ አይቀርም:: ሌላው የብርቲሽ ሙዚዬም ተወካይ ሪቻርድ ሆምስ በደረቅ እርሳስና ቡርሽ

ራሳቸውን ከገደሉ በኋላ የሳለው ይሆናል:: ይህንም ከላይ እንደጠቀስኩት በአቶ ፈንታሁን ጥሩነህ አማካኝነት ኮንግረስ ላይብረሪ የገዛሁት ምሥል ፎቶ ሪቻርድ የሣለው ነው::

Darrell Bates <u>The Abyssinian Difficlty</u> page 176 "The head of Theodrus,sketched by R.R.Holmes immediately after the emperors death."ይላል::

ከነዚህ ከሁለቱ ምስሎች ፎቶዎች በኋላ ትክክለኛ ተክለ ሠውነታቸውን የሚገልጽ በኢትዮጵያውያን በራሳቸው አሣሣል እንደገና አሳምረውታል:: ለዚህም ቀዳሚው ሠአሊ አገኘሁ እንግዳ፤ በ1924 ዓም ሥለዋቸዋል:: ከዚያ በኋላ ኢትዮጵያውያን አጤ ቴዎድሮስን የሣሉ ብዙ ናቸው::

ታሪካዊ መቅደላንና ታሪካዊ መድፋቸውን ለኢትዮጵያ ትውልድ ሠዓልያን አቅርበዋል:: የአጤ ቴዎድሮስ ምሥል ይበልጥ የታወቀው ደግሞ በግርማቸው ተክለሐዋርያት "ቴዎድሮስ" የተሰኘው ተውኔት የመጽሐፉ ሽፋን ሁኖ ከወጣ በኋላ ሠዓልያን የአገር ፍቅር አደረባቸው:: የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ አንድ መጽሐፍ አሳትሟል::

INSITUTE OF ETHIOPIAN STUDIES KASA AND KASA ይላል:: በብዛት በእንግሊዘኛ የተጻፈበት ሲሆን አማርኛም አለው:: በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ብዙ የተለያዩ ምሁራን ስለ አጤ ቴዎድሮስ ጽፈዋል:: ከነዚህም አንዱ ስዩም ወልዴ "የቴዎድሮስ ገጽታ በታሪካዊ አሣሣል ውስጥ" ብለው ሰፋ ያለ ማብራሪያ ሰጥተዋል::

ስዩም ወልዴ <u>KASA AND KASA</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 163 "ከሃምሳዎቹ ሁለተኛ አጋማሽ በኋላ በርካታ የቴዎድሮስን ገጽ የሚጠቁሙ ወጣት ሠዓሊዎች ታይተዋል:: በቴዎድሮስ ገጽታ በተከታታይ ከቀረቡት ከነዚህ ወጣት ሠዓሊዎች መካከል አብዛኛዎቹ በአዲስ አበባ የሥዕልና የቅርፃቅርፅ ትምህርት ቤት ይማሩ የነበሩ ናቸው:: ታደሰ በላይነህ፤ዳንኤል ጣፌ፤ታዬ ታደሰ መስፍን እሸቱ ጥሩነህ፤ሙሉጌታ ታፈሰ ደምሴ ሺፈራው ኪዳኔ በላይነህ ይገኙበታል:: ከአማተር ሠዓሊዎች መካከል ደግሞ ሻምበል ለማ ጉያና እኔም ራሴ ጭምር እንገኝበታለን::"



"በተለይ ባለፉት ሃያ ዓመታት በሥዕል፤በቅርፃቅፅና በኀትመት ጥበብ ውስጥ የቴዎድሮስ ምስል በብዛት ተሠርተዋል:: ለብዙዎቹ ተደጋጋሚ የፈጠራ ገጽ ባሕርይ ሆኗል:: ለምሳሌ የአዲስ አበባው ስነጥበብ ትምህርት ቤት መምህር ታደሰ በላይነህ ከሶቪየት ኅብረት ትምህርቱ መልስ በኋላ ከ1962 ጀምሮ የቴዎድሮስን ገጽታ በተለያዩ ድርሰቶች ደጋግሞ ሠርቶት እናገኛለን" ሲሉ ጽፈዋል::

ታዬ ታደሰ <u>አንዳንድ የኢትዮጵያ ሠዓሊዎች አጭር የሕይወት ታሪክ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 95 አጤ ቴዎድሮስ በሠራዊት ታጅበው ጉዞ ወደ መቅደላ ሲያደርጉ የተሣለው ሥዕል እጅግ ይማርካል:: ብሔራዊ ቱሪዝም ኮሚሽን ገጽ 173 "ሰውየው ቴዎድሮስ" የሚለው ሥዕል በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም የተሣለ ሲሆን ገጽ 175 በአዲስ አበባ ሥነ ጥበብ ት/ ቤት "ቴዎድሮስ" ይታያል:: በገጽ 209 ላይ እጅግ ማራኪ የሆነ የአጤ ቴዎድሮስ ሥዕል ይታያል:: በአዲስ አበባ ሥነ ጥበብ ት/ቤት "ውርስ"ይላል::

አጤ ቴዎድሮስ ከመድፋቸውና 7 ጀግኖች ጠበንጃና ጋሻ ይዘው በአንድ ምስል የቀረበ ሲሆን መልእክቱ "ውርስ" የሚለው የአደራ መልእክት እንዳለብን ለእኛውና ለሚቀጥለው ትውልድ መልእክቱን አስተላልፏል:: ከአንድ መጽሐፍ ውስጥ 4 ምስሎች ቀርበዋል::

ሠዓሊው ኤሪክ ሮብሰን ትርጉም ሰሎሞን ሙሉነህ <u>የኢትዮጵያ ታሪክ በሥዕል</u> ከተባለው መጽሐፍ ገጽ 31-32 ጠቅለል አድርጎ የእርሳቸውን ዓላማ በአጭር ከገለጠ በኋላ የሚታየው ሥዕል ቴዎድሮስ ከነሠራዊቱ መድፉን እየገፋ ሲጓዝና እርሳቸው ራሳቸውን ሲገድሉ ካሳየ በኋላ መቅደላን፤ ማኅተማቸውንና ዘውዳቸውን አስቀምጧል:: ይህንና ይህን በመሰለ አሣሣል ታሪካቸውን ለአለነው ትውልድ ሠሰዓልያን አቅርበዋል::

እኛም ኢትዮጵያውያን ከአገራችን ወጥተን በስደት ዓለም እንኖራለን:: ታሪካቸውን በመሣል የሚታወቁ ሰዓልያን በስደቱ ዓለም እንዳሉ ይታወቃል:: ነገር ግን የተሣለው ሥዕል እንዲሁ ሰብሰብ ብለው በአንድ የሞያ ማኅበር አዘጋጅተው ያቀረቡት መጽሐፍ ባለመኖሩ ማንነታቸውን ለማወቅ አልቻልንም:: አጤ ቴዎድሮስ ትናትም ዛሬም ነገም የተባለውን መጽሐፍ ለመጻፍ ስጀምር ሠዓልያንን ለማግኘት ብዙ ጥሬ ነበር::

ለመጀመሪያ ጊዜ ኮሎምቦስ አጓዮ በአቶ መልኩ በላይነህ በኩል ሰዓሊ ኪሩቤልን አግኝቼ የአጤ ቴዎድሮስን ሆነ የሌሎችን የምፈልገውን ሥዕል ሥሎ ልኮልኛል:: እኔም በመቀጠል ሌላ ሠዓሊ ስፈልግ እስክንድር ስዩምን አገኘሁ:: እርሱም የዚህ መጽሐፍ መሸፈኛ የሆነውን ሥዕል ስሎልኛል:: እንዲሁ ደግሞ በዲያቆን አቢይ መኮንን በኩል ሰዓሊ ተስፋየን አገኘሁ:: እርሱም የአጤ ቴዎድሮስን፣የራስ እንግዳንና የፊታውራሪ ገብርዬን ስሎልኛል:: በዚህ አጋጣሚ እነዚህን ሰዓልያን ከልብ አመሰግናለሁ:: እንግዲህ በያንዳንዳንዱ ስዕል ግርጌ የሰዓልያኑን ስም እገልጻለሁ::

አጤ ቴዎድሮስ የሚታወቁት በሹርባ እንጂ ዘውድ ጭነው ተሥለው አይተን አናውቅም:: ነገር ግን እርሳቸው አጤ እንደመሆናቸው መጠንና ዘውዳቸውም ዛሬ ድረስ በክብር ተቀምጦ ያለ እስከሆነ ድረስ ለምን ዘውድ ጭነው አይሣሉም? በማለት እኔ እንዲሣሉ አድርጌአለሁ::

አጤ ቴዎድሮስ ዘውድ ደፍተው ተሥለው ከመጽሐፉ የውጭ መሸፈኛ እንዲሆን ማድረጌ ከታሪክ ውጭ ሳይሆን ከታሪክ ያለ ነው:: ከታሪክ ያለ ነው ማለቴ ዘውድ ጭነው የተሣሉት ነው ለማለት ሳይሆን የንጉሠ ነገሥት ዘውድና ማኅተም ያላቸው መሆናቸውን ለመግለጽ ነው:: መተማመኛው ደግሞ ዘውዳቸውና ማኅተማቸው ክፍል አሥራ አራት ምሥራፍ 4 ላይ ይመልከቱ::

## አጤ ቴዎድሮስ በደራስያን

አጤ ቴዎድሮስን አስመልክቶ ብዛት ያላቸው ኢትዮጵያውያን ደራስያንና ተዋናያን ጽፈዋል የአጤ ቴዎድሮስ ታሪካቸውን አንዱ የዘነጋውን ሌላው በማስታወስ በኢትዮጵያ ውስጥ ከነገሡት ነገሥታት በሁለተኛ ደረጃ የተጻፈላቸው አጤ ቴዎድሮስ ናቸው ብል ማጋነን አይሆንም::

በኢትዮጵያ ውስጥ ከነገሡት ነገሥታት ታሪካቸው በብዛት የተጻፈላቸው ቀዳማዊ አጤ ኃይለ ሥላሴ ሲሆኑ በሁለተኛ ደረጃ አጤ ቴዎድሮስ ናቸው:: አጤ ቴዎድሮስ በሕይወት በነበሩበት ዘመን ሦስት መዋዕለ ዜናቸውን የጻፉ ደራስያን መኖራቸው አይዘነጋም::



በነገራችን ላይ አለቃ ዘነብ የአጤ ቴዎድሮስን ታሪክ የጻፉት እርሳቸው ከሞቱ ከአሥር ዓመት ቆይታ በኋላ ሲሆን እንዲሁም አለቃ ወልደ ማርያም የጻፉት አጤ ቴዎድሮስ ከሞቱ ከ13 ዓመት በኋላ መሆኑን "ይህ ታሪክ የተጻፈ ቴዎድሮስ ከሞቱ ከ13 ዓመት በኋላ ነው" ሲሉ የመጽሐፉ መደምደሚያ አድርገውታል::

ስማቸው ያልታወቀው ደራሲ የትግራይ ተወላጅ ሳይሆኑ አይቀሩም ለዚህም እርሳቸው ከጻፉት ውስጥ ግእዝ ያልሆነ የትግርኛ ግጥም በመገኘቱ ምክንያት ነው:: እርሳቸው አጤ ቴዎድሮስ ሲነግሡ ጀምሮ አብረው የነበሩ ናቸው የሚሉ አሉ:: ያም ሆነ ይህ ሦስቱም ደራስያን ከአጤ ቴዎድሮስ ጋር አብረው የነበሩ ናቸው::

1ኛ አለቃ ዘነብ ዘብሔረ ሸዋ
2ኛ አለቃ ወልደማርያም ዘብሔረ ሸዋ
3ኛ ስማቸው ያልታወቀው ደራሲ ምናልባት ዘብሔረ ትግራይ ናቸው::
4ኛ ሌላም ለንባብ ያልቀረበ መጽሐፍ በዘጌ ገማድ መኖሩ ታውቋል::

ቀደም ብዬ ሉስ አንጀለስ በነበርኩበት ወቅት አዛውንቶች ሰብሰብ ሲሉ እኔ ጠጋ በማለት ጨዋታ ማዳመጥ እወድ ነበር:: ታዲያ አንድ ቀን ደጃዝማች ብርሃነ መስቀል ደስታ በተለያዩ ገዳማት ሲዘዋወሩ ሳለ የአጤ ቴዎድሮስ ታሪክ የተጻፈ መጽሐፍ ማየታቸውን ሲናገሩ ሰምቼ ነበር:: ይህን የሰማሁት በ1986 ዓም መሆኑን አስታውስ ነበር:: ቦታውም አዋሽ ምግብ ቤት ነበር::

መጽሐፉን ያዩበት ቦታ የት እንደሆነ ለማጣራት የካቲት 23 ቀን 2003 ዓም ማታ ስልክ ደወልኩላቸው:: ደጃዝማችም ያዩበትን ቦታ:: በዚህ አጋጣሚ ደጃዝማች ብርሃነ መስቀል ከልብ አመሰግናለሁ:: የእኔ ጥያቄ " ደጃዝማች የአጤ ቴዎድሮስ ታሪክ የተጻፈበት መጽሐፍ ከገዳም ማየትዎን ሲጫወቱ ሰምቼ ነበር:: ያንን መጽሐፍ ያዩበት የት ገዳም ነው? ሌላው ከነዚህ ከታወቁት 3 መጻሕፍት የተለየ ነው ወይ?" የሚል ጥያቄዬ ጠይቄ ይህንን መልሰውልኛል::

<u>ደጃዝማች ብርሃነ መስቀል ደስታ</u> "በ1950 ዓ.ም የላስታ አውራጃ አስተዳዳሪ በነበርኩበት ወቅት ዜና ላሊበላል የተባለውን መጽሐፍ ለመጻፍ ሳቅድ በተለያዩ ገዳማት ስዘዋወር ሳለ ጎጃም ክፍለ ሀገር ዘጌ ደረስኩ:: የገዳሙ መነኮሳት መጻሕፍት እንደሌላቸው ነገሩኝ:: ነገር

ግን ማንነቴን ከገለጽኩላቸው በኋላ ለእርስዎማ ችግር የለም ብለው መጻፍቱን ሁሉ አሳዩኝ:: አጤ ቴዎድሮስ ሲሞቱ የተለዩ አብረው የነበሩ ስማቸውን ዘነጋሁት አለቃ መሆናቸውን አስታውሳለሁ::"

"ዛሬ በተለያዩ መጻሕት ተጽፈው የምናያቸውን ግጥሞች ተጽፈውበታል:: ከገዳሙ ያየሁት መጽሐፍ ዛሬ በተለያዩ የታሪክ መጻሕፍት ጥቅስ ተጠቅሰው የምናያቸው መጻሕፍት አይደሉም ሌላ ነው:: እንዲያውም ከማስታውሰው አጤ ቴዎድሮስ ቅድሚያ ሊገድሉ የፈለጉ ባለቤታቸውን ነበር:: ስትርበተበትባቸው ጊዜ በይ ተይው ብለው ራሳቸውን እስኪገድሉ ድረስ አብሬ ነበርኩኝ ይላል ደራሲው:: ይህን አልረሳሁትም አስታውሳለሁ:: ዋና ዋና ፍሬ ነገሮችን ገልብጠው ሰጥተውኝ ነበር:: ነገር ግን ደርግ ወደ 800 መጻሕፍት ሲዘርፈው አብሮ ዘርፏታል" በማለት ነግረውኛል::

በጣም የሚገርመው ነገር ቢኖር ያ ሁሉ ደብተራና ካህናት የቤተ ክርስቲያን ምሁራን የበዙበት ጎንደር አጤ ቴዎድሮስን አስመልክቶ ስም ማጥፋት እንጂ የታሪክ ማስታወሺያ ጽፎ የተዎ አለመኖሩ ነው:: እኔ ከእጄ የገቡትን አጤ ቴዎድሮስን አስመልክቶ የተጻፉትን መጻሕፍት ደግሜ ደጋግሜ አንብቤአለሁ:: እንኳን የቀድሞው ይቅርና ዛሬም በጎንደር ደራሲ የለም? ለምን ይሆን በጎንደር ደራሲ ያልተወለደበት?

የጎንደር ሰው የታሪክ መጻሕፍትን ከማገላበጥ ይልቅ መሳሪያ አንግቦ ለዳር ደንበር መዋጋትን ስለመረጠ ነው የሚሉ አሉ:: የአጤ ቴዎድሮስ ስም ተጠቅሶ የተጻፈባቸው መጻሕፍት ከእጄ የገቡትና ያሉት እነዚህ ናቸው::

1ኛ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ከአጤ ልብነ ድንግል እስከ አጤ ቴዎድሮስ፤
2ኛ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ከአጤ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ አጤ ኃይለ ሥላሴ
3ኛ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ አጤ ቴዎድሮስ እና የኢትዮጵያ አንድነት
4ኛ ገሪማ ታፈረ አባ ታጠቅ ካሳ የቋራው አንበሳ
5ኛ ጳውሎስ ኞኞ አጤ ቴዎድሮስ
6ኛ ትርጉም ዳኛው ወልደ ሥላሴ የእሥራት ዘመኔ በሐበሻ አገር ዶ/ር ብላንክ፤

አንድ ሰው መጽሐፍ ሲጀምር የአጤ ቴዎድሮስን ስም በብዛት የሚጠቅስ አለ:: ሌሎችም እንዲሁ ከእጄ ከገቡት ከዚህ መጽሐፍ በያንዳንዱ ምዕራፍ የተጠቀሱ እንደ ምሳሌ ልንወስዳቸው



እንችላለን:: አጤ ቴዎድሮስን አስመልክቶ ብዛት ያላቸው ደራስያን የጻፉ መሆናቸው አይዘነጋም::

## ታሪካዊ ልብ ወለድ መጻሕፍት

ታሪካዊ ልብ ወለድ ድርሰት አጤ ቴዎድሮስን አስመልክቶ ሦስት መጻሕፍት ተጽፈዋል:: ከእጄ የገቡት
1ኛ አቤ ጎበኛ አንድ ለናቱ
2ኛ ብርሃኑ ዘሪሁን የቴዎድሮስ እንባ
3ኛ ብርሃኑ ዘሪሁን የታንጉት ምስጢር የተባሉ መጻሕፍት ናቸው::

## በእንግሊዘኛ ቋንቋ የተጻፉ፤

በውጭ አገር ሰዎች ሆነ በኢትዮጵያውያን አጤ ቴዎድሮስን አስመልክቶ ብዙ መጻሕፍት ተጽፈዋል:: ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ የተተረጎመውን ከአማርኛው መጻሕፍት ተርታ ዘርዝሬዋለሁ:: ከዚህ ጀምሮ ደግሞ የምዘረዝረው በእንግሊዘኛ የተጻፉትን መጻሕፍት ይሆናል::

1 Acton,Roger The Abyssinan Expedition
2 DARRELL BATES THEABYSSINIAN DIFFICLTY
3 SVEN RUBNSON TEWODROS AND HIS CONTEMPORARIES 1855-1868
4 INSITUTE OF ETHIOPIAN STUDIES KASA AND KASA ከዚህ ዝቅ ብሎ የተጠቀሱት መጻሕፍት እኔ በዓይኔ አላየኋቸውም አንብቤም ጥቅስ አልወሰድኩም:: ነገር ግን መኖራቸውን አቶ ፈንታሁን ጥሩነህ ሰብስበው ልከውልኛል:: ፈረንሳይኛንና ጣልያንኛውን መጻሕፍት ግን እርሳቸው ቢልኩልኝም እኔ አልጠቀስኳቸውም::

1 Sven Rubnson Tewodros 2nd who he?
2 Sven Rubnson King of Kings, Tewodros of Ethiopia
3 Richard Pankhurst. History of Ethipian Tents from Mediaeval Times to the Reign of Emperor Tewodros
4 Richard Pankhurst. A-Social History of Ethiopia.the Northern and Central Highlands from Early Medieval Ttmes to the Rose of Emperor Tewodros

5 Richard Pankhurst, with Germa Selassie Asfaw, Tax Records of Emperor Tewodros of Ethiopia,1855-1868.
6 Roberto Sciaky, Ethiopia.Tewodros to Menelik.postal History from the napier Expedition to the indepedebt Imperial post 1867-1908
7 Philip Marsden, the barefoot Emperor,an Ethiopian Tragedy
8 Rita Pankhurst the Library of the Emperor Tewodros 2nd at Maqdala
9 Kirsten Pedersen The History of the Ethiopian Community in the Holy Land from the time of Emperor Tewodros በነገራችን ላይ በአማርኛ ከተጻፉት መጻሕፍት ይልቅ በውጭ አገር ቋንቋ ስለ አጤ ቴዎድሮስ የተጻፉት መጽሐፍት ይበዛሉ::

## አጤ ቴዎድሮስ በተውኔትና በተዋንያን ዘንድ!

ተውኔት ማለት በእኛ ቋንቋ ለድራማ የሚቀርብ ገጸ ባሕርይ ያለውን ለመግለጽ ሲባል በእንግሊዘኛ ቋንቋ አክተር የሚለውን "ተዋናይ"ይባላል:: ለምሳሌ ታማኝ በየነ፣ "ተዋናይ" ሊባል የሚችል ነው:: የእርሱን ስም ጠቀስኩት እንጂ ብዙ አሉ:: አርቲስት ታማኝ ከማለት ተዋናይ ታማኝ ማለት ገጸ ባሕርዩን ይገልጻል::

አርቲስት የሚለው ሰዓልያንን ለማለት ይመስለኛል እኛ ግን ድምጻውያኑንም ሠዓልያኑንም ተዋንያኑንም ሁሉንም አርቲስት እያልን እንጠራለን ትክክል አልመሰለኝም:: አጤ ቴዎድሮስን በተውኔት ዘንድ የሚገልጸው የተውኔት ሰዎች ማለትም ተዋያን አጤ ቴዎድሮስን አስመልክቶ የሠሩአቸውን ሥራ ለመግለጽ ነው:: ስለዚህ አጤ ቴዎድሮስ በተውኔት ሰዎች ዘንድ እንዴት ቀርበዋል? ተዋንያን ቅድሚያ ታሪክን በጽሞና ማንበብ አለባቸው::

ታሪክን ጠንቅቀው ካወቁ በኋላ ቢያንስ ከግማሽ በላይ የሆነውን ትክክለኛ ታሪክ ሲያቀርቡ ሌላው ደግሞ ማጣፈጫ ሊሆን ይችላል:: በዚህ ምክንያት በአጤ ቴዎድሮስ ዙሪያ ብዙ ተውኔት ተሠርተዋል፣ ለወደፊቱም ሊሠሩ ይችላሉ:: እኔ ከሰበሰብኩት ሠነድ አኳያ የአጤ ቴዎድሮስን ያህል በተውኔት የተጻፈላቸው አጤዎች ያሉ አይመስለኝም:: ለእርሳቸው ብዙ ተጽፏል::

ቅድሚያ ለአጤ ቴዎድሮስ ተውኔት የጻፉት ፊታውራሪ ግርማቸው ተክለሐዋርያት ሲሆኑ ተውኔቱን አልተመለከትኩም ተውኔቱን ወደ



መጽሐፍ ቀይረው ለአንባብያን አቅርበውታል:: ሌላው ጸጋዬ ገብረ መድኅን ናቸው:: አሁን በቅርቡ ደግሞ ተዋናይ ጌትነት እንየው የዛሬ 3 ዓመት ጽፈው ተውኔቱን ሠርተዋል:: ተዋናይ ጌትነት እንየውን አስመልክቶ በጋዜጣ ያነበብኩት "ታሪኩን እንየው" ብለዋቸዋል:: የቴዎድሮስ ራእይ የተውኔቱ ተመልካቾች ናቸው:: ከማድነቃቸው በላይ ስማቸውን እስከ መቀየር ደረሱ::

ጌትነት እንየው "የቴዎድሮስ ራእይ" ይላል:: ይህን ተውኔት በመጀመሪያ ስመለከተው አልቅሻለሁ:: ይህ ተውኔት የተዋጣለት ሲሆን የኢትዮጵያን አንድነት የሚወድ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የሚያስቆጭና የሚያስቆጣ ልባችን ወደ ሀገራችን እንድንገባ የሚገፋፋ ሥራ ሲሆን ለወደፊቱ ሌሎችም ተዋናዮች እንደሚጽፉ ተስፋ አደርጋለሁ::

እንዲሁም የባለቤታቸውን የቴጌ ተዋበችን ታሪክ ተዋናይ ጠለላ ከበደ ተዋበች ሁነው መሥራታቸውን ቅንጭብታ አንብቤአለሁ:: ከዚህ ተውኔት ድራማ ዋናው የቴጌ ተዋበች ይሁን እንጂ የአጤ ቴዎድሮስን ታሪክ በመጠኑ አይነካም ማለት አይደለም:: ተውኔቱን ስላላነበብኩትና ሙሉውን የተውኔት መጽሐፍ ባለማንበቤ ጥቅስ ልወስድ አልቻልኩም::

አቶ ወልደ ገብርኤል አሰጌ፣ "የአጤ ቴዎድሮስን ድርማ ጽፌ ጨርሻለሁ:: ነገር ግን አሜሪካን አገር ግጥሙን አስጠንቶ ለተመልካች ማቅረብ ከባድ ነው:: ኢትዮጵያ ገብቶ ተዋናይ ሰብስቦ ለማስልጠን ደግሞ የገንዘብ አቅም ችግር ስለሚፈጥር እንጂ ጽፌ ከጨረስኩኝ ብዙ ጊዜዬ ነው:: ድራማው (መንጠላዊት)ይባላል:: በቴዎድሮስ ታሪክ ላይ የተመሠረተ ነው" ብለውኛል:: እርሳቸው የልጃቸውን የልዑል ዓለማየሁን ታሪክ ደርሰው ጎንደር ማሳየታቸውን ነግረውኛል:: ተውኔቱ ወደ መጽሐፍ ተለውጦ በ1966 ዓም ታትሟል:: መጽሐፉንም ልከውልኝ አንብቤዋለሁ::

ወልደ ገብርኤል አሰጌ መስፍኑ ምርኮኛ በተባለው የተውኔት መጽሐፍ ገጽ 65 "ቴዎድሮስ በታላቅ ድምፅ እየተንጎራደደ መጋረጃ ይከፍታል:: አንድም ቀን ሳይኖረን ደስታና ተድላ
ሱሪና ድጋችን ፈጽሞ ሳይላላ
ቃጠቅ ፈረሳችን አሸዋ እየበላ

በጥቅጥቅ በረሃ በሐረር በዙላ
ቀዩ ሰው ሲጠቁር ጥቁር ሰው ሲቀላ
ዘወትር ጧት ማታ ጎራዴ ውልወላ
ልንጠጣው ነው መሰል ሽጉጣችን ፈላ
ነገ ምስክር ነሽ ታዘቢ መቅደላ”
ብለው መናገራቸውን ጽፈዋል።

በአጤ ቴዎድሮስ ላይ ታሪካዊ ድርሰቶች በግጥም መልክም ተጽፈዋል። ራሱን ችሎ የግጥም መጽሐፍ የተጻፈ ከእጄ ባይገባም ስለ ሌላ ሲጽፍ ቆይቶ ሳያስበው ወኔው ነሽጦት ወደ አጤ ቴዎድሮስ የሚገባው ደራሲ ብዙ ነው። ጸጋዬ ገብረ መድኅን እሳት ወይ አበባ ከተባለው መጽሐፋቸው ያን ያህል ሲጽፉ ከቆዩ በኋላ ደግሞ ስለ አጤ ቴዎድሮስ እንዲህ ይላሉ።

## ግጥም፤

ጸጋዬ ገብረ መድኅን <u>እሳት ወይ አበባ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 212
“ይልቅስ ተረት ልንገርሽ፤የተላከ ከእንግሊዝ ዘንድ
እጅህን ስጥ አለኝ ፈረንጅ፤እጅ ተይዞ ሊወሰድ፤
ምን እጅ አለው የእሳት ሰደድ?
አያውቅም ከንዴ እንደሚያነድ” ሲሉ ጽፈዋል።

ታማኝ በየነ <u>ካሳን አትቀስቅሱት</u>
ካሳን አትቀስቅሱት ይብቃው ከንዱ ይረፍ
በሰላም ይተኛ ያሸልበው እንቅልፍ
መይሳውን ተዉት ያንን ዳልጋ አንበሳ
ተራውን ይተኛ ዳግም አይነሣ” ሲሉ ገጥመው ነበር። የተዋናይ ታማኝን ግጥም ሙሉውን ክፍል አሥር ምዕራፍ ሁለት ጽፌዋለሁና ይመልከቱ።

ብርሃኑ ጣሰው <u>ሰቆቃው ወፍቅር</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 87
“በአጤ ቴዎድሮስ ጉልበት የተገባደደ
በተክለ ጊዮርጊስና በዮሐንስ በምኒልክ የተዋደደ
ኢትዮጵያን አንድ አድርጎ አዋሐደ” ሲሉ ጽፈዋል።



አጤ ቴዎድሮስን አስመልክቶ ራሱን ችሎ የተጻፈ የግጥም መጽሐፍ ከእጄ ባይገባም ቅሉ ብዛት ያላቸው ኢትዮጵያውያን በየመጻሕፍታቸው ሳይጠቅሱ አያልፉም። ባለፈው ዓመት ካሊፎርንያ ከሊቀ ጠበብት አዱኛው ወርቁ ጋር ቁጭ ብለን ትራቱን ስንመለከት ሳለ ተዋናይ ዮኒ ስሎሞን ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ አንሥተው በእንግሊዘኛ ግጥም ካሰሙን በኋላ ጋሼ አዱኛው ወርቁ እንዲህ አሉ።

ሊቀ ጠበብት አዱኛው ወርቁ <u>የሚያስተውለው ሰው የሚያውቅለት ጠፍቶ</u>
“የሚያስተውለው ሰው የሚያውቅለት ጠፍቶ
ያለጊዜው ሄደ ያለ ጊዜው መጥቶ
የኢትዮጵያን ጥፋት ማየት የማይወደው
የፍቅሩ ማስረጃ ለራሱም ቆራጥ ነው
እንደ ቴዎድሮስ ያለ የሚገኝ መቼ ነው?”

በማለት ሲናገሩ ሁለቱን ዘለላ ጻፍኩት ሦስቱ ዘለላ ሳልጽፈው አመለጠኝ። መልሼ ልጠይቅ ቀና ስል ዓይናቸው በእንባ ተሞልቶ በማየቴ ደግሜ ልጠይቅ አልቻልኩም። ወራት በኋላ ስልክ መታሁና ስንጨዋወት ሁለቱን ዘለላ ግጥም ሳነሣላቸው የቀሩትን ስንኞች ደገሙልኝ። ግጥሙ ደስ ስላለኝ ከላይ የተጠቀሱት ናቸው።

## ድምጻውያን

ከቅርብ ዘመናት ወዲህ አጤ ቴዎድሮስን አስመልክቶ ከገጠሪቱ ኢትዮጵያ ባህላዊ ድምጻዊ ወደ ከተማ ዘመናዊ ድምጻዊ ጎራ እየተስተጋባ ነው። የገጠሪቱ ኢትዮጵያ ድምጻውያን ቤተ ክርስቲያን ሄደው እንኳን መሰንቆአቸውን ጠበቅ ካደረጉ በኋላ እንዲህ ይላሉ።

“ክብር ተመስገን የኛ ጌታ
ከጧት አንሥቶ እስከ ማታ
ካሉ በኋላ የበገናውን ዘለሰኛ አንሥተው
“ታጠቅ ብሎ ፈረስ ካሳ ብሎ ስም
ዓርብ ዓርብ ይሸበራል ኢየሩሳሌም” ይላሉ።

አሁን የገጠሪቱ ኢትዮጵያ ባህላዊ ድምጻውያን ወደ ከተማ እየገቡ ስለ አጤ ቴዎድሮስ ማዜም ጀምረዋል። ምናልባት አንዱን ትቼ አንዱን መጥቀስ እንዳይሆንብኝ እንጂ ብዙ ባህላዊ ድምጻውያን አጤ

ቴዎድሮስን ከደራስያን በላይ ከፍ እያደረጉ ናቸው:: ከሕቶቻችን ድምጻውያን መካከል ከብዙ በጥቂቱ ድምጻዊት አቦነሽ አድነው፣ ድምጻዊት ንግሥት አፈወርቅ፣ድምጻዊት ኀብስት ጥሩነህና ድምጻዊት ማናልሞሽ ዲቦ፣ድምጻዊት አምሳል ምትኬና ድምጻዊት ገነት ማስረሻ ሌሎችንም ድማዊት መጥቀስ ይቻላል::

ከወንዶች ድምጻዊያን መካከል ከብዙ በጥቂቱ ድምጻዊ ሻምበል በላይነህ፣ድምጻዊ ሀብተ ሚካኤል፣ድምጻዊ ፋሲል ደመዎዜ እና ድምጻዊ ማንዴጎ አፈወርቅ፣ሌሎችም ስማቸውን ያልጠቀስኩት ድምጻውያን በአጤ ቴዎድሮስ ጀግንነት ላይ ተንተርሰው እያቀነቀኑ ናቸው:: ሌላው ቀርቶ በቤተ ክርስቲያን የአርባ ጾም ቢገና አጤ ቴዎድሮስ እርሳቸው ሲሙቱት የነበረው እንዳለ ዜማው ሁኖ በወቅቱ የነበሩ አባቶች ደግሞ ከሞቱ በኋላ የጨመሩት ግጥም ታክሎበት ይዘመራል:: ሰዓልያንም የታሪክ ደራስያንም ድምጻውያንና ገጣምያን አጤ ቴዎድሮስን አስመልክቶ የጻፉትንና ያዜሙትን ዋቢ በማድረግ እነሆ አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ ትናንትም ዛሬም ነገም የተባለው መጽሐፍ ለንባብ ቀርቧል::

## ዘጋቢዎች ጋዜጠኞች

በአጤ ቴዎድሮስ ዙሪያ ጋዜጠኞች ብዙ ጽፈዋል:: ከላይ የጠቀስኳቸው አቶ አቤ ጎበኛና አቶ ብርሃኑ ዘሪሁን የጻፉት ምስክር ነው:: ኋላም አቶ ጳውሎስ ኞኞ "አጤ ቴዎድሮስ"በሚል የጻፉት መጽሐፍ ተወዳዳሪ የሌለው የታሪክ መጽሐፍ ሲሆን ጋዜጦችና መጽሔቶች ላይ ብዙ ስለ አጤ ቴዎድሮስ ተጽፏል:: ለወደፊቱም ሌሎች ወጣት ጋዜጠኞች ታሪክ መጻፋቸው አይቀርም::

በውጭው ዓለም ያሉ ጋዜጠኞች እንዲሁ ብዙ ጽፈዋል:: በተለይ የጀርመን የሬዲዮን ጋዜጠኛ አቶ ተክሌ የኋላ ራእይ መጽሔት ላይ በአጤ ቴዎድሮስ ዙሪያ ሰፊ ዘገባ አቅርበው ነበር:: እንዲሁም በኢትዮጵያ 2000 ዓም ዋዜማ ምልኒየም ወራት የአጤ ቴዎድሮስን የልጅ ልጃቸውን ኮሎኔል ገናናው ካሳ መሸሻ ቴዎድሮስን ለማነጋገር ጥረው ሳይሳካላቸው የቀረ ቢሆንም ሊቀ ጠበብት ሮቤርሰንን በመጋበዝ ስለ አጤ ቴዎድሮስ ገለጻ እንዲያደርጉ ማድረጋቸው ብቻ ሳይሆን ራሳቸው በጣም ጥሩ ጥናት አቅርበው ነበር::



*ተክሌ የኋላ ጀርመን ዴዮን ጋዜጠኛ "ኢትዮጵያን መልሶ የሚያስተሳስር አንድ ሰው በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ተነሣ:: የዚህ ሰው ወይም የነሀ ሰው አነሣስና አወዳደቅ የሀገር ፍቅር ባላቸው ኢትዮጵያውያን ዘንድ ለዓላማ ጽናት ለክብርና ኩራት ተምሳሌት ለመሆን ቀጥኋል ወደፊትም ይቀጥላል:: አድማጮቻችን የዛሬው ፕሮግራማችን የሚያተኩረው በካሳ ኃይሉ ወይም ዳግማዊ አጤ ቴዎድሮስ ላይ ይሆናል::"*

*"የጥንታውይቷን ኢትዮጵያ ክብርና ሞገስ ለመመለስ በአንድነቷ ለጠንከረው የባሕር ወደቦቿን ከውጭ ነጻ አድርገው ሌሎችንም ለመታደግ ብሩህ ራእይ የነበራቸው የኢትዮጵያ ባል የኢየሩሳሌም ልጮኛ ይሉ ነበርና ሩቅ አሳቢ ቅርብ አዳሪ የመሆን እጣ ለስኪገጥማቸው ድረስ" ሲሉ አቅርበው ነበር::*

*ለፉ አድርገው አቅርበዋል::* በዚህ ቀን ዝግጅት ከቀረቡት መካከል ሊቀ ጠበብት ስቨን ሮቤርሰንና ሊቀ ጠበብት ማሞ ሙጬ፣ ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛውን አቅርበው የአጤ ቴዎድሮስን አነሣስና አወዳደቅ አስመልክተው ዘርዘር አድርገው አሰምተዋል:: ጋዜጠኞች አቶ ተክሌ የኋላ ብቻ ሳይሆኑ ብዙ ጋዜጠኞች ጽፈዋል:: ለወደፊቱም ይጽፋሉ: ከእኔ እጅ ያልገቡ ብዙ ጋዜጠኞች የጻፏቸው ይኖሩ ይሆናል::

## ምዕራፍ 2

## ለመጽሐፉ ጥቅስ የተጠቀምኩበት ፈሊጥ

ግርማ ተክለ ኢየሱስ የሰው ምግባርና የመከራ ቀምበር በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 2" ደራሲ ድርሰቱን ለማስፋፋትና አሳቡን ለማቃናት የሚችለው ታሪክን ተመልክቶ መጻሕፍትን መርምሮ ነው" ሲሉ ጽፈዋል:: ብዙ ሰዎች ሲጽፉ ለሥነ ጽሑፉ ውበት እንጂ ለታሪኩ ግድ የሌላቸው አሉ:: እኔ ደግሞ እምነቴ በሥነ ጽሑፉ ግርድፉ ሆኖ ቢቀርብም ታሪኩ በመረጃ የተጠናከረ መሆን አለበት ብዬ አምናለሁ::

ታደሰ ታምራት ውይይት ቅጽ 1 ቁጥር 2 ነሐሴ 1984 ዓም ገጽ 72 "የታሪክ ምርምር፣ እንደማንኛውም ሳይንስ፣የራሱ የሆነ ዘዴ አለው::

ይኸውም እንዲያው ባጭሩ፤ለሚጠና ዘመንና ጉዳይ መረጃዎች በትጋት ፈልጎ መሰብሰብ የአስተማማኝነት ደረጃቸውን ማጣራት በዝርዝር ማጥናት መተንተንና የተጣራ ዘገባ መስጠት ነው" ሲሉ ሊቀ ጠበብት ታደሰ ታምራት ጽፈዋል::

ታሪክ የራሱ የሆነ ዘዴው ምንድነው ከተባለ ማንኛውንም ሰነድ መሰብሰብና ማጥናት ነው:: የአንድን ደራሲ ሥራ መስረቅ መስሎ የሚታየኝ የደራሲውን ስም ሳይጠቅሱ የራስ አስመስሎ ማቅረብ ነው እንጂ የደራሲውን ስም ጠቅሶ መጽሐፉን ዘግቦ ገጹን ገልጾ በራሱ የጥናት ዘዴ ከሌላው ጋር አቀራርቦ መጻፍ መስረቅ አይደለም::

ዶ/ር የማነ ገ/ማርያም <u>የፍልስፍና መግቢያ ቅጽ 2</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 94 "ዳቦን የሚሹት ሊጎርሱት ሊበሉት ሊውጡት እንጂ ሊያዩት ወይም ሊልሱት አይደለም:: ማየትና መሳሱስ ለምንም አይበጅም:: በእጅ ይዘው ቢያሻሹትም ያው ነው:: እንደዚሁ ሁሉ ምርምር ማድረግ ትርጉም እንዲኖረው ከተፈለገ በአንድ ነገር ላይ ብቻ ማኘክ ይበጃል" ሲሉ ጽፈዋል::

በእኔ ግንዛቤ አንድ ደራሲ ስለሚጽፍበት ጉዳይ አስቀድሞ ሰነዶችን መሰብሰብና ጠንክሮ ማየት አለበት:: አበክሮ ካኘከውና ካጠናው በቋንቋ አገላለጹ የተዛባ ቢሆንም እንኳ ታሪኩ የታኘከና የተጠና ከሆነ ተከታዩ ትውልድ መሠረት የሚያገኝበትን ሰነድ ሊተው ይችላል:: ነገር ግን መጻሕፍትን ከማየት ገልጦ ማንበብ ይበልጣል:: ያ ከሆነ የተጣራ ታሪክ ሊጽፍ ይችላል::

ዶ/ር አየለ በከሪ <u>ሐመር መጽሔት</u> ጥር የካቲት 2000 ዓም ገጽ 17 "ባልተጠና መረጃ ታሪክ የሚጽፉ ሰዎች እንዳይበረክቱ ማድረግ የታሪክ ባለሙያዎች ተግባር ይመስለኛል" ሲሉ ተናግረዋል:: ስለ አንድ ጉዳይ ለመጻፍ ሲታሰብ በመጀመሪያ ያንን ጉዳይ ሊያጠናክር የሚችል ሰነድ ማሰባሰብ የአንድ ደራሲ ተግባር መሆን አለበት:: የሃይማኖት መጽሐፍ ከሆነ የተጻፈ በመሆኑ ሰዎች ተግባሩን እንዳይረሱ በየጸሎት ቤታቸው ይሰሙታል:: የታሪክ ጉዳይ ግን የሃይማኖት መጽሐፍ ስላይደለ መረጃ መሰብሰብ ጠቃሚ ይሆናል:: ከላይ ሊቅ አየለ በከሪ እንዳሉት ባልተጠናከረ መረጃ ታሪክ መጻፍ ውጤቱ መልካም አይሆንም::



የጻፏቸውን መጻሕፍት ጥቅስ ስለማበዛ ወዳጆቼ "ጥቅስ ታበዛለህ" በማለት ያስገነዘቡኝ ብዙ ናቸው:: እኔ ያደኩት ገጠር ሲሆን ያሳደጉኝ አያቴና የአያቴ ባልንጀራ ሲሆኑ ለአንድ ነገር ዋቢ ከሌለኝ ማውጋት እንዳልችል አስተምረውኛል:: ያም የአያቴ ባልንጀራ አባ ፈጠነ ሲመክሩ "እንኳን የሰው ልጅ የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በነቢያት የተነገረውን ለዋቢነት እየጠቀሰ ያስተምር ነበር "ይሉ ነበር::

ይህ አባባላቸው ከጭንቅላቴ አልፋቅ ብሎአል:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከነቢያት ጥቅስ እየጠቀሰ አስተምሮአል:: እንደሚታወቀው ኢትዮጵያዊቷ ንግሥተ ሳባ የንጉሥ ሰሎሞንን ጥበብ አድንቀው ነግረዋት ለማየት መሄዷን በታሪክ መጻሕፍት ተጠቅሶ ይገኛል::

መጽሐፈ <u>ነገሥት</u> 1ኛ 10፥ 1 "የሳባም ንግሥት በእግዚአብሔር ስም የወጣለትን የሰሎሞንን ዝና በሰማች ጊዜ በእንቆቅልሽ ትፈትነው ዘንድ መጣች" ይላል:: ይህን ታሪክ በአዲስ ኪዳን <u>ማቴ 12፥42</u> "ንግሥተ ዓዜብ በፍርድ ቀን ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥታ ትፈርድበታለች፥የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት ከምድር ዳር መጥታለችና እነሆም ከሰሎሞን የሚበልጥ ከዚህ አለ" በማለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጠቅሶ አስተምሯል::

ከዚሁ መጽሐፍ ቅዱስ በንዳጉ ቁጥሩ ተጠቅሶ ይገኛል:: ጥቅስ መጥቀስ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰደ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ሐዲስ፤ ስትመለከቱ ከቁሉይ ኪዳን ብቻ ሳይሆን አንዱ ሐዋርያ የጻፈውን ሌላው ሐዋርያ ስለጻፈው ከንዳጉ ላይ ምዕራፉና ቁጥሮች ተጠቅሰው ይገኛሉ:: አባቶቻችንም ብዛት ያላቸው ጠቃሚ መጻሕፍት ሲጽፉ የአጻጻፋቸው ፈሊጥና ዘዴ ልዩ ልዩ ይሁን እንጂ ዋቢ መጻሕፍት ሳይኖራቸው አይጽፉም::

ተካ አባዲ ትርጉም ደራሲው ዲቪድ ለዊስ <u>ጥቃት በናቶ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 235 "ከ20.000 (ሃያ ሺ) የሚበልጡ የታተሙ (መጻሕፍት፤መጽሔት፤ጋዜጣ በራሪ ወረቀት)ከ6 አገሮች ተዘዋውረን ባገኘነው ላይ ለብዙ ዓመታት ሰፊና ጥልቅ የሆነ ጥናት አድርገንበታል" ሲሉ ጽፈዋል::

እኔ ከሁለት መቶ በታች መጻሕፍትና መጽሔት ጋዜጣና በራሪ ወረቀት ሰበሰብኩ ተብዬ ስወቀስ ከፍ ተብሎ የተጠቀሰውን ጥቅስ ስትመለከቱ ደግሞ የእኔ ከምንም አይቆጠርም:: ስለዚህ እኔ "አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ ትናትም ዛሬም ነገም" የተባለውን መጽሐፍ ስጽፍ ከሀገራችን ደራስያን ብቻ ሳይሆን ከውጭ አገር ደራስያንም ስለ አጤ ቴዎድሮስ የተጻፈውን ሰብስቤ ለማቅረብ እሞክራለሁ::

አንዳንዶቹ አንባቢዎች ደግሞ "ከጋዜጣና ከመጽሔት ከበራሪ ወረቀት፣ ከመጣጥፍ የተለቀመ ጽሑፍ ለዋቢነት አይበቃም" በማለት የጻፉልኝ ብዙ ናቸው:: አሁንም ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ሐዲስ ኪዳን እንመለስና መልእክቶች ደብዳቤዎች ናቸው:: እነዚህ የደብዳቤ መልእክታት ዛሬ ላለነው ትውልዶች ትምህርት ሰጭ ናቸው:: ለምሳሌ በ1984 ዓም ላይ ርእሰ ብሔር አቶ መለስ ዜናዊ ለተባበሩት መንግሥታት ኤርትራ እንድትገነጠል የጻፉአት በራሪ ወረቀት 1 ገጽ ናት ነገር ግን አገር ያፈረሰች መሆንዋ አሊ አይባልም::

ስለዚህ በጦማር ጋዜጣ ሆነ በመጽሔት፥በበራሪ ወረቀት አልያም በነፋስ ድምጽ ራዲዮ በሌላም የተላለፈ ጽሑፍ ዋቢ ይሆናል:: አንባቢዎቼን ለማስገንዘብ የምፈልገው ሌላው ታሪክ "አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ ትናትም ዛሬም ነገም" ብዬ ለመጻፍ ወደ ተነሣሁበት ታሪክ ስገባ አጤ ቴዎድሮስ ለእንግሊዝ ንግሥት አምርረው የጠየቁት ዛሬ ድረስ ጥያቄው ያልተመለሰው በመጽሐፍ ሳይሆን በደብዳቤ ነበር::

የውጫሌ ውል የተጻፈባት አንስተኛ ወረቀት ናት:: መዘዟ ግን ረጅም ነው:: ስንት ሕዝብ እንዳስጨረሰች ዛሬ ድረስ ጦሱ አላለቀም:: እንዲያውም ከመጽሐፍ ይልቅ ብዙ ጠቃሚ ታሪክ የሚወጣው በጋዜጣና በመጽሔት ነው:: ምክንያቱም የአገራችን የሥነ ጽሑፍ ሀብት ቢኖርም የምጣኔ ሀብት አቅም ስለማይፈቅድ ብዙ ጠቃሚ የታሪክ ሰነዶች ለኅትመት ደርሰው አንባቢ ስለማያገኛቸው በጋዜጣና በመጽሔት እየተጨለፉ ይወጡ ነበር::

ለምሳሌ ከታሪክ አምባ ዐምድ ጦማር ጋዜጣ ሲያወጣው የነበረው ታሪክ (ከግርግብ)" ሐበሾች በውጭው ዓለም" የተባለው መጣጥፍ ስንቱን ኢትዮጵያዊ እንዳስተማረ አልጠራጠርም:: ስለዚህ መጽሐፍ ለመጻፍ ዋቢ መጠቀም ስንፍና መስሎ ለእኔ አይታየኝም:: ነገር ግን



አንዱ የለፋበትን ድርሰት ጥቅስ ሳይጠቅስ የራሱ አድርጎ መጠቀም ወንጀል ይመስለኛል::

አሥራት ገብረማርያም ግብረ ገብነት ሁለተኛ እትም በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 23 "አንድ ሰው ጥሮ ግሮ ያዘጋጀውን ድርሰት ወይም የዜና ቅኝት ያለ ደራሲው ፈቃድ ራሱ እንደደረሰው አስመስሎ ማቅረብ የሌብነት ወንጀል ነው:: ደራሲ የሌላውን ሰው ድርስት በመጥቀስ ቢጽፍ ሌብነት አይባልም" ሲሉ ጽፈዋል:: እኔ መጽሐፍ ስጽፍ የብዙ ደራስያንን መጽሐፍ ጥቅስ የምወስደው በሥርዓት እንጂ ያለ ሥርዓት አይደለም:: እኔ ከአንድ መጽሐፍ ጥቅስ ስወስድ በትክክል የታሪኩን ባለቤት ስም ጠቅሼ ነው::

አማረ አፈለ ብሻው ከጋንቤላ እስከ ሁመራ በተባለው መጽሐፍ ገጽ 185 "በእኔ እምነት እንኳን በወረዳ በአውራጃ የሚቋቋም ማኅበር ኢድስ ነው" ስል ጽፌ ነበር:: በዚህ ዓይነት የሸረደድኩአቸው ግለሰብ ጋር ጥር 10 ቀን 2002 ዓም ሎስ አንጀል ተገናኝተን እኔ በጻፍኩት መጽሐፍ በአሽሙር ሲጠርቡኝ "የሌሎችን ጽሑፍ እየጻፍክ ደራሲ ነኝ ትላለህ" አሉኝ:: የታሪክ መጽሐፍ እንዴት እንደሚጻፍ ቅድሚያ ከዚህ በፊት የታተሙ መጻሕፍትን ማንበብ ይጠቅማል::

አለቃ ታየ ወልደ ማርያም የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ በተባለው መጽሐፋቸው መቅድም" ይህንም ታሪክ ስናወጣው ከልብ አንቅተን ከሕሊና አውጥተን ልብ ወለድ የጻፍነው አይደለም:: ከመጻሕፍት ቅዱሳት፣ከቀድሞ ሰዎች ታሪክ ከመሐከለኞች ከኋለኞች ሊቃውንት የታሪክ መጻሕፍት ተመልክተን አርመን አስማምተን ያወጣነው ነው እንጂ" ይሉና" ከቀድሞ ሰዎች ታሪክ ያልነው ከሙርታድ፣ከግብጽ አዘጋጁ ነው::" ይሉና ኢትዮጵያን አስመልክቶ ከመጽሐፍ ቅዱስ ከተለያዩ ምዕራፍ የወሰዱበትን ጥቅስ ደርድረውታል:: ከዚያም በመቀጠል እንዲህ ሲሉ አክለውበታል::

"ከሊቃውንት የታሪክ መጻሕፍት ያልነው ከብዞች በጥቂቶች ከግሪክ ፕሮፌሰሮች፣ከአሚሮስና ከሄሮድቱስ፣ከእንግሊዝ ፕሮፌሰር ከጀምስ ብሩስ፣ከፈረንሳይ ሊቃውንት ከሻንፓዎንና ከምሪዮ፣ከጀርመን ሊቃውንት ከኢዮብ፣ልዶፍስና ከኢዘንበርግ፣ከአስተራቦን ከሞስንጀር፣ ቄርኔር ከፕሮፌሰር ሊትማን፣ከኢጣልያ ሊቃውንት ከዲማርቲኒስ ጂ ከሳሞኒ ኤሊ ከሳትራቤርሲ፣ ከኤሊ ቢቦኔ በጉኢዲ ኢግንዋዮጥ፣ወይም

ከዓረብ ሊቃውንት ከአዝርቅይ ከግብጽ ሊቃውንት ከኢይብኮ፤ ይስሓቅ ከአብልዝና ከአፊልፊል::"

"ከየመን ታሪክ መጽሓፍ እስክንድር ከዮሐንስ መደብር ከጊዮርጊስ ወልደ አሚድ በዘዋይ ከተገኘ የጥንት ታሪክ ከቀድሞው ክብረ ነገሥት ከነዚህም የሚበዛ ልዩ ልዩ ዓይነት ታሪክ ተቀስሞ ተለቅሞ ታርሞ የወጣ ነው:: ታሪክ መማርና ማወቅ ለብዙ ነገር ይጠቅማል:: በመጀመሪያ በድንቁርና የታወረ ዓይንን ይከፍታል:: ሁለተኛ ሰው የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነት በፍጥረቱንም ብዛትና የልዩ ልዩ ወገንንም ዓይነት የዓለምንም ታላቅነትና ስፋት ያይበታል" ሲሉ ጽፈዋል::

አለቃ ታየ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ ብዙም በአገር ቤት የታተሙ የታሪክ መጻሕፍትን ጥቅስ አልወሰዱም:: በብዛት ከውጭ አገር ድርሰት ተጠቅመዋል:: ይህ በውጭ አገር ድርሰት ዋቢ አብዝቶ መውሰድ ትክክል አይደለም የሚል እምነቴ የጠነከረ ነው:: ታሪክ ለሌላቸው አገሮች አማራጭ የላቸውም:: ነገር ግን ኢትዮጵያውያን ታሪክ ያለን በመሆኑ ብዙ መበደር አስፈላጊ አይመስለኝም:: ዛሬ ያሉት ምሁራን ወደ ገዳም ወርደው ምርምር ከሚያደርጉ ይልቅ አውሮፓ መጥተው መመርመር አብዝተዋል:: ቅድሚያ በሀገራችን ድርሰት አበልጽገን መጻፍና አልፎ አልፎ ሳይበዛ ብንጠቅስ መልካም ይመስለኛል::

እኛ እኮ ኢትዮጵያውያን የታሪክ ድሆች አይደለንም:: እኛ ኢትዮጵያውያን ኀብረት የለንም፤ስለዚህ ድሃ ነን:: ነዳጅ የለንም ድሃ ነን:: አገራችን በምጣኔ ሀብት ድሃ ነች:: ነገር ግን የታሪክ ድሆች አይደለነም:: የራሳችን ፊደል ያለን፤ የታሪክ መጻሕፍት ያለን ነን:: በተለይም ድርሰት ሞልቶናል:: የጎደለን በሀቀኝነት መዝግቦ ማስቀመጥ ነው::

ስለዚህ ቅድሚያ ታሪካችንን እኛ መጻፍ አለብን:: እስኪ ኢትዮጵያውያን "እኛ ለእኛ እንሁን" የሚል መፈክር አውጥተን እንቀሳቀስ:: ለእኛ የውጭ አገር ሰው ጽፎ ሊሰጠን አይገባም:: ስን ጽፍም በፊደላችን እንጻፍ:: የአፍሪካ አንድነት ድርጅት በግእዝ ፊደል ጽፎ በስህዋሊ ቋንቋ ለማስፋፋት ሲያስብ ያልተዋጠላቸው የእኛዎቹ መሪዎች ናቸው::



ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስና ጄኔራል ጃጋማኬሎ እነ ደጃዝማች ገረሱ ዱኪ፤እነ መሐንዲስ አያና ብሩና ሌሎች ስማቸውን ያልጠቀስኩት ጀግኖች አፍቃሪ ኢትዮጵያ የሆኑ ወገኖቻችን የተወለዱባት ሀገራችን ኢትዮጵያ አንዳንድ አሳፋሪ ተግባር የሚፈጽሙ ትውልዶችን እያፈራች ነው:: እኛ ኢትዮጵያውያን በሃይማኖትና በባህል ብንለያይም ደማችን አንድ ነው::

ዛሬ አንዳንድ ምሁራን የፈጠራ ታሪክ እንደሚያቀርቡት ሳይሆን በትክክል አንድን ኦሮሞና አንድን አማራ ፎቶ አስቀምጦ "ምረጥ የትኛው ነው ኦሮሞ፤የቱ ነው አማራ ሌላም ሌላ ..ተብሎ አንድ ሰው ቢጠየቅ ፎቶ አይቶ ጎሳቸውን ሊለያቸው አይችልም::"

"ይህ የሚያሳየው የኢትዮጵያ ሕዝብ በመልክ አንድ መሆናቸውና መዋሐዳቸው ነው:: ስለዚህ ሁላችን በታሪካችን እንኩራ፤በፊደላችን እንጻፍ፤ እኛ ለእኛ እንባባል:: ለእኛ ለኢትዮጵያውያን የውጭ አገር ተወላጅ ታሪክ ጽፎ የሚሰጠን እኛ ምን እየሠራን ነው? በእኔ እምነት እንደ ደራሲ ጥራት ያለው ድርሰት ለመድረስ ቅድሚያ ወገኖቹ የጻፉትን መጻሕፍት መጥቀስ ይኖርበታል::

ዶ/ር ሪቻርድ ፓንክረስት <u>ሉሲ መጽሔት</u> የካቲት 1985 ዓም ገጽ 37 "የኢትዮጵያን ታሪክ እስከዛሬም ቢሆን ከውጭ በሚገኙ ምንጮች ላይ ተመርኩዞ መጻፍ አግባብ አይደለም:: ኢትዮጵያዊ በሆኑ ምንጮች ላይ ማተኮር አለበት:: አለዚያ እገዳው ወይንም ማዕቀቡ ኢትዮጵያ በታሪክም በባህልም እየደኸየች እንድትሄድ ያስገድዳታል ምክንያቱም ታሪኳ በባዕዳን ምንጮች ላይ ብቻ ተንተርሶ ስለሚጻፍ ይሆናል" ሲሉ ትምህርታዊ መጣጥፍ ለመጽሔቱ አቅርበዋል::

ኢትዮጵያውያን የራሳችን ፊደል ያለን ሰዎች የራሳችን ቋንቋ ያለን ስንሆን እንዴት ከሌሎች ቁንጽል ታሪክ ልንቀበል ወደድን? ይህን ተግባር መተው እንዳለብን ዶ/ር ሪቻርድ ፓንክረስት፤ በአደባባይ ሊስኪገስጹን ቆይተናል:: ይህ መሆን የለበትም:: የራሳችን ታሪክ ሌሎች እስኪመክሩን መጠበቁ ውርደት ነው:: ታሪክ ለባለታሪኩ እንጂ ለባላገር ኢትዮጵያ ለኢትዮጵያውያን ብለን መነሣት የምንችለው መቼ ነው? እኔን የሚናፍቀኝ ነገር ቢኖር እኛ ለእኛ

የምንልበትን ዘመን ነው:: በታሪክ በፊደል ብቻ ሳይሆን ሥዕላችን ሁሉ ከአውሮፓ እየተቀዳ መምጣት ጀምሯል::

አንድ እንግሊዛዊ የሰጡትን ተግሣጽ ሳነብ ከልቤ ተሰምቶኛል:: እኚህ ሰው ትክክለኛውን ሃይማኖት ለማወቅ ብዙ ጥረት ሲያደርጉ የነበሩ ናቸው:: ብዙ ከመረመሩ በኋላ በግብጽ ኮፕቲክ ሃይማኖት ተጠምቀው ጥናት ሲጀምሩ አሁንም አልዋጥላቸው ይላል:: ከግብጽ ወደ ኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ይመጡና ገዳማቱን አንድ ባንድ ጎብኝተዋል:: በዚህ ተደስተዋል ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉት ሥዕላት ከሃይማኖቱ ጋር የሚጋጭና ነባሩ አሣሣል የተቀየረ መሆኑን ተገንዝበው ነቀፌታቸውን አሰምተዋል::

ሚስተር ዮአኪም ኢያቄም ሐመር መጽሔት ጥር 1990 ዓም ገጽ 24 "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እጅግ በጣም ብዙ ሀብት ያላት ቤተ ክርስቲያን ናት:: ለምሳሌ በሥነ ሥዕል ረገድ የተለየ ሥጦታ አላት:: ነገር ግን አብዛኞዎቹ ምእመናኖች ይህንን ስለማያውቁ የሚጠቀሙበት ሥዕል የአውሮፓውያኑን ሥዕል ነው:: ይህም ከእምነታችሁና ከሥርዓታችሁ ጋር የሚጋጭ ነው::

ቤተ ክርስቲያናችሁን የአውሮፓ ሥዕሎች እያጥለቀለቋት ነው:: ትልልቅ በዓላት ስትሄዱ ገበያ ላይ የምትመለከተው ሥዕል በሙሉ የውጭ ነው:: አንድ ኢትዮጵያዊ ሥዕል አታገኝም" ሲሉ ተናግረዋል:: አበው አባቶቻችን "አይነደው አይቆጨው፤ ወጨፎውን ሽጦ ገዛበት ጥሬጨው"ብለዋል::

በተለይም ምሁራን እባካችሁ በራሳችሁ ታሪክ ኩሩ! በፊደላችሁ ተጠቀሙ! በታሪካችሁ እርኩ፤ የምታውቁትን ታሪክ አስተምሩን:: ምሁራን ብቻ ሳይሆኑ ዛሬማ መነኮሳቱም ጭምር በውጭ ቋንቋ መጠቀም ከጀመሩ ውለው አድረዋል:: አሁንስ እንኳን ውጭ አገር ላለው ትውልድ ሊሆን ቀርቶ አገር ውስጥ ያሉትን ወጣቶች በባህላቸውና በታሪካቸው እንዲኮሩ የሚያስተምራቸው ያለ አይመስለኝም::

አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ ትናትም ዛሬም ነገም የተባለውን መጽሐፍ ስጽፍ የተለያዩ ሰነዶችን ተመልክቼ ነው:: አንድን መጽሐፍ



ከደራሲው ስም ጋር የምጠቅሰው አንዴ ሲሆን ሁለተኛ ያንን መጽሐፍ ከሌላ ምዕራፍ የምጠቅሰው ከሆነ የደራሲውን ስም ጭምር ሳይሆን መጽሐፉን ብቻ ነው::

አንዳንድ ጸሐፊዎች ማዕረጋቸውን ሳይጠቅሱ መጻሕፍት ያሳተሙ አሉ:: ወይም መጽሐፉ ከታተመ በኋላ ማዕረግ አግኝተው ይሆናል:: ስለዚህ እኔ የምጠቅሰው መጽሐፉ በታተመበት ጊዜ ያለውን ስምና ማዕረግ ነው:: መጽሐፉ የታተመበትን ዓ.ም የአሳታሚውን ድርጅት የታተመበትን ቦታ አልጠቅስም:: ምክንያቱም መጽሐፉ ከደራሲው ስም ጋር ከተጠቀሰ ፈልጎ ለማግኘት ችግር የሚያመጣ ስላልመሰለኝ ነው::

ሁሌም ከመጽሐፍ ጥቅስ ከመውሰዴ በፊት መጽሐፉን ከጻፍኩ በኋላ መሥመር እጽፍበታለሁ ለምሳሌ መጽሐፍ ቅዱስ ካልኩኝ እሠምርበታለሁ:: ከገድላት ከአዋልድ መጻሕፍት ላይ ጥቅስ ስወስድ ገጽ አልጠቀስኩም:: ሌላው ገጽ ያልጠቀስኩበት መጽሐፍ የገብረ ሕይወት ባይከዳኝ የአጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ የተባለው ነው:: ዓመተ ምሕረቱን በተመለከተ ጥቅስ እስካልተወሰደ ድረስ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ነው::

በጥሞና እንድትከታተሉልኝ የምፈልገው ነገር ቢኖር "አለ"ወይም "ብለዋል" ወይ"ተብሏል" ስል ትምህርተ ጥቅስ ከፍቼ ከጻፍኩ በኋላ ትምህርተ ጥቅስ እዘጋለሁ "---" በዚህ ዓይነት ምልክት ይሆናል:: አንዳንድ ጠቃሚ ታሪክ የነገሩኝ ግለሰቦች ስማቸውን ጠቅሼ እጽፋለሁ:: አንዳንድ ግለሰቦች ደግሞ የማላምንበትን የነገሩኝ ከሆነ እሳባቸውን ስጠቅስ ስማቸውን አልጠቅስም::

ሌላው ለዚህ መጽሐፍ ዋቢ ሁነው የተጠቀሱት የተለያዩ ጽሑፎችና የነፋስ ድምጽ ራዲዮን ክር፤ካሴቶችና ተውኔት ክሮች፤ብሎም ጥያቄ ያደረኩላቸው ግለሰቦችን ጭምር የያዘ ነው:: ለምሳሌ በራሪ ወረቀት ማለት ከ1-5 ገጽ ያለው ሲሆን ከ1-64 ገጽ ያለው ደግሞ መጣጥፍ ተብሎ ተጽፏል:: ከ65 ገጽ በላይ ከሆነ መጽሐፍ ነው::

የአጤ ቴዎድሮስን መዋዕለ ዜና የጻፉት 3 ደራስያን ናቸው:: ከነዚህም መካከል አንዱ ደብተራ ዘነብ፤ ናቸው:: ጽሑፉ ሙሉ አይደለም:: በ1902 ዓም ጀርመናዊው ሊቀ ጠበብት ሊትማን

ያሳተመው ሲሆን የቴዎድሮስ ታሪክ ደብተራ ዘነበ የንጉሡ ጸሐፊ ትእዛዝ የነበረ የጻፈው ታሪክ ነው ይላል:: ጽሑፉ ሙሉ አይደለም ያልኩበት ምክንያት ከእንግሊዞች ጋር የተፈጠረውንና መጨረሻውን ጠብ ሳይጠቅሱ የተውት በመሆኑ ነው::

ይህ የደብተራ ዘነብ ጽሑፍ በሊቀ ጠበብት ሊትማን የታተመው 35 ገጽ ነው:: እኔ ከዚህ ጽሑፍ ጥቅስ ስጠቅስ ደብተራ ዘነብ የቴዎድሮስ ታሪክ ሊትማን ያሳተመው እያልኩ እጠቅሳለሁ::

ሁለተኛው የአጤ ቴዎድሮስን ታሪክ የጻፉት ስማቸው ያልተጠቀሰው ደራሲ ናቸው:: መጽሐፉ 55 ገጽ ሲሆን ከትውልዳቸው ጀምሮ እስከ ሞታቸው ዘግቧል:: ይህን መጽሐፍ ያሳተሙት ሉዊጅ ሁፌለ ናቸው:: ከዚህ መጽሐፍ ጥቅስ ስወስድ ስማቸው ያልታወቀው የቴዎድሮስን ታሪክ የጻፉት በሉዊጅ ሁፌለ የታተመ እያልኩኝ ጥቅስ እወስዳለሁ:: ስለዚህ አንዴ ሙሉው ስም ከተጠቀሰ በኋላ በአጭሩ ስማቸው ያልታወቀው የቴዎድሮስን ታሪክ የጻፉት በማለት ጥቅስ እወስዳለሁ::

በአንድ መጽሐፍ ውስጥ የብዙ ሰዎች ጽሑፍ ያለበት INSITUTE OF ETHIOPIAN STUDIES kASA AND KASA ከተባለ መጽሐፍ ጥቅስ ስወስድ ቅድሚያ የጸሐፊውን ስም ከጠቀስኩኝ በኋላ ደግሞ KASA AND KASA ብዬ ገጹን ጠቅሼ እጽፋለሁ:: በአማርኛ የተጻፈውን ስጠቅስ በእንግሊዘኛ የተጻፈውን ሳይሆን "ካሳ እና ካሳ"በሚል በአማርኛ ጽፌ ጥቅስ እወስዳለሁ::

ሌላ ደግሞ የአንድ ሰው ስም ሆነ የመጽሔት፤ጋዜጣ፤ ተደጋግሞ ተጠቅሶ ልታገኙ ትችላላችሁ:: ይህ የሆነው በመጽሔት አልያም በጋዜጣ በይቀጥላል የወጣ ጽሑፍ ሲሆን በተለያዩ ወራት መጽሔቱ፤ ጋዜጣ በወጣበት ቀን ተመዝግቦ ጥቅሱ በመጠቀሱ እንዲታወቅ ለማስገንዘብ ነው:: ሌላው ከመጽሔትና ከጋዜጣ ጥቅስ ስወስድ ከአንዳንድ ጋዜጣና መጽሔት ላይ የጻፈው ሰው ያልተጠቀሰ ከሆነ መጽሔቱንና ጋዜጣውን ብቻ ጠቅሼ እጽፋለሁ::

ሁሌም መጽሐፍ ጽፌ ወደ ማተሚያ ቤት ከማስገባቴ በፊት ከአንባብያን የተሰጠኝን አስተያየት እገልጻለሁ:: ለምሳሌ ብዙ ሰዎች "ጥቅስ ማብዛት ስንፍና አልያም ደግሞ ስርቆት ነው" በማለት



በተደጋጋሚ አስተያየታቸውን የሚጽፉልኝ ብዙ ናቸው:: ነገር ግን ከላይ እንደጠቀስኩት በእኔ እምነት ስንፍና አልያም ደግሞ ስርቆት አይደለም:: ክፍል 8 ምዕራፍ 1 ከአንድ ድቪዲ በቀር ምንም አይነት ጥቅስ ሳይገባበት የተጻፈ ምዕራፍ ነው:: ብዙ ደራስያን ይህን አስመስለው ይጽፋሉ:: በእኔ እምነት ይህ ትክክል አይደለም እላለሁ:: እርሱን አንድ ምዕራፍ ስጽፍ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን የታሪክ መጻሕፍትና ጋዜጣዎች ላይ የወሰድኩት መሆኑን እገልጻለሁ::

1 ተክለ ጻድቅ መኩሪያ የግራኝ አህመድ ወረራ
2 ሙራድ ካሚል እንደጻፈው ዮናስ ቦጋለ እንደተረጎመው የፖርቱጋሎች ጀግኖች
3 ዶ/ር ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም
4 ንቃ ጋዜጣ ኅዳር 26 ቀን 1988 ዓም ገጽ 5
5 ገርገብ ጦማር ጋዜጣ መስከረም 4 ቀን 1992 ዓም ገጽ 10 ሌሎችም መጻሕፍት::

አባሪ አንድ አልያም ደግሞ አባሪ ሁለት እያልኩኝ እዘግበዋለሁ:: እናንተም አንባብያን በተሰጠው ቁጥር መሠረት ወደ ፊት ሕዳችሁ የአባሪውን ቁጥር ተመልከቱ:: መጽሐፉን በዚህ መልክ የቻልኩትን ያህል በሰነድ አጥግቤ ጽፌአለሁ:: ለዚህ መጽሐፍ ዋቢ የተጠቀሱ በተለያዩ ሠነድ የተጠራቀመ ሲሆን እያንዳንዱን ዘርዝር ለማድረግ ከተፈለገ እነሆ ከዚህ በታች እዘረዝራቸዋለሁ:: አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ ትናትም ዛሬም ነገም የተባለውን መጽሐፍ ሳዘጋጅ በእኔ አመለካከት ይሆናል በሚል ታሪካቸውን ለሠዓሊዎች እያስረዳኋቸው የተሣሉ ብዙ ሥዕሎች ገብተውበታል::

አንባብያንን አደራ የምለው ነገር ቢኖር እኔ የአጤ ቴዎድሮስ ጠበቃ አይደለሁም:: እኔ አንዳንዴ ጠንከር ያለ ትችት የምወስድባቸው የታሪክ ሠነድ በተጻፈው ላይ እንጂ በግለሰቦች ላይ አለመሆኑን ለአንባብያን ማስገንዘብ እወዳለሁ:: ከማንም ጋር ምንም ዓይነት ጥላቻ የለኝም:: ለምሳሌ አንድ ሰው የጻፈውን መጽሐፍ ሙሉ በሙሉ ለአንድ አንባቢ ጥሩ ላይሆን ይችላል:: ምክንያቱም ፍጡር በመሆኑ ነው:: እኔ ከአንድ መጽሐፍ ለእኔ ይጠቅመኛል የምለው ከአንድ ገጽ እስከ አስር ገጽ ሊሆን ይችላል::

ምንም የተማረ ምሁር ቢሆን ሰው ነውና ሊሳሳት ይችላል:: ስለዚህ ከአንድ መጽሐፍ ላይ ጥሩ የጻፈውን በጥሩ ጥቅስ እወስዳለሁ:: ስህተት የመሰለኝን ደግሞ በሌሎች የታሪክ መጻሕፍት ጋር በማመሳከር ስህተት መሆኑን መተቸቴን አልተውም:: በዚህ ምክንያት ብዙ አስተያየት በአድራሻዬ ይደርሰኛል:: ነገር ግን

ብዙዎቹ ስማቸውን አይጽፉም:: ስማቸውን ጽፈው ከላኩልኝ አንባቢ መካከል አንድ ለናሙና ልጥቀስ::

አቶ ገረመው ጌታነህ "አቶ አማረ የነበሩትን መሪዎች በወቅቱ ታማርራለህ፤ በሌላ ገጽ ላይ ደግሞ ታመሰግናለህ ሁለቱ ሊጣጣምልህ አልቻለም" ሲሉ ጽፈውልኛል:: አቶ ገረመው ጌታነህን ከልብ አመሰግናለሁ:: ለማስረዳት የምፈልገው ነገር ቢኖር አንድ ሰው ሙሉ በሙሉ ፍጹም ባለመሆኑ ይሳሳታል:: በስህተቱ ተችቼ በጥሩ ሥራው ደግሞ አመስግኜ እጽፋለሁ:: ብዙ ሰዎች ግልጽ አይደሉም:: ጥሩ ያልሆነ ጽሑፍ የጻፈ ሰው መሆኑን እያወቁ ደራሲውን ሲያገኙት ጥሩ እንደጻፈ አድርገው ያመሰግኑታል:: ከሌላ ሰው ጋር ሲሆኑ ደግሞ መጥፎ ጽፏል ብለው ያሙታል:: ይህን ድብብቆሽ ልንተወው ይገባል:: እኔ ስህተት መስሎ የታየኝን ነገር ከመንገር አልቆጠብም:: አንባብያንም አትቆጠቡ ሰው ይከበራል እንጂ አይፈራም::

## ምዕራፍ 3

## ፈር አስጨባጭ

ማንኛውም ሰው መጽሐፍ ሊጽፍ ሲነሣ የራሱ የሆነ ዓላማ አለው:: ያም አስቀድሞ ሊጽፍ ከማቀዱ በፊት የሚጻፈው መጽሐፍ ጥቅም ለአገሩና ለትውልዱ ይሆናል ብሎ አስቦበት ነው:: እኔ ይህን "አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ ትናትም ዛሬም ነገም" የተባለውን መጽሐፍ ለመጻፍ የተነሣሁበት በ3 ዓበይት ጉዳዮች ላይ ነው:: እነዚህን 3 መሠረታዊ ጉዳዮች ከዚህ በሚቀጥለው መሥመር እዘረዝራለሁ::

1ኛ "የኢትዮጵያን አንድነት መደፈርና ዳር ደንበር አስጠባቂ ኃይል፤ አለሁ ብሎ የሚጮህ ጀግና ባለመኖሩ አገሪቱ የደረሰባት ጉስቁልና አልበቃ ብሎ ከበደል ላይ በደል ከችግር ላይ ችግር ይሻላል ሲባል እየባሰ ሲመጣ ማየት ከተጀመረ ውሎ አድሯል:: አሁንስ መዋልና ማደር ብቻ ሳይሆን ሰንብቷል ማለት ይቻላል:: በተለይም ኢትዮጵያውያን አንድ እንዳይሆኑና ለአንድነት እንዳይነሡ ከወያኔ ጋር ጎን ለጎን የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚከፋፍሉ ዘመናዊ ምሁራን ናቸው:: በዚህ ሰዓት አገር ብትጠፋ ወንድ እንዳይወጣባት ሆዳም እንዲሆን አድርገውታል::



አማረ አፈለ ብሻው የሁለት ሺህ ዓመታት ውጣ ውረድ በኢትዮጵያ በተባለው መጽሐፍ ገጽ 182" በጭልጋ አውራጃ ውስጥ ለም መሬት በተለይም ደለሎ፤ሽመለጋራ ሽንፋንና ሌሎችን የቋራ የእርሻ መሬት አርሰው የሚበሉት ሱዳኖች ናቸው" በማለት በ1999 ዓም ጽፌ ነበር:: ይህን መጽሐፍ ከጻፍኩ በኋላ ነገሮቹ መልካቸውን እየቀየሩ መምጣትና የኢትዮጵያ ሁኔታ አስጊ ደረጃ ላይ መድረሱን ማየት ስጀምር እየፈራሁ መጣሁ!

2ኛ የኢትዮጵያ አንድነት ሊያንሰራራ የቻለው በአጤ ቴዎድሮስ ጀግንነት ሲሆን እርሳቸው መቅደላ ስኞ ሚያዝያ 6 ቀን 1860 ዓም እጃቸውን ለጠላት ከመስጠት ይልቅ ሞትን መርጠው ሽጉጣቸውን ጠጥተው ሞቱ:: አጽማቸው መቅደላ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አርፎ ነበር:: ነገር ግን ልጃቸው ራስ መሼሻ ቴዎድሮስ አጽማቸውን ከመቅደላ ወደ ማኅበረ ሥላሴ ገዳም በመጋቢት 1871 ዓም አፍልሰውታል::

ዛሬ የኢትዮጵያ አንድነት ተዋርዶ የኢትዮጵያ ሕዝብ በዘር ተለያይቶ ባለበት ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት እያለ ሲነሣ ድምጻዊው፤ሠዓሊውና ደራሲው ሁሉ "ቴዎድሮስ፤አባ ታጠቅ"እያለ በመዘመሩ ወያኔ ቀደም ሲል በምሁሮቹ የሥነ ልቦና ስብራት ለማባል ሲል አጤ ቴዎድሮስን አስመልክቶ ጭራ እየሰነጠቀ ሲያስጽፍ የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይ አንድነት ፈላጊው ዝናቸውን ከፍ አድርጎ ማንሣት ሲጀምር አጽማቸው ያለበትን የማኅበረ ሥላሴን ገዳምና ሌሎችንም ለም ወረዳዎች መሬት ለሱዳን መስጠቱን አስመልክቶ በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የድንበር ኮሚቴ ተመሠረተ::

ውጭ አገር የተመሠረተው የደንበር ኮሚቴው እየተከታተለ ማስረዳት ሲጀምር በውጭ አገር ያሉ የሕዝብ መገናኛ አገልግሎቶች በተለይም የአሜሪካ ድምጽ የአማርኛው ሬዲዮንና የጀርመን ድምጽ ዘጋቢዎች የሞያ ግዴታቸውን ተወጥተዋል:: እኔም በእጄ ከነበረ ሰነድ ጋር በማጋጨት ከላይ የተጠቀሰውን መጽሐፍ ስጽፍ "የአጤ ቴዎድሮስ አጽም የት ይረፍ" የሚል ጥያቄ አቅርቤ ነበር::

ያን ምዕራፍ ትንሽ ጨመርመር አድርጌ ከዚህ መጽሐፍ መጨረሻ ላይ በድጋሜ አውጥቸዋለሁ:: ኢትዮጵያ አገራችን እንድትጠፋ እንጂ

እንድትለማ ብዙ ሀገሮች አይፈልጉም:: ምክንያቱም ትፈራለች፤ ይችን "ትፈራለች" የምትለውን መሥመር ስታነቡ ትስቁ ይሆናል ድሃ በመሆናችን ብላችሁ አስባችሁ ግን በድሃዎቹ በእኛ ጀግንነት ሳይሆን በአባቶቻችን ጀግንነት ኢትዮጵያ ትፈራለች::

ሹመት ሲሻኝ <u>የኤርትራ ሕዝቦች የአንድነት ትግል</u> በተባለው መጣጥፍ ገጽ 16 "አብዛኛዎቹ ምዕራባውያን ኢትዮጵያ በቅኝ ግዛት ሥር ባሉት በጥቁር ሕዝቦች መካከል የፖለቲካና የሞራል መነቃቂያ ምሳሌ ትሆናቸዋለች ብለው ስለሚሰጉ በክፉ ዓይን ይመለከቷታል:: አንዳንዶቹ እንዲያውም ጊዜ ካገኘች እንደ ጃፓን ታይል ይሆናል የሚል ፍራቻ አላቸው:: ይህ ዓይነት አዝማሚያ ስላላቸውም ኢትዮጵያን የሚሸራርፍና ኃይሏን የሚወስን ሁኔታ ቢያዩ ደስ ይላቸዋል" ሲሉ ሊቀ ጠበብት ሹመት ሲሻኝ ጽፈዋል::

ለዚህም በደርግ ዘመን የተጀመረው የመሣሪያ ማምረቻ ተጨናግፎ እንዲቀር ብዙ ሴራ የተደረገበት ምክንያት ኢትዮጵያ ስለምትፈራ ነው:: ይህን ማንም አሊ አይልም:: ስለዚህ ጀግና እንድትወልድ እንደ ቴዎድሮስ ያለ ወንድ ትፈልጋለች ትውልድ አገሬ ኢትዮጵያ::

ደጃዝማች ግርማቸው ተክለ ሐዋርያት <u>አድዋ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 5 "በራስ መኩራት በራስ መተማመን፤የብርታትና የኃይለኝነት ምልክት ሲሆን መነሻ ከሌለው ወይም በሥራ ካልታየ ግን ከከንቱነትና ከግብዝነት ያስገመግማል:: ስለዚህ ሕዝብ በታሪኩ ባባቶቹ (በባህሎቹ) በመኩራትና በመመካት ምሳሌያቸውን ተከትሎ ሙያውን ሲያሳይ ማንነቱን ያስመስክራል" ሲሉ ጽፈዋል::

አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ ማንነታቸውን አስመሰከሩ ጀግና ናቸው:: አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ የፈጸሙት ተግባር ምን ነበር? እኛስ የዛሬው ትውልድ ለአጤ ቴዎድሮስ ምን ልናደርግ እንችላለል? ለምሳሌ ሚያዝያ 6 ቀን 2003 ዓም አጤ ቴዎድሮስ ከሞቱ 143 ዓመት ሆናቸው::

ምንም እንኳ አገር አፍቃሪ መሪ ኑሮ ከዚህ በፊት የነበሩት አባቶቻችን ለአገራቸው የፈጸሙትን ተግባር በሥዕል ድምጽ በቴሌቭዥን በነፋስ ድምጽ ራዲዮን ታሪካቸውን ለተተኪው ትውልድ ማስተማሩ ከወያኔ ባይጠበቅም ነገር ግን አገር ወዳድ የሆኑ



ኢትዮጵያውያን እንዲያነቡት የ143 ዓመት ማስታወሻ እንዲሆን ለማድረግ በማሰብ ነው የተጻፈው::

ፃሮ የተለያዩ ሠነዶችን ሳገላብጥ አንዳንድ ግለሰቦች አጤ ቴዎድሮስን አስመልክቶ የጻፉት ታሪክ መልካም ሁኖ ስላልታየኝ ታሪክ በታሪክነቱ መጻፍ እንዳለበት ለማሳሰብ ነው:: በተለይ በቅድስት ማርያም ስም <u>ታምረ ማርያም</u> ላይ የተጻፈውን ስርዋጽ ሳነብ ያሳሰበኝ የኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አዋልድ መጻሕፍትን እንድንጠራጠር ያደረጉ በመሆኑ:: የነዚህ አንዳንድ ግለሰቦች የጻፉት ጽሑፍ ለወደፊቱ የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድ ሊያደርግ የማይችል በመሆኑ ለማሳሰብ እንጂ የአጤ ቴዎድሮስን ታሪክ ዛሬ ያለው የኢትዮጵያ ትውልድ ጠፍቶታል በማለት አይደለም::

እኔም ብዙ አዲስ ነገር ለማውጣት አስቤ ሳይሆን ትውልዱን ለማሳሰብ ነው:: ሌላው የኢትዮጵያን አንድነት አፈቅራለሁ!የሕዝቡን አንድነት እመሰክራለሁ ለሚለው ትውልድ የገጠመው ችግር ከፍተኛ ነው:: ከላይ እንደጠቀስኩት የአጤ ቴዎድሮስ አጽም ያረፈበት መነበረ ሥላሴ ገዳም ለሱዳን ሊሰጥ የተወሰነበት ከሆነ ስማቸውን እንሥተን እንዳንኮራ ለማድረግ የተጀመረ በመሆኑ ምን ይደረግ? ብዬ ለትውልዱ አደራ ለማለት ነው::

አዲስ ነገር <u>ጋዜጣ</u> ቅዳሜ መጋቢት 13 ቀን 2000 ዓም ገጽ 17 "ፕሮፌሰር ሮቢንሰን ስለ አጤ ቴዎድሮስ የሚሉት ቃል በቃል ሲነበብ የሚከተለውን ይመስላል:: የዘመናዊቷ ኢትዮጵያ አባት አጤ ቴዎድሮስ ናቸው:: የኢትዮጵያ አባትነታቸውን ስለ ግዛት አንድነቷ ጥንካሬ እና ተራማጅነት ያላቸውን ራእይ በግልጽ አስታውቀዋል::"

"በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያው ንጉሠ ነገሥት እና የዘመናዊት ኢትዮጵያ ፈር ቀዳጅ ናቸው" ሲሉ በጀርመን ሬዲዮ የተናገሩትን ጋዜጣው ጽፏል:: የዚህን መጽሐፍ ርእስ "አጤ ቴዎድሮስ የአንድነት አባት" የሚል ለማድረግ ፈልጌ ነበር::

Dr, Getachew Mekasha, <u>Ethiopian Review</u>/April 1991 page 18 Theodros is one of the architcts of the modern Ethiopian nation ሲሉ ጽፈዋል:: ሚያዝያ 1983 ዓም ከእርሳቸው አባባል ጋር ሊቅ (ዶ/ር) ስብሐት መርስዔ ኀዘን ይስማማሉ::

ሊቅ ዶ/ር ስብሐት መርስዔ ኀዘን "ኢትዮጵያ ከአጤ ቴዎድሮስ በፊት የነበረችና የሰለጠነች አገር ነበረች። ከ18ኛው ክፍለ ዘመን እስከ 19ኛው ግማሽ በጣም ደክማ ነበር። በዚህ ወቅት አጤ ቴዎድሮስ ተነሥተው እንደነበረች ለማድረግ ጣሩ እንጂ አዲስ አገር አልመሰረቱም።"

"የአንድነት አባት የሚባለው ለምሳሌ ጆርጅ ዋሽንግተን ሲሆን ሌሎች የእርሱን ፈለግ ተከትለው እነሆ ዛሬ አሜሪካ ከደረሰችበት ሥልጣኔ አደረሷት። በእኔ እምነት አጤ ቴዎድሮስ አንድ ለማድረግ ጥረት አደረጉ የጥረታቸው ውጤት ራሳቸውን በራሳቸው ለአገራቸው ክብር ሲሉ ሠዉተዋል። ስለዚህ የመጽሐፉ ስም ፥አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ፥ መባል ይገበዋል" አሉኝ። እነሆ የእርሳቸውን ምክር ተቀብዬ አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ የሚል ስም ሰጥቸው ነበር።

ከላይ እንደጠቀስኩት መጽሐፉን ቅድሚያ ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው እና አቶ ዘርፉ ታከለ ተመልክተዉት ነበር። ነገር ግን ስሙን አስመልክቶ ምክር አልለገሱም። ሻለቃ ግርማ ይልማ፤ እንዲመለከቱት መጽሐፉን ሰጥቼአቸው ካነበቡ በኋላ ስልክ ደውለው በትሕትና "አቶ አማረ የመጽሐፉ ስም ግን ከመጽሐፉ ጋር አብሮ አይሄድም። የዶ/ር ስብሐትን ስያሜ እንዳለ ይዠው ታሪኩን ሳነበው ግን አልገልጽልኝ አለኝና የመጽሐፉ ስም ተንጠልጥሎ ቀረ። ስለዚህ ብትጨምርበት ምን ይመስልሃል" አሉኝ። እኔም "ሻለቃ እርስዎ ይሰይሙት አልኳቸውና ስልኬን ዘጋሁ።

በሌላው ቀን ስልክ ደወልኩና "ሻለቃ የመጽሐፉን ስም አወጡለት ወይ?" በሚል መልእክት ከድምጽ መቀበያው ላይ ተውኩላቸው። እርሳቸው ስልክ ሲመቱ ሥራ ስለነበርኩኝ "አቶ አማረ ከተስማማህበት አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ ትናንትም ዛሬም ነገም ቢባል ጥሩ ይመስለኛል መልእክቱን ካዳመጥከው በኋላ ደውልልኝ" ብለው ትተውልኝ አገኘሁ። ከሥራ ስወጣ ስልኬ መልእክት ተቀባዩ የሻለቃን ድምጽ አሰማኝ። እኔም ወዲያው ስልክ መታሁና "እርስዎ ባወጡት ስም እስማማለሁ አልኳቸው።

አንባብያን አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ ትናትም ዛሬም ነገም የተባለውን መጽሐፍ ስታነቡ የተወለዱት በ1811 ዓም የነገሡት



በ1845 ዓም የሞቱት በ1860 ዓም መሆኑን ብቻ ሳይሆን እርሳቸው ከልጅነት እስከ ጎልማሳነት ብሎም ለአገር እድገት የታገሉለት የአገራቸውን ታሪክ በመረዳት አንቱ ከተባሉት አገሮች ጋር እቻ ለእቻ ለማስኬድ የነበራቸውን ራእይ የዛሬው ትውልድ አመለካከት መረዳት አለበት። ይህን መጽሐፍ ስታነቡ ልታዝኑም ልትበሳጩም ልትቆጩም ትችላላችሁ። ለዚህም ነው ታሪክ መማር እንዳለብን አባቶቻችን የሚያሳስቡን።

ልዑል ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ <u>ካየሁት ከማስታውሰው</u> በተባለው መጽሐፋቸው መቅድም "ንባብ የጥንቱን የተጻፈ ታሪክ ሁሉ ማንበብ ያቻላል። ታሪኩንም በማንበብ የጥንቱን ሥራውን የሰውንም ኑሮ የነገሩንም አኳኋን ሁሉ እንደምን እንደነበረ የሩቁን ብዙ ዘመን የሆነውን የቅርብ ጊዜ አስመስሎ ያሳያል። እንደዚሁም በየጊዜው የተጻፈው ታሪክ ሁሉ የሰው አእምሮ የዕውቀት ደረጃ በምን አኳኋን ከፍ ከፍ እያለ እየተጓዘ እንደመጣ ያስረዳል። ይኸውም ታላቅ ትምህርት ሰጭ ነው" ሲሉ ጽፈዋል። ቅድሚያ ከኢትዮጵያ ደራስያን መካከል የታሪክ መጻሕፍትን አገላብጠው የጻፉ አለቃ ታዩ ወልደ ማርያም በ1920 ዓም ይመስለኛል።

<u>የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 6 "ታሪክ መማርና ማወቅ ለብዙ ነገር ይጠቅማል። መጀመሪያ በድንቁርና የታወረ ዓይንን ይከፍታል። ሁለተኛ ሰው የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነት የፍጥረቱንም ብዛትና የልዩ ልዩ ወገንንም ዓይነት የዓለምንም ታላቅነትና ስፋት ያይበታል።"

"ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ከተቆጠረ እስከ ዚህ ዘመን የሆነውን ሁሉ ነገር ሲማር ጥንት እንደ ተፈጠረ አስቀድሞ እንደ ነበረ ሁኖ ያውቃል። በዓለም ያሉን ልዩ ልዩ ሕዝብ አገራቸውና ጠባያቸውን ያምላኩቻቸውን የመንግሥታቸውን ሥርዓትና አኗኗራቸውን በታሪክ ሲመለከት ሲመረምር ሲያስተውልም በቤቱ ተቀምጦ ዓለምን ሁሉ ዞሮ መርምሮ እንዳየ ሰው ይሆናል ማለት ነው" ሲሉ ጽፈዋል።

ግብረ ሕይወት ባይከዳኝ <u>አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ</u> በተባለው መጽሐፋቸው "ታሪክን መማር ለሁሉ ሰው ይበጃል። ለቤተ መንግሥት መኮንን ግን የግድ ያስፈልጋል። የድሮ ሰዎች ስሕተትንና ዘኅነትን አይቶ ለመንግሥቱ ላገሩ የሚበጀውን ነገር ያውቅ ዘንድ

የታሪክ ትምህርት ግን የሚጠቅም የውነተኛ ታሪክ ትምህርት ሲሆን ነው:: እውነተኛም ታሪክ ለመጻፍ ቀላል ነገር አይደለም" ሲሉ የታሪክን ጥቅም ገልጸው ጽፈዋል::

አጤ ቴዎድሮስ የተከፋፈለች ኢትዮጵያን አንድ ለማድረግ መሠረቱን ጥለው አልፈዋል:: ከእርሳቸው በኋላ የተነሡ ነገሥታትና ርእሰ ብሔሮች እንዲሁ አጠናክረዋል:: በተለይም ኢትዮጵያ ከ1983 ዓም ወዲህ ወርዷ እየጠበበ ቁመቷ እያጠረ በመምጣቱ ልጆችዋ ለሥልጣን ብለው ሕዝብን ከሕዝብ ለያይተው ልክ ዘመነ መሳፍንቱ ያደርገው እንደነበረው ሕዝቡን በመከፋፈል ላይ ናቸው:: ይህን መጽሐፍ የጻፍኩት ምናልባት ሱሪ የታጠቀ ወንድ እንዳለ እምቢ ለኢትዮጵያ ለአንድነት እታገላለሁ የሚል ካለ ሞራል ለመስጠት ጭምር ነው:: ግን እኮ ዛሬ ወንድ አለ?

ይህ መጽሐፍ በ12ክፍል በ79 ምዕራፍ የተከፈለ ሲሆን አንዳንድ ምዕራፎች ረዘም ያሉ ናቸው:: በያንዳንዱ ምዕራፍ ዋቢ መጻሕፍት ማለትም ሰነድ ከሌለኝ ምዕራፉን ለመጻፍ አልጀምረውም:: ይህ መጽሐፍ ሊታተም የታሰበው ለ140 ዓመት መታሰቢያ እንዲሆናቸው ተብሎ ታስቦ ነበር:: ነገር ግን የኢትዮጵያ መሬት ለሱዳን ወያኔ ሊሰጠው የተነሣ በመሆኑ ድንበሩን በሚመለከት ከጋንቤላ እስከ ሁመራ የተባለውን መጽሐፍ ቀድሜ ለማሳተም ተነሣሁ::

ወዲያው ደግሞ በቤተ ክርስቲያን አባቶች ድብድብ በመከሠቱ እንዲሁ በአባ ጳውሎስና በጳጳሳት ምክንያት በቤተ ክርስቲያን ላይ የተነሣው እሳት የተባለውን መጽሐፍ ጽፌ ለማሳተም ጉንብስ ቀና ስል አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ ትናትም ዛሬም ነገም የተባለው መጽሐፍ 3 ዓመት ፊጀበት እንጂ ሊታተም ተዘጋጅቶ የነበረው ለ140 ዓመታቸው መታሰቢያ ነበር:: "ለሁሉም ጊዜ አለው"እንዳለ ሰሎሞን ጊዜው ሲፈቅድ እነሆ በ2003 ዓም ለመታተም በቅቷል::

ለአንባብያን የማመለክተው ነገር ቢኖር በዚህ መጽሐፍ ታላላቅ ሰዎች ተነቅፈው ትመለከቱ ይሆናል:: ነገር ግን እኔ የነቀፍኩት ብዕራቸውን እንጂ ታላላቆችን ምሁራን ለማዋረድ አለመሆኑን ተረዱልኝ:: በእኛ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ያለብን ችግር እንኳን የተነቀፈው ግለሰብ ቀርቶ የተነቀፈው ግለሰብ ከተወለደበት ክፍለ ሀገር የመጡት ሁሉም አኩራፊ የሆኑበት ዘመን መሆኑ ጠፍቶኝ አይደለም::



ታዲያ አባቶቻችን "ሕልም ተፈርቶ እንቅልፍ ሳይተኛ አይታደርም" ያሉት መሠረት እኔም አኩራፊው መብዛቱን ባውቅም በምችለው መጠን የግለሰቦችን ገጸ ባሕርይ ሳይሆን በጽሑፋቸው ላይ ብቻ ተንተኜ መተቸቱን ደፍሬ ገብቼበታለሁና አልፈራም::

ከዚህ በፊት በጉግግ መጽሔትም ሆነ በተለያዩ መጻሕፍቶቼ ላይ "እገሌ ዘመዴ ነው?እገሌ የአገሬ ልጅ ነው!ለምን ተነቀፈ? ተብሎ ብዙ ወቀሳ ደርሶብኛል:: በእኔ ላይ ጥርሳችሁን አትንከሱ! ግለሰቦችን ሳይሆን የምተቸው ብራዕቻቸውን መሆኑን ተገንዘቡልኝ::

አንባብያን ከዚህ በላይ እንደጠቀስኩት መንደርደሪያዬ መብዛቱን ባውቅም ቅሉ የእኔን እምነት እንድትረዱልኝ ለመግለጽ የምፈልገው ከዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱትን የታሪክ መጻሕፍትን በተቻለ መጠን ተተኪው ትውልድ የራሴ ብሎ እንዲይዘው ለማድረግ ብዙ ያደከመኝ ቢሆንም ከላይ በጠቀስኳቸው ወገኖቼ ትብብር ይህ መጽሐፍ ውበት ኑሮት ለንባብ በቅቷል::

አንባብያንም ከዚህ መጽሐፍ ትምህርት እንደምትቀስሙ ተስፋ አደርጋለሁ:: የጎደለውን እያሟላችሁ የተጣመመውን እያቃናችሁ አንብቡ:: የፊደል ግድፈት የቃላት ጉልድፍነት ሊገኝ ይችላል:: ሆን ተብሎ የተደረገ ሳይሆን የሥራው ጸባይ  መሆኑን እንድትገነዘቡልኝ ከአደራ ጋር አሳስባለሁ::

ፍሥሐ ይሁን መጽሐፈ ቡዳ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 252
"መጽሐፍን ለመጻፍ አንድ ዓመት ተኩል
በጣም ያደክማል ሥራው ቀላል አይደል
ተዘጋጅቶ ሲያልቅ ይመስላል ቀላል
መጽሐፉ ተጽፎ ከፍጻሜ ሲደርስ
ቀለሙ ድጉስቱ ትእግሥት የሚያስጨርስ::" ሲሉ ጽፈዋል::

መልካም ንባብ!አማረ አፈለ ብሻው!

# ምዕራፍ 4

## መግቢያ

### ሻለቃ ግርማ ይልማ

የአቶ አማረ አፈለ ብሻው አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ ትናንትም ዛሬም ነገም የተባለውን አዲስ መጽሐፍ በልዩ የባለቤትነት ስሜት፤ አገራዊ ኩራትና የማንነት አኩሪ ትዝታ አነበብኩት። ደራሲው ስለአጤ ቴዎድሮስ የተጻፉና በቃል የተነገሩ የኢትዮጵያና የውጭ የታሪክ ሥራዎችን በብዛት የመጽሐፉ አካል በማድረግ የመረጡት የአቀራረብ ዘዴ ይበል የሚያሰኝ ነው። እጅግ በጣም ብዙ የሆኑትን ስለአጤ ቴዎድሮስ የተጻፉትን የታሪክ ሰነዶች ለማንበብ በቂ ጊዜ ለሌላቸው የአቶ አማረ አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ ትናንትም ዛሬም ነገም ምጥን ምግብ ነው።

ደራሲው ይሄንን መጽሐፍ ለማቅረብ ያደረጉትን ጥረት ከራሳቸው እንስማ“ በኢትዮጵያውያን የተጻፉትን የኢትዮጵያን ታሪክ በክፉም በደጉም የሚያነሡትን ደግሜ ደጋግሜ አነበብኩ። እራሴን አንቱ ለማሰኘት ሳይሆን እግዚአብሔር በሚያውቀው ከ1000 በላይ መጻሕፍትን፤ከ200 የሚበልጡ መጽሔቶችንና ጋዜጦችን፤የሥዕል ድምፅ ቪዲዮችንና ካሴቶችን አጠራቅሜ ሳነብና ስመለከት ያች ጎስቋላ የአጤ ቴዎድሮስና የእኛ አገር ትዝ ትለኛለች፤ ስለአገሬ ጠዋት ማታ አስባለሁ”።

የእናታቸውንና የፍቅረኛቸውን ደብዳቤ ለማንበብ ጊዜ የላቸውም እየተባልን በምንታማ ዜጎች መካከል የአቶ አማረ የመጽሐፍት ፍቅርና የንባብ ባህል በአርአያነት የሚጠቀስ ነው። በጥቂት ጊዜ ትውውቃችን ከሰበሰቧቸው እጅግ ብዙ መጻሕፍት ጥቂቱን እንዳነብ እድል ስለሰጡኝ ባለውለታዬ ናቸው።

በአጤ ቴዎድሮስ ጀግንነት፤አገር ወዳድነት አትንኩኝ ባይነት አርቆ አሳቢነትና እምቢ ለኢትዮጵያ ባይነት አድናቆትና ፍቅር



የተለከፍኩት ገና ከልጅነቴ ጀምሮ ነው። በጉልምስና እና በአዋቂነት ዘመኔም የዕለት ተዕለት ሕዝባዊና አገራዊ ተግባሮች ምርኩዜና አርአያዬ ነበሩ። ከብዙ ገጠመኞቼ አንድ ምሳሌ ብቻ እጠቅሳለሁ።

የኢትዮጵያ የማስታወቂያና መርሃ ብሔር ምኒስትር በነበርኩበት ወቅት የቀድሞዋ የሶቪት ኅብረት አምባሳደር በኢትዮጵያ በቀጠሮ ቢሮዬ መጡ። አመጣጣቸው በሀቀኝነቱ በታማኝነቱና በሞያው የማከብረውንና የምወደውን በጊዜው የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት መምሪያ ኃላፊ የነበረውን አቶ ኃይለ ማርያም ጎሹን ለመክሰስ ነበር። የትሬታው መንሥኤ ታስ የሚባለው የቀድሞው የሶቪየት ኅብረት የዜና ወኪል ያስተላለፈውን እንዳለ የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ሁኔሁነት ለሌሎች እንዲያሠራጭ የሚጠይቅ ነበር። የመምሪያ ኃላፊየን ውሳኔ ደግፌ በትሕትና መመሪያ የምንቀበለው ከኢትዮጵያ መንግሥት ብቻ መሆኑን አስረዳሁት።

ፊቱ ተለዋውጦ ቂምና ቅሬታ አርግዞ ከቢሮዬ ወጣ። ከዕለታት በአንዱ ቀን ከቀድሞው የኢትዮጵያ ፕሬዜዳንት ከሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ጋር በጽሕፈት ቤታቸው ስለሌላ የሀገር ጉዳይ ተወያይተን ስንጨርስ “የቀድሞው የሶቪየት ኅብረት አምባሳደር በኢትዮጵያ ደፋርና ጀብደኛ ነህ ይልሃል ምን አደረገክዋል?” ሲሉ ጠየቁኝ።

የታስ የዜና አገልግሎት ያገኘውን ዜና ምንም ለውጥ ሳይደረግ የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት እንዳለ ለሌሎች እንዲያስተላልፍ ያቀረበውን ጥያቄ አሻፈረኝ ከማለት ሌላ በግል መልካም ግንኙነት እንደነበረን አስረዳሁ። የቀድሞው ፕሬዜዳንት ለቅጽበት ጸጥ አሉ። በመንፈስ ርቀው ሄዱ። በሕዝብና በሀገር ጉዳይ እምቢ አሻፈረኝ ሲባል የአጤ ቴዎድሮስ ውርስ በውስጣቸው እንደሚሠራ ተሰማኝ።

አጤ ቴዎድሮስ ጀግናቸውና በስሜትና በሀሳብ አራአያቸው እንደሆኑ አውቃለሁ። የቀድሞው የኢትዮጵያ ፕሬዜዳንትም የአጤ ቴዎድሮስን ጎራዴ በአየር እየቀዘፉ የሕዝብና የአገር ክብር ከሚደፈር የአጤ ቴዎድሮስን ጽዋ እንደሚቀምሱ ለሕዝብ በመገናኛ ብዙኃን ቃል እንደገቡ ትዝ አለኝ። የቁርጥ ቀን ሲመጣ በኢትዮጲያ ብሔራዊ ሸንጎ የመጨረሻና የስንብት አስቸኳይ ልዩ ጉባኤ አንድ የሸንጎ አባል የነበሩ የሃይማኖት አባት ይህንኑ ነበር ያስታወሱአቸው።

“የቴዎድሮስን ጽዋ ከመጠጣት በስተቀር ሌላ አማራጭ የለዎትም::” ፈታኙ ለት ሲመጣ ግን የቀድሞው የኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት አድናቂዎች፤አክባሪዎችና ደጋፊዎች፣ በእጅጉ ተሸማቀቅን:: ሕዝብና አገር ብለን በእውነት ለተነሳን ኢትዮጵያውያን አጤ ቴዎድሮስ ትናትም፣ ዛሬም፣ ነገም የአጥቢያ ኮከባችን ናቸው::

የሕዝብና የአገር ክብር እንዳይደፈር አጤ ቴዎድሮስ ስለወሰዷቸው ቅድመ እርምጃዎች በልጅነቴ የገበየሁት የታሪክ ትምህርት ሁልጊዜም መንፈሴን ያሞቀዋል:: ቀላል ግን የሕይወት ዘመን ትዝታ የሚጭረውን ምሳሌ እጠቅሳለሁ:: “ስንቱን ክርስቲያን ያልሆኑ አገሮችን አልፋችሁ ከእናንተ በፊት ክርስትናን የተቀበለ ሕዝብ ምን አዲስ ነገር ታስተምራላችሁ? ንሳ ዓለሜ እዚያው ጀልባቸው ድረስ ሸኝልኝ የቅድስት አገሬን ትቢያ ይዘው ከኢትዮጵያ እንዳይወጡ መጫሚያቸውን በሚገባ አራግፍልኝ”:: አጤ ቴዎድሮስ ለመላው ሕዝብና አገር ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያ ትቢያ የሚሳሱ ንጉሠ ነገሥት ነበሩ::

የአጤ ቴዎድሮስን ዓላማና እርቆ አሳቢነት ለመረዳት በንግሥ በዓላቸው ለሕዝብ ያደረጉትን ንግግር በጥሞና ማጤን ያስፈልጋል:: ንግግራቸውን በአጭሩ እጠቅሳለሁ:: “..የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!አንተ ለአቋቋምከው መንግሥትና ለአነገሥከው ንጉሥ ተገቢውን ግብር እንድትከፍል ሕግ ይወስንብሃል:: ይህ ያቋቋምከው መንግሥት አንተንና ኢትዮጵያን እንዲያገለግልና እንዲጠብቅ ለመለመልከው ነፍጠኛ (ወታደር) ስንቅና ቀለቡን ሳያጓድል እንዲሰፍርለት:: ከዚያም ሌላ መተዳደሪያ የሆነ አበል እንዲሰጠው እንጂ እንዳለፈው የመሳፍንት ጭፍራ ዘረፋና ተጽእኖ እንዳያደርግብህ ያደርጋል::”

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!ከአሁን በፊት ስትገድል ስትቀማ፤ቤት ስታቃጥል፤በአርአያ ሥላሴ የተፈጠሩትን እህቶችህንና ወንድሞችህን ባርያ አድርገህ ስትሸጥና ስትገዛ የነበርክ ሁሉ ከአሁን በፊት ስለፈጸምከው ድርጊት ምሕረት ተደርጎለሃል:: ወደቤትህና ወደ ሀገርህ በሰላም ተመልሰህ በግብርናህና በእጅ ሞያህ ተሰማርተህ እንድትኖር ያለፈውን ወንጀልህን ሳላይ የሚመጣውን በማስተዋል ሙሉ ምሕረት ተደርጎለሃል::



የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! ይህ አዋጅ ከተነገረህና እግዚአብሔር ያነገሠው ንጉሠነገሥትህ ቴዎድሮስ ከነገሠበት ጊዜ ጀምሮ ወደቤትህ ተመለስ:: በሽፍትነት ሁነህ የምትቀማና ወንድምህን አድብተህ የምትገድል፤ባሪያ ብለህ ሰውን የሸጥክና የገዛህ እንደ አውሬ ታድነህ ተይዘህ በአደባባይ እጅህና እግርህ ፈጽሞ እንዲቆረጥና ርኅሩኄ እንደማይደረግልህ እወቅ:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!ትናንትናና ከትናንትና ወዲህ ባሪያ ብቻ፣ ሳይሆን ለሥልጣንና ለሹመት ሲባል ሴት ልጅህን ሸጠሃል:: አንተም አንድ ስትሆን ሁለት ሴት ይዘሃል:: ከእንግዲህ ግን ይህ ቃል ተስተካክሎ በሕግ እስኪጸድቅና እስኪታወጅልህ ድረስ እንድታስብበትና እንድትመርጥ ቀን ሰጥቼሃለሁ::

እውቁ የኢትዮጵያ የታሪክ ምሁር ዶር መርዕድ ወልደ አረጋይ ካሳ እና ካሳ በተባለው መጽሐፍ “የአጤ ቴዎድሮስ ዓላማዎች ከየት መነጩ?” በሚል ርእስ ያቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፍ የአጤ ቴዎድሮስን ማንነትና ባሕርያት ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ስለሚገልጽ በዚህ የመግቢያ ጽሑፍ በሰፊው መጥቀስ ተገቢ ሆኖ አግኝቸዋለሁ::

አጤ ቴዎድሮስን ከልጅነታቸው ጀምሮ በሰዎች ተወዳጅነትን ወይም መጠላትን ካፈሩላቸው ጠባዮች መካከል ሀቀኝነታቸውና ታማኝነታቸው ነበሩ:: በረጅሙ የኢትዮጵያ ታሪክ ሂደት ኢትዮጵያውያን እውነት በመናገራቸውና በቃላቸው ጽኑ በመሆናቸው በጎረቤትና በሩቅ ሕዝቦች ታውቀዋል::

ከ16ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ግን እነዚህ ጠባዮች ለብዙ ኢትዮጵያውያን እንግዶች እየሆኑ መጥተዋል:: በግራኝ ወረራ አብዛኛው ሰው ጉልቱንና ሕይወቱን እንዳያጣ ፈርቶ ንጉሡን ከድቷል:: ሃይማኖቱን ክዷል:: ከግራኝ ወረራ በኋላም ሰላምና የመንፈስ ዕረፍት የሚያሳጡ ሁኔታዎች በመፈራረቅ በመነሣታቸው የአድር ባይነትና የምቀኝነት ጠባዎች እየጎሉ ሄዱ::

ዘፊት ኢትዮጵያውያን በሀቀኝነታቸው የታወቁትን ያህል ከዚህ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በወላዋይነታቸውና አጠራጣሪነታቸው አጉል ዝናን አተረፉ::ይህን የጠባይ ለውጡን ያስመጡ የፖለቲካ የዓለመረጋጋትና የኑሮ አስተማማኝ አለመሆን ሲሆኑ አጤ ቴዎድሮስ እነዚህን ገና ሳያሸሽሉ የአስተያየትን ለውጥ ማምጣትን አስቀደሙ::

አጤ ቴዎድሮስ ገና ሽፍታ በነበሩበት ጊዜ የአገኙትን ሁሉ ተካፍለው ለመብላት ከሌሎች ሽፍቶች ጋር ተማምለው ነበርና እነዚህ ሽፍቶች በአንድ ወቅት ቃል ኪዳናቸውን አፍርሰው አንድ በሬ አርደው ብቻቸውን ሲበሉ "እናንተ አሰተኞች"ብለው እንደወጉአቸው ዘነብ ይናገራሉ። በሌላ ጊዜ ደግሞ ሁለት ሰዎች ተካሰው ከፊታቸው ቀረቡ፤አንዱ ለሌላው አንድ ፈረስ ሰጥቶት ነበርና ውለታውን እንዲመልስ ቢያስታውሰው ተቀባይ ለመካድ አሰበ ግን የካሳን ፊት ፈርቶ አመነ።

ዘነብ ታሪኩን እንዲህ ብለው ይዘግቡታል። "ደጃዝማች ካሳም እግዚአብሔርን እንደፈራ ባዩ ጊዜ ስለእውነቱ እኔ እከፍልልሃለሁ አሉት። ለከሳሹ አስር ብር አንድ ፈረስና አንድ በቅሎ ሰጡት። እውነትን ሰው ሁሉ እንዲማር ብለው በፈጸሙት መልካም ተግባር በአደባባይ የነበረው ሰው እጅግ ደስ አለው።"

ቴዊሎስ ቫልድሜር የሚባል ፕሮቴስታንት ሚሲዮናዊ የእጅ ሥራ እውቀት ስለነበረው አዱሪ ትምህርት ቤት ከፍቶ ጋፋቶችንና ፈላሻዎችን በማስተማሩና በሁዋላም የወዳጃቸውን የእንግሊዛዊው የሊቀመኳስ ዮሐንስ ቤልን ልጅ በማግባቱ አጤ ቴዎድሮስ ይወዱት ነበር። አጤ ቴዎድሮስ ሀቀኝነት ለማስለመድና ቅጥፈትን ለማስቀረት ብለው ካደረጉዋቸው ነገሮች እርሱም አንዳንዶቹን ይናገራሉ። "አንድ ቀን አንድ ሰው ሀያ ብር ወድቆ አግኝቶ ባለቤቱን ለማወቅ ባለመቻሉ ደጅ ጠንቶ ከሩቅ (አቤት! አቤት)ብሎ ገንዘቡን ለአጤ ቴዎድሮስ ሰጣቸው። እሳቸውም ሰውየውን በአደባባይ አመስግነው ባለቤቱ እስኪገኝ ድረስ የአንተ ይሁን ብለው ብሩን መረቁለት ሌላ ሃያ ብር ጨምረው አሰናበቱት።

ይህንን ያየ ጮሌ በሌላ ጊዜ እንዲሁ "(አቤት!አቤት!)ብሎ አርባ ብር ወድቆ ማግኘቱን ነገራቸው። እሳቸውም ሁኔታውን አስተውለው በጅሮንዳቸው አርባውን ብር እንዲረከብ ካደረጉ በኋላ አሰናበቱት። ታማኝነት ከሀቀኝነት የሚመነጭ ሲሆን አንዱ ጠባይ ካለሀ ሁለተኛው በሰው ውስጥ አይገኝም። አጤ ቴዎድሮስ ከልጅነታቸው ጊዜ ጀምሮ ሀቀኛ እነደመሆናቸው ለታማኝነታቸውም ከብዙዎቹ ታሪኮቻቸው ጥቂቶቹን ብቻ እናወሳለን።



ገና ለመጀመሪያ ጊዜ ሽፍታ እንደሆኑ ከጥቂቶች ተከታዮቻቸው ጋር ሁነው አንዷን መንደር ሲዘርፉ ሁለቱ በጣም ቆስሉና ወደቁ። የተቀረው ታሪክ በዓይን ምስክሩ በዘነብ ሲነገር ያምራል። "ከወደቁበትም አንዱ እርስዎ ተሸክመው አንዱን አሽከርዎችዎ አነሡት። ካሳም እግርዎ በክረምት እንደሚሄድ ሰው ብዙ ጭቃም አነሣ። የተወጋው ሰው ደም በድግዎ እየወረደ ሰውነትዎን አጠመቅዎ። የተወጉት ሁለቱም ከሰፈር ገብተው ሞቱ።"

"ካሳ ለወዳጆቻቸው ምን ያህል ታማኝ እንደነበሩ አንድ ሌላ ታሪክ በዘነብ እናገኛለን።" ከትኩሪርና ከግንጃር ሻንቅሎች ወዳጆቻቸውና የአባታቸውም ገባሮች ነበሩና አብረዋቸው ሳሉ ከደጋው ሊዘርፉና ሊፈነግሉ አገዎች መጡ። ካሳ አገዎቹን ወግተው ከማረኩ በኋላ ለተኩሪርዎች አለቃ እንድሪስ መቶ አገው መርጠው ሰጡት። አንተን ሊገዛህ ነበርና ግዛው" አሉት።

አጤ ቴዎድሮስ ለታማኝነት ሰፊ አስተያየት ነበራቸው። አባት ለልጁ በተፈጥሮው አሳፊነት እንደተሰጠው እሳቸውም እግዚአብሔር መርጦ እንዳነገሣቸው ከማመናቸው የተነሣ የሕዝባቸው ታማኝ አገልጋይ ለመሆን ግዴታ እንዳለባቸው ተቀበሉ። ዘነብ ደጋግመው እንዳሳዩትና በሌሎችም ምንጮች እንደተደገፈው አጤ ቴዎድሮስ በመጀመሪያ ያሳዩአቸው የነበሩት ባሕርዮች በተለይም ደግነታቸው፣ ርሕራኄያቸውና ይቅር ባይነታቸው፣ለሕዝባቸው ከነበራቸው ታማኝነት አገልጋይነትና አባታዊ ኃላፊነት የፈለቁ ነበሩ።

አጤ ቴዎድሮስ ለድሆችና ለአቅመቢሶች ተጨናቂ እንደነበሩ ቫልድሜር አንድ ልብ የሚነካ ምሳሌ ይነግረናል። አጤ ቴዎድሮስ በመንገድ ሲያልፉ አንዲት ችግረኛ ባልቴት ወድቃ ሲያዩ ከፈረሳቸው ወርደው የለበሱትን ሸማ አንሥተው ደረቡላት። ቫልድሜር ያለውን ብር እንዲያበድራቸው ጠየቁትና የነበረውን አምስት ብር ተቀብለው ሰጡአት። ለቫልድሜርም አምስቱን ብር መቶ ብር አድርገው መለሱለት።

አጤ ቴዎድሮስን ትልቅ ብስጭትና የጠባይ ለውጥ ያደረሰባቸውና እንዲሁም ሩሕሩኅና መሐሪ የነበሩትን ያህል እንዲጨክኑ ያደረጋቸው ባመኑአቸውና ያላማቸው ደጋፊ መስለው በፈጸሙባቸው ክህደት መሆኑ አይጠረጠርም።

አንድ ግራዝማች ዓለሜ የሚባል ባለሟላቸውን በጣም ስለሚያምኑት መቅደላ በነበረው ግምጃቤታቸው ጠባቂ አድርገውት ነበር:: ይህ በአጤ ቴዎድሮስ እሻራለሁ፣እታሰራለሁ፣ ወይም እገደላለሁ የማለት ፍርሃት ሊኖረው የማይችል ዓለሜ ሊሾመውና ሊሸልመው አቅም ካልነበረው አመዴ በሽር ጋር ተላልኮ ወደእርሱ መኮብለሉን ሲሰሙ "እንግዲህ ማንን አምናለሁ?" ብለው ተበሳጩ አዘኑ::

ለዚህም ነው በአጤ ቴዎድሮስ ታሪክ ብቻ ሳይሆን የገብርዬ የማያወላውል ታማኝነት ብርቅና ልብ የሚነካ አርአያ ሁኖ የሚታየው:: ረጅሙን የኢትዮጵያ ታሪክ ጠለቅ ብለን ብንመረምር የታማኝነት ጉድለት ለሰላምና ለእድገት ትልቅ እንቅፋት ሁኖ ይገኛል:: የኃላፊነት ስሜታቸው ከፍ ያለ ብዙ ነገሥታት የሕዝብን ችግር ለማቃለል ተነሣስተው ይረዱናል፣ያግዙናል፣ብለው የሾሟቸው ሰዎች እያደሙ እያሳደሙ እየሸፈቱና እያስሸፈቱ ስላስቸገሯቸው ዓላማዎቻቸው ከሽፈዋል::

እንግሊዞች መቅደላን እንደከበቡ አጤ ቴዎድሮስ መጨረሻቸው እንደደረሰ በማወቅ ለጦር መሪው ለሮቤርት ናፒየር የጻፉላቸው ሁለት ደብዳቤዎችን እንደኑዛዜ ማየት ይቻላል:: እንግሊዞች በሕግና በሥነ ሥርዓት የሚተዳደሩ ሕዝቦች ናቸው:: በማለት ዓላማዎቻቸው ሁሉ ለምን እንደከሸፈባቸው ለማስረዳት የተጠቀሙባቸው ቃላት ለእኛም ለምን ከፍተኛ ትራጂዲ (እጅግ በጣም አሳዛኝ ፍጻሜ) እንደሆነ ይገልጽልናል::

በሕዝብ ግንዛቤ ጉድለት የዓላማዎቻቸው መክሸፍ ለሕዝብና ለሀገር እንደማይበጅ ባንደኛው ደብዳቤ አጤ ቴዎድሮስ እንዲህ ይላሉ:: "የአገሬ ሰው ግብር ሥራዓት ግባ ብለው እምቢ ብሎ ተጣላኝ:: እናንተ ግን በሥርዓት በተገዛ ሰው አቸነፋችሁኝ:: ጌታ ነኝ መስሎኝ ባልሰላ መድፍ ስታገል ውዬ ነው::

የአገሬ ሰው የፈረንጅ ሃይማኖት ይዟል ስልሟል እያለ አሥሩን ምክንያት ይሰጠኝ ነበረ:: እኔ ከከፋሁበት እግዚአብሔር መልካም መሪ ይስጠው:: እርሱ እንደወደደ ይሁን::" ሁለተኛው ደብዳቤያቸው ደግሞ አመራራቸው ለምን ኃይለኛ ጭካኔ እንደበዛበትና ጥረታቸው ሁሉ ለምን ከንቱ እንደቀረ ገልጸውታል::



"የአገሬ ሰው ከትእዛዝ መውጣቱን አይቼ ብገድለው ብቀጣው:: አልመለስልኝ ቢል ቢነደኝ ብቀና በገዛ ጠመንጃዬ እሞታለሁ ብዬ ሰይጣን አሳብ አሳደረብኝ::"

አጤ ቴዎድሮስ በጋፋት ያሠሩትን መድፍ ሰባስቶፖል ብለው የሰየሙት ሩሲያውያን በክራይሚያ ጦርነት በቱርኮች ላይ የተቀዳጁትን ድል እሳቸውም በግብጾች ላይ የሚደግሙት ስለመሰላቸው ነበር:: ግን የተሸነፉት ባልነቃሕዝብ ተደናቅፈውና "ባልሰላ መድፍ" መቅደላ ላይ ተዋግተው ብቻ አልነበረም:: ብሪታንያና ሌሎች ምዕራባዊ የአውሮፓ አገሮች የሩሲያውን የሰባስቶፖል ድል ቱርኮችን በማገዝ እንዳጨናገፉባቸው ሁሉ እነዚሁ አገሮች አጤ ቴዎድሮስ በግብጽ ላይ ድል እንዲያገኙ አልፈለጉም::

የኢትዮጵያ ሕዝብ በበኩሉ የአጤ ቴዎድሮስን ሞት ተመኘ:: አንዱ ወታደር ፈጣሪውን ሲያማርር አጤ ቴዎድሮስ ከኋላው ደርሰው ሰለሰሙት "ለምን ፈጣሪህን ታማርረዋለህ? ንጉሡን ግደልልኝ እንዳርፍ ብለህ ለምነው እንጂ!" አሉት:: እርሱም ሲመልስ "ጃንሆይ አልሰማኝ አለ እንጂ እኔስ ሁልጊዜ ለመንኩት" አላቸው:: ይህ የሁሉም ጸሎት ሆነ! ሕዝቡም እንደፈለገው ሚያዝያ 6 ቀን 1860 ዓ.ም ለተከፉባቸው ሕዝብ ራሳቸውን አስወገዱለት:: ችግሩ ግን ተባባሳ እንጂ አጤ ቴዎድሮስ ጋር አልተወገደለትም:: የችግሩ ምክንያት እርሳቸው አልነበሩምና::

በአጤ ቴዎድሮስ ትጉህና ፈጣን እቅዶች ተዳክመው የነበሩ ጦረኛ መሳፍንት በተዘናጋው ሕዝብ በመጠቀም እንደገና አንሰራሩ:: ከዱሮው በበለጠ ተጠናክረው ተነሡ:: እንደ አጤ ቴዎድሮስ ለድሃ በማያዝኑና በማይራሩ መሳፍንት አገር ተጨነቀች:: ሕዝብ መድረሻ አጣ! የአጤ ቴዎድሮስ መነሣት አደናግጦአቸው የነበሩት የውጭ ጠላቶች ይበልጥ ትምህርት ቀስመው በየአቅጣጫው ብቅብቅ አሉ:: የኢትዮጵያ ሕዝብም ሌላ እውነተኛ እና ታማኝ ዓላማው የማይከሽፍበት ቴዎድሮስ የሚመጣበትን ቀን እንደገና በናፍቆት መጠባበቅ ጀመረ::

ለራሳችን ለቤተሰባችን፣ለጎረቤታችን፣ ለሕዝባችንና ለአገራችን ሀቀኞችና ታማኞች ካልሆን የግልም ሆነ የጋራ ዓላማዎቻችን መንገዚም ከዳር አይደርሱም:: የአጤ ቴዎድሮስ እጣ ፈንታ የእኛም

ይሆናል። ዛሬ ስለመልካም ሥነግምባር ስለንጹሕ ሕሊና ስለይሉኝታ መወያየት የሚያሳፍር ጊዜው ያለፈበትና ለአደጋ ለተጋለጠ እሴት በከንቱ መቆዘም እንደሆነ የሚያምኑ ሰዎች አሉ። ብቸኛውና ትክክለኛው መንገድ ግን እንደ አጤ ቴዎድሮስ ሀቀኛና ታማኝ መሆን ነው። ቆንስል ፕላዊዴን ልክ እንደ ዶ/ር መርዕድ ስለ አጤ ቴዎድሮስ መልካም ባሕርያት የሚከተለውን ምሥክርነት ሰጥቷል።

"..ለጋስነታቸው በኢትዮጵያ የመዊዎች ታሪክ ወደር የሌለው ነው። ድል ሲያደርጉ ሆደ ሰፊና መሐሪ መሆናቸውን ከአንደበታቸውና ከተግባራቸው በጥንቃቄ ተመልክቻለሁ። ከመጠን በላይ ለጋስና ከማንኛውም ፍቅረ ንዋይ የጸዱ ናቸው። ድል ያደረጓቸውን ሁሉ ከተማረኩ በኋላ እንደጠላት ሳይሆን እንደወዳጅ ያዩአቸዋል።

የእምነታቸውም ጽኑነት የሚደነቅ ነው።" አቶ አማረ አፈለ ብሻው አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ ትናንትም ዛሬም ነገም በተሰኘው መጽሐፋቸው መይሳው የሞቱበትን የመቶ አርባ ሦስተኛ ዓመት ስለ ሰውየው የተሟላ ሰብእና ታላቅ ገጸ በረከት አቅርበውልናል። እግዚአብሔር ይባርካቸው።

## ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው፤

አቶ አማረ አፈለ "አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ ትናትም ዛሬም ነገም "በሚል ማራኪ ርእስ የጻፈውን መጽሐፍ ኮፒ ልኮልኝ በጥሞና አንብቤዋለሁ። የታላቁን ንጉሠ ነገሥት ገድል ሲያዘጋጅ አማኝ ማስረጃዎችን ፈልፍሎ በማውጣት ጥሩ መጽሐፍ ደርሷል። ከዚህ በፊት ባዘጋጃቸው ድርሰቶቹ ሁሉ በጣም የሚያስገርመኝ ነገር ቢኖር ለዋቢነት የሚጠራቸው ሰነድ ምስክሮቹ ናቸው።

የአጤ ቴዎድሮስን ደካማም ሆነ ጠንካራ ጎን ገልጿል። በተለይም አጤ ቴዎድሮስ የወሰዱት እርምጃ ከሕግ አንጻር መሆኑን ግልጥልጥ አድርጎ የዓይን ምስክሮች የደረሱትን በተጨባጭ ማስረጃ አስረድቷል። ብዙ ከበቂ በላይ መጻሕፍት፤መጣጥፍና መጽሔት፤ ጋዜጦች ለዋቢነት ጠቅሷል። ከዚህ በፊት አይተናቸው የማናውቅ ፎቶዎች በተጨማሪ ከመጽሐፉ የተቀመጡ ሲሆኑ በእርሱ አማካይነት ተሥለው የቀረቡ ፎቶዎች መጽሐፉን ውበት ሰጥተውታል።



አጤ ቴዎድሮስ ከውስጥም ከውጭም ከባድ ጠላቶች ነበሩባቸው። "ከሸህ ጠረኛ አንድ ወሬኛ" ያሉትም ወደው አይደለም። ዋናው ለሞት ያበቃቸው ከአገር ልጆች ውጭም ሌላው ወሬኛ ሰባኪው ሄንሪ ስተርን ነበር። ይህ ሚሲዮናዊ በጀርመን የተወለደ ይሁዳ ሲሆን በ19 ዓመቱ ወደ እንግሊዝ አገር ሥራ ፍለጋ ይሄዳል። የተጎሣቆለ ኑሮ በሚኖርበት ጊዜ በእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን "ሚሲዮን ለይሁዲዎች" ከሚባል የበጎ አድራጎት ድርጅት ሥር ይጠጋል።

በዚህ ክርስትና ይነሣና ያሠለጥኑታል። ቆይቶም ወደ መካከለኛው ምሥራቅ እየተመደበ በሚሽን ተልእኮ ይሠራል። ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ "ሚሲዮን ለኢትዮጵያ ፈላሾች" በሚል ስም በጎንደር፤ወገራ አውራጃ ጀንዳ በሚባል ቦታ በ1852 ዓም የበጎ አድራጎት ድርጅት አቋቁሞ ስብከቱን ይቀጥላል።

ይህ ሰው ሥራውን በኢትዮጵያ ሲጀምር ግን ክርስትና የሚያስተምራቸውን አሪታውያን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አባልነት አሳምኖ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቀሳውስት እንዲያጠምቁለት አጤ ቴዎድሮስና አቡነ ሰላማ ጥብቅ መመሪያ ሰጡት። አሪታውያኑን ወደ ክርስትና ለመመለስ የተፈቀደለትም ክርስቲያኖችን እንዳይከልስ በጥብቅ የተከለከለ በመሆኑ ቅሬታውን እንደ አረገዘ ለሥራ ብሎ እንግሊዝ አገር ሂዶ በነበረ ጊዜ በየቦታው የአጤ ቴዎድሮስን ስም ሲያጠፋ ቆይቶ ያነኑ ዘለፋውን በመጽሐፍ አሳትሞ ያወጣል። ለጊዜው ስለ ውጭው ዓለም ማኅበረሰብ ማወቅ የሚፈልገው የእንግሊዝ ሕዝብና አንባቢ መጽሐፉን ቢወድለትም ለዚያች ተናዳፊ ሚስቱና ለሌሎች ሚሲዮናውያንም መታሰር አንዱ ጠንቀኛ ምክንያት ይህ መጽሐፍ ይሆናል። "የምላስ ወለምታ በቅቤ አይታሽም" እንደሚባለው ሆነበት።

ከዚህ ላይ በተለይ ሃይማኖትን በተመለከተ አጤ ቴዎድሮስ የነበራቸውን አቋም ባጭሩ ማስረዳት እወዳለሁ። በአጤ ቴዎድሮስ ጊዜ የነበሩትን የላዛሪስት ሚሽን ሰባኪዎች ችግር እየፈጠሩባቸው አጤ ቴዎድሮስ አባረዋቸው ነበር። እንዲያውም "የአገሬን አፈር በጫማቸው ይዘው እንዳይሄዱ ጫማቸውን እያራገፉችሁ ላኩአቸው" ያሉም በዚህ ጊዜ ነበር። ታዲያ በወቅቱ የነበረው የፈረንሳይ ቆንስል

ጊሊበርት ጉዳዩን እንደገና እንዲያዩት አጤ ቴዎድሮስን ሲጠይቃቸው የሚከተለውን ግልጽ መልስ ሰጥተውታል::

"እስልምና በአንድነቱ ተጠናክሮ እያለ ክርስትናን በአምስት በስድስት ቡድን መከፋፈል አምባጓሮን መፈለግ ነው:: ለምን አንድ ዓለም አቀፍ የክርስቲያኖች ጉባኤ አይሠየምምና በአንድ እምነት ላይ ተስማምቶ ውሳኔ አያሳልፍም::.....ይሄ ቢደረግ ለዚህ ጉባኤ ውሳኔ እኔም ራሴን እሰገዛለሁ:: ይህ እስኪሆን ድረስ ግን እኔም በአባቶቻችን ነባር ሃይማኖት እጸናለሁ:: በአንድ ሥርዓት ባለው አገርና መንግሥትም ውስጥ አንዱ ሌላውን እንዲሰብከው እንዲከልሰው አይፈቅድም" ብለውታል::

ይህ ማለት ግን የእምነት ነጻነት የለም ማለት አይደለም:: የከለከሉት ክርስቲያኑን ክርስቲያን መልሶ ማጥመቁን ነው:: pnoseiytism አጤ ቴዎድሮስ ያሉት "ወንድሞቻችን ክርስቲያኖች ብቻ አይደሉም፣ እስላሞችና አረታውያንም እንደዚሁ የሀገሪቱን ሕግ አክብረው የንጉሠ ነገሥቱን የበላይነት ተቀብለው እስከ ኖሩ ድረስ የአምልኮ መብታቸው የተጠበቀ ነው" በማለትም አረጋግጠዋል::

እንግዲህ ስም አጥፊው ሰባኪ ሂነሪ እስቴር ይህን ጥሶ እየዞረ ስም በማጥፋቱና ይባስ ብሎ አሉባልታውን አጠናክሮ በመጽሐፍ ስላወጣና ስለሰሙ በዚያች ጠንቀኛ ደብዳቤም የባሕር መመላለሻ ዋስትና አግኝተው ከአውሮፓ ጋር የዲፕሎማሲ ግንኙነት ለመፍጠር የጥበብ ሰዎችንና የመሣሪያ እርዳታ ለማግኘት ወጣቶችን ልከው በእደ ጥበብ ለማሰልጠንና ኢየሩሳሌምን ገዳም ለማስከበር ያቀረቡት ጥያቄ ለንግሥቲቱ ሳያደርሱ ለሁለት ዓመታት በመታፈኑ እንደ ንቀት ቆጥረውት ሚሲዮናውያኑን አሰሩአቸው:: ያው ለጥበብ የነበራቸው ፍቅር እርሳቸውንም ከሞት አደረሳቸው::

በዚህ ታሪክ ውስጥ ሌላም የሚገርም ነገር አለ:: በዚያ ወቅት የንግሥት ቪክቶሪያ ባለቤታቸው ዐርፈው ነበር:: ታዲያ አጤ ቴዎድሮስ አካባቢ የነበሩ እንግሊዞች ብዙ ነገር ይመክሯቸው ስለነበር መክረዋቸው ሊሆንም ይችላል::

አጤ ቴዎድሮስ ንግሥቲቱን ለማግባት ጠይቀው እንደነበር ተጽፎ ይገኛል The English letter text of the letter was not disclosed



for some time,and until it was madle public,it was suposed to contaia severel tancitul demands and selggestions inclueding a proposal of marrigge to the qeen. p.53- The Abyssinian Difficulty Darrell Bates PS 25.40-53 አጤ ቴዎድሮስ አገራቸውን ለማልማት ሕዝባቸውን ለማሠልጠን በነበራቸው ከፍተኛ ፍላጎት ሁሉንም ለማድረግ የሞከሩ ይመስላል::

1ኛ በተለይ በጋፋት የመሠረቱት የእደ ጥበብ ፋፍሪካ በጣም አንጉቶአቸው ነበር:: እኔ የተወለድኩት አደንጎጥ ደብረታቦር ሲሆን ከጋፋት አንድ ኪሎ ሜትር አይርቅም:: ካደኩና ከተማርሁ በኋላ በ1964 ዓም ከቦታው ተገኝቼ የሀገር ታሪክ አዋቂዎችን እነ ብላታ አማማሴ መኮንንን ይገፎ በጋፋት በአጤ ቴዎድሮስ ዘመን የተገኘውን በረከት በዝርዝር ተረድቼ ዝርዝር ጥናት አጠናቅቄ ነበር:: ያን ጊዜም በዛሬዪቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ ጥር 25 ቀን 1966 ዓም "ጋፋት የአጤ ቴዎድሮስ የብረታብረት ፋብሪካ "በሚል ርእስ መጠነኛ ጽሑፍ አውጥቻለሁ::

2ኛም በጎንደር ክፍለ ሀገር ምክትል አስተዳዳሪ በነበርኩበት ጊዜ በአቶ ጳውሎስ ኞኞ የሚመራ አንድ የቴሌቭዥን ቡድን በቦታው ተገኝቶ ፊልም አንሥቶ እንዲመለስ በተደረገው ጥረት ቁጥቋጦ (ዳዋ)የለበሰውን በአራት ማእዘን መድፍ ይጠመድበት የነበረውን መከላከያ በማስመንጠር ተቀርጾ ግሩም ፊልም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ታይቷል:: አጤ ቴዎድሮስ ያን ፋብሪካ በየቀኑ ይጎበኙት ነበር:: ለሚሲዮያውያኑም ሚስት ሳይቀር እያጋቡ እየሸለሙ ያስደስቷቸው ነበር:: ታዲያ ያነን የመሰለ ንጉሥ እብድ የሚሉ እብዶች እነሱ ናቸው::

አቶ አማረ የአጤ ቴዎድሮስን 143ኛ ዓመት መታሰቢያ በመዘከር ይህን የመሰለ ለኢትዮጵያ የዋሉትን ውለታና መሥዋዕትነት በዋቢ ጽሑፎች አጠናክሮ ለአለውና ለሚቀጥለው ትውልድ ሀቁን ለማውረስ በመጻፉ ምስጋና ይገባዋል:: መጽሐፉ ተነቦ የማይሰለችና የሚጠና ነው:: መጽሐፉ ያጠነከረው አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ በዋሉላት ውለታ ላይ ብቻ ነው::

የሚስዮናውያንንና የልጃቸውን የልዑል ዓለማየሁ ቴዎድሮስን ታሪክ ሰፋ አድርጎ አልዘረዘረም:: የሰነድ እጥረት ገጥሞት ሳይሆን ናቅ

አድርጎ የተወው ይመስላል። በተለይ የልዑል ዓለማየሁን ምርኮ አኗኗርና አሟሟት ጠቅሶ ለወደፊቱ ደኅና መጽሐፍ ይጽፍ ይሆናል። ብዙ ማስረጃ በእጁ ስላለው የሚገደው ነገር ያለ አይመስለኝም።

አቶ አማረ "አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ ትናንትም ዛሬም ነገም" በተባለ መጽሐፍ ያጤ ቴዎድሮስን ውለታ የካዱና ስማቸውን ያጠፉና የሚያጠፉ ጥላቻ ወርሰው ዛሬም ስማቸውን ከማጥፋት ያላረፉ ሁሉ መለስ ብለው እንዲያስቡበት የሚመክር መጽሐፍም ነው የጻፈው። ይህን መጽሐፍ የኢትዮጵያ አንድነት መደፈር የሚቆጨው ሁሉ እንዲቆጠቁጠው የሚያደርግ ነው። በተለይም ምሁራኑን ከእንቅልፋቸው እንዲባንኑ የሚያደርግ በመሆኑ እኔ ይበል ብያለሁ።

### አቶ ታያቸው (ዘርፉ ታከለ)

አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ ትናንትም ዛሬም ነገም፤ የተባለውን መጽሐፍ እንዳርም ተሰጥቶኝ ያነበብኩት በአርምሞ እና በከፍተኛ ጥንቃቄ ነው። የአጤ ቴዎድሮስን ታሪክ በመጻሕፍትና በትያትር፣ መልኮች እየቀረበ አንብቤአለሁ፣ተመልክቸማለሁ። ነገር ግን ይህን አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ ትናትም ዛሬም ነገም የተባለውን መጽሐፍ ከሌሎች የተለየ የሚያደርገው አንዳች ነገር ቢኖር፣ከተለያዩ የሥራ ውጤቶች የተቀመረና የተቀነባበረ መሆኑ ነው።

ጸሐፊው ይህን ምርት ለአንባብያን ለማቅረብ ከግምት በላይ የሆኑ የተለያዩ መጻሕፍትን፣ልዩ ልዩ ጽሑፎችንና መሰል መጣጥፎችን ያለመታከት አንብበዋል፣ አጥንተዋል፣በየሥራ ውጤቶችም ለዚህ መጽሐፍ የሚጠቅሟቸውን ለቅመው አውጥተዋል። ይህ እጅግ ከባድና አድካሚ ሥራ እንደሚሆን እገምታለሁ። በመሠረቱ የተለያዩ የታሪክ መጻሕፍትን፣ሠነዶችንና መጣጥፎችን እየጠቀሱ መጻፍ ታላቅ ችሎታ እንጂ የሚያስነውር አንዳች ነገር የለበትም። በድፍረትና በኩራት የሚጽፉትን የሚናገሩ እኒህ ደራሲ፣ዛሬም እንዳለፉት ሥራዎቻቸው ሁሉ የተሟላ የሥራ ምርት አቅርበውልናልና እነሆ።



# ክፍል ሁለት

## ምዕራፍ 1

### ኢትዮጵያ በዘመነ መሳፍንት ሥርዓት!

በንጉሠ ነገሥት 2ኛው አጤ ኢያሱ ብርሃን ሰገድ ዘመን በ1747 ዓም ትግራይን ሲያስተዳድሩ የነበሩት ደጃዝማች ስሑል ሚካኤል ይባሉ ነበር። እርሳቸው በባሕረ ነጋሽ አርኪኮ ብቅ እያሉ ከሚሄዱ ቱርኮች ጋር ተወዳጅተው የጦር መሣሪያ እያጠራቀሙ ራሳቸውን ማደራጀት ጀመሩ። ከዚህ በኋላ ሸፈቱ። አጤ ኢያሱ ምታ ነጋሪት ክተት ሠራዊት ብለው ከጎንደር ወደ ትግራይ ገሰገሱ። ከዚያም ትድሚያ በሰላም ግባ ተብለው ቢጠየቁ ደጃዝማች ስሁል ሚካኤል አልገባም አሉ። ምክንያቱም ደጃዝማች ስሁል ዘመናዊ የጦር መሣሪያ የታጠቁ በመሆናቸው ነበር። ነገር ግን የአጤውን ሠራዊት ሊቋቋሙ አልቻሉም። ቀድሞ እምቢ ብለው የነበረውን ሰላም በራሳቸው ፍላጎት ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ሽማግሌዎችን ላኩ።

ንጉሠ ነገሥት አጤ ኢያሱም በሰላም ግባ ተብሎ ተለምኖ እምቢ ያለ ራሱ እንጂ እኛ ሰው እንዲሞት ፍላጎታችንም አልነበረምና አሁንም ይምጣ ሲሉ ለሽማግሌዎች መልስ ሰጡ። ደጃዝማች ስሑል እጃቸውን ሰጥተው ጎንደር በግዞት እንዲቀመጡ ተወሰነ። ከዚያም ምሕረት ተደርጎላቸው የንጉሠ ነገሥቱን ልጅ ወይዘሮ አስቴር ኢያሱን እንዲያገቡ ተደርጎ ከደጃዝማችነት እራስ ተብለው የቀድሞ ግዛታቸው ትግራይ ተመልሰላቸው ወደ ግዛታቸው ሄዱ። ራስ ስሁል፣ ግን እንደቀድሞው ተግባራቸው ከውጭ ኃይሎች ጋር ግንኙነት ከማድረግ አልተቆጠቡም።

ንጉሠ ነገሥት አጤ ኢያሱ ሙተው ልጃቸው አጤ ኢዮአስ በኢትዮጵያ ሲነግሡ ለራስ ስሑል ሚካኤል ደስታ ተሰማቸው። አጤ ኢዮአስ ልጅ በመሆናቸው ብቻ ሳይሆን ሌሎች መኳንንቶች ደግሞ ራስን መንግሥታቸውን ሊቀሙ ይመጣሉ ብሎ የማያስብ መሆኑን

ያውቃሉና ነው:: ራስ ስሑል "እንኳን ደስ አልዎ"ለማለት የሚመጡ መስለው 26 ሺህ የጦር መሣሪያ ከቱርክ ተቀብለው ከትግሬ ጎንደር ገቡ:: ከዚያም ግንቦት 8 ቀን 1761 ዓም አጤ ኢዮአስ ኢያሱን በሻሽ አንቀው ገደሉአቸው:: አንዳንድ ጸሐፍያን "ራስ ስሑል ከትግሬ ጎንደር እንደገቡ ከአጤ ኢዮአስ ጋር በሰላም በፍቅር ብዙ ወራት ተቀምጠዋል" የሚሉ ሲኖሩ አብዛኛው ሠነድ ግን የሚለው ራስ ከፍተኛ የሆነ የሥልጣን ፍላጎት ስለነበራቸው ሁኔታውን ለማለሳለስና የየጁ ኦሮሞዎችና የቋራ አማሮችን ጠብ በከፍተኛ ልዩነት እንዲያድግ ካደረጉ በኋላ አጤ ኢዮአስን ገድለው ሌሎችን የነገሥታት ዘሮች ከወኅኒ አምባ አምጥተው እንግሠው ለ70 ዓመቱ አዛውንት እኅታቸውን ድረው እርሳቸው አድራጊ ፈጣሪ ሁነው ሳለ የቋራ አማሮች የእቴጌ ምንትዋብ ቤተሰቦች በከፍተኛ ቁጭት ሲነሡ የየጁ ኦሮሞዎችንና አማሮችን እንዲደባበዱ ራስ ስሁል ሚካኤል አድርገዋል::

ዶ/ር ሀብተ ማርያም አሰፋ <u>የኢትዮጵያ ታሪክ ጥያቄዎችና ባህሎች</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 295 "ራስ ስሑል ሚካኤል የተባለው ሰው ተነሥቶ ነገሥታቱን በየምክንያቱ አንዱን እየገደለ አንዱን እያነገሠ ኢትዮጵያን ለሥርዓት አልበኝነት አመራር ዳረጋት:: ከጥንት ጀምሮ ለኢትዮጵያ አንድነት ምልክት የነበሩት ነገሥታት ከተደፈሩ በኋላ በሌብነት፣በቀማኝነትና በስንፍና ወድቆ የነበረው ሁሉ አሁን በያለበት እኔ ልግዛ እኔ ልግዛ በመባባል በያለበት ብጥብጥና ጦርነት ያካሂድ ጀመረ::"

"ትምህርትና ብስለት በሌላቸው ደደብ አለቆች መሪነት የተነሣ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሞት ፍርድ የተፈረደበት ለከፍተኛ የመጨረሻ ውድቀት የተጋለጠ አሳዛኝ ሕዝብ ሆነ:: ዘመነ መሳፍንት በሚባል ዘመን የሌቦች አለቆች ወሮበላ እንዲከተላቸው ዋና መጠቀሚያ ያደርጉት የነበረው መሣሪያ ዘር እየቆጠሩ የጨዋ ልጅ ነኝ በማለት ነበር:: እኔ በጣም የሚገርመኝ ወሮበላዎቹ እርስ በራሳቸው ፈታውራሪ፣ደጃዝማች፥ ራስ ተባብለው ሕዝቡን እርስ በርስ እያፋጁ ኢትዮጵያን ያጠፉአት መሆናቸው ሲታወቅ መሳፍንትና መኳንንት መባላቸው ነው" ሲሉ ጽፈዋል::

በላይ ግደይ <u>የኢትዮጵያ ሥልጣኔ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 171 "ራስ ስሑል ሚካኤል በ1761 ዓም አጤ ኢዮአስን በሻሽ አሳንቆ



አስገደለው:: በንጉሥ ሿሚና ሻሪነቱ የሚታወቀው ኃይሉ ራስ ስሑል ሚካኤል ባለሙሉ ሥልጣን በመሆን ለእርሱ አገዛዝ የሚመቹትን ነገሥታት ብቻ እየመረጠ በየጊዜው አንግሦአቸዋል" ሲሉ ጽፈዋል::

የቱርክ መንግሥት ቀኝ እጅ በመሆን አገሩን ለጠላት ለማስረከብ የተነሣው ባሕረ ነጋሽ ይስሐቅ በ1573 ዓም ድል ከሆነ ወዲህ የውጭ ጠላት ክትት ማለት ጀምሮ ነበር:: ኋላ ግን ራስ ሥሑል ሚካኤልን አገኙ:: ራስ ስሑል ሚካኤል ኢትዮጵያን በፈላጭ ቆራጭነት በሥልጣን ላይ ሲኖሩ አገሪቱን እንዲያስተዳድሩ የፈቀዱላቸው ከቤተ ክርስቲያኑ እስከ ቤተ መንግሥቱ ለትግራይ ተወላጆች ነበር:: ዛሬ እንዳለው ሥርዓት ማለት ነው:: ሌሎች ነገዶች መሣሪያ ታጥቀው አልገብርም ያለውን የገንዛ ወገኑ እንዲወጋ አዘዙት እንጂ አገር ለማስተዳደር አልሰጡም:: አንዴ ካንዱ ነገድ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሊላውን ነገድ እያደባደቡ የኢትዮጵያን ሕዝብ እንዲተላለቅ አደረጉ:: በራስ ስሑል ምክንያት በኢትዮጵያ ውድቀት የታየበት የአንድነት ምልክት የጠፋበት ዘመን ነበር::

ዶ/ር ላጲሶ ጌ.ድሌቦ <u>የኢትዮጵያ የመከራ ሥርዓትና የኤርትራ ጥያቄ</u> በተባለ መጽሐፋቸው ገጽ 106 " በ1769 ራስ ሚካኤል ስሑል በጎንደር አጤ ኢዮአስን ጨምሮ የኦሮሞና የአማራ የሥልጣን ባላንጣዎቹን ለመቅጣት 26.000 ወታደሮቹን ይዞ ወደ ጎንደር ከተማ በገባ ጊዜ" ካሉ በኋላ ::

በገጽ 107 "ራስ ሚካኤል ስሑል በአመጽ እርምጃ በጎንደር አጤ ኢዮአስንና ዕጨጌ ስላማን በማስገደልና ሁለት ሌላ አሻንጉሊት ነገሥታትን ሹም ሽር በማድረግ በአካባቢው ዘመነ መሳፍንት ተብሎ የሚታወቀውንና እስከ ዳ/ዊ ቴዎድሮስ ድረስ የሚቆየውን የጦርነት ዘመንና ሥርዓት ከመሠረተው በኋላ በኦሮሞና በአማራ የጦር አበጋዞች ኅብረት በጦር ሜዳ ተሸንፎ በሰኔ 1772 ወደ ትግሬ ክልሉ በሽንፈት ተመለሰ" ሲሉ ጽፈዋል:: በራስ ስሑል የአገዛዝ ዘመን ትቢያ የምትባለው የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገር ሱዳን የተባለችው ሀገር እንድትፈጠር ሆኖአል:: ደቡብ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያኑ መስጊድ እንዲሠራበት ሆኖአል::

ማሞ ውድነህ ዮሐንስ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 19 "ሚካኤል ሥሑል ንጉሡን ከገደሉ በኋላ ራሳቸው ለመንገሥም አስበው ነበር። ነገር ግን የአክሱም ካህናት ንጉሥ ገድለሃልና ልትነግሥ አይገባህም ስላሉዋቸው ወኅኒ አምባ ይባል በነበረው የነጋሥያን ዘሮች ማጎሪያ ታስረው ከነበሩት ለእርሳቸው የሚስማሙዋቸውን የሰባ ዓመቱን አዛውንት ዮሐንስን ከእስር ፈትተው አጼ አሰኝተው አነገሡዋቸውና እርሳቸውም እንደ ተለመደው የእንደራሴነቱን ሥልጣን ያዙ።"

"ቀጥለውም እኅታቸውን ወ/ሮ ወለተ ሥላሴን ለሽማግሌው ንጉሥ ድረው ከንጉሥ በላቀ ክብርና ሥልጣን ተደላድለው እንደተቀመጡ አሁንም ከንጉሡ ጋር ተጣሉ። ከአንድ ዓመት ንግሥና በኋላ አጤ ዮሐንስንም በእጅ አዙር አስገድለው የአጼውን ልጅ ተክለ ሃይማኖትን ስመ መንግሥታቸውን ኃያልሰገድ አሰኝተው በ15 ዓመት ዕድሜያቸው አነገሡዋቸው። እሳቸውም በፈላጭ ቆራጭነታቸው ሥልጣን ቀጠሉ" ሲሉ ጽፈዋል።

አጤ ተክለ ሃይማኖት ብቻ በአስር ዓመት ውስጥ አስር ጊዜ ከዙፋን ወርደዋል። አንዴ ስድስት ወር በሌላ ጊዜ ደግሞ አስር ቀን ብቻ የነገሡበት ጊዜ ነበር። ራስ ስሑል የገደሉት አጤ ኢዮአስን ብቻ ሳይሆን ራሳቸው ያነገሡአቸውን 2ኛ አጤ ዮሐንስን ገድለዋል። እኒህ የ70 ዓመት አዛውንት 2ኛው አጤ ዮሐንስ በሚበሉት ምግብ ላይ መርዝ ተጨምሮበት በልተው ሞቱ።

ጎጃም ውስጥ ደጃዝማች ፋሲል ለራስ ስሁል አልገዛም ብለው ሸፈቱ። ታዲያ ራስ ስሁልም ጎጃም ዳሞትና አገው ምድር ለመዝመት ሲያስቡ አዛውንቱን አማቻቸውን 2ኛ አጤ ዮሐንስን ይዘው መሄድ ፈለጉ። አጤው ግን በእድገታቸው ጸሎትና ቅኔ ቆጣሪ ሁነው የኖሩ በመሆናቸው ጦርነት አይወዱም። አጤ አልሄድም ካሉና ጎንደር ከቀሩ እኔን ሊሸሩ ይችሉ ይሆናል ብለው ገደሉአቸውና የ15 ዓመት ልጅ አንግሠው ጎጃም ይዘው ዘምተዋል።

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፤ ከአጤ ልብነ ድንግል እስከ አጤ ቴዎድሮስ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 283 "በዳሞት ሸፍቶ ብዙ ቀን ያስቸገረ ፋሲል አሁንም አልገበረም ነበርና ራስ ሚካኤል ሮ እርሱን ለመውጋት ይዘጋጁ ጀመር። ዝግጅቱም ካለቀ በኋላ ንጉሡን



አብረን እንሂድና ፋሲልን እንውጋ ብለው አማከሯቸው። አጤ ዮሐንስ ግን በወህኒ አምባ ሲኖሩ ጸሎትና ስግደት በማዘውተር ኖሩ እንጂ የጦርነት ነገር ሞክረውት አያውቁም ነበርና አልችልም ብትፈልግ ወደ ወኅኒ አምባዬ መልሰኝ እንጂ አልሄድም አሉ።"

"ራስ ሚካኤል ግን አሁን እንቢ ማለታቸው እኔ እልፍ ስል ሌላ እንደራሴ ለማድረግ አስበው ይሆናል ሲሉ ተጠራጥረው በጅ አዙር ንጉሡን ከመብል ጋር መርዝ አብልተው አስገደሉአቸው። የአጤ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥታቸው 1 ዓመት ብቻ ነው የሞቱትም በ1762 ዓም ነው። አጤ ዮሐንስ ከሞቱ በኋላ ራስ ሚካኤል የኙሀኑ የአጤ ዮሐንስን ልጅ ተክለ ሃይማኖትን ስመ መንግሥተቸውን ኃያል ሰገድ አሰኝተው አነገሡአቸው" ሲሉ ጽፈዋል።

ራስ ስሑል አገሪቱን ብቻ ሳይሆን ቤተ ክርስቲያንን ለማፍረስ የተነሡ ነበሩ። ከሶርያ ጳጳስ አስመጥተው በትግሬ አስቀምጠዉት ነበር። ምክንያቱም ራሳቸው እነግሣለሁ ብለው እንደነበር አይዘነጋም። በቀድሞው ሥርዓት አንድ መስፍን ጳጳስ ካለው ነግሥ እምቧ ይላል። ይህን ታሪክ ራስ ስለሚያውቁ ግብጽ ጳጳስ ለማስመጣት ሳይሆን ሙከራቸው በሃይማኖት አንድዓይነት ከሆኑት ከሶርያ ፓትርያርክ በቱርኮች በኩል ተላልከው ስሙ ያልታወቀ የሶርያ ተወላጅ ጳጳስ አስመጥተው ነበር።

ዲ.ን ዳንኤል ክብረት የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች በተባለው መጽሐፋቸው•ገጽ 254 "የራስ ሚካኤል ስሑልን ድጋፍ በማግኘቱ ትግራይ ውስጥ የጳጳሱ ርስት የነበረውን አዲ አቡንን ያስተዳድር ነበር። ማን ጵጵስና እንደሰጠው ሲጠየቅም የአንጾኪያ ፓትርያርክ የኢትዮጵያ ጳጳስ እንዲሆን እንደሾሙት ተናገረ" ሲሉ ጽፈዋል። ይህ ጳጳስ በ1747 ዓም ራስ ስሑል ሚካኤል ሲማረኩ አብሮ የተማረከ ሲሆን ጎንደር መጥቶ ፍትሐ ነገሥት ተዘርግቶ "ፍረዱበት" ሲባል የሕግ ሰዎች የባረከበት እጁ ይቆረጥ ብለው ፈረዱ። አጤ ኢያሱ ግን ቆረጣው ቀርቶ በአስቸኳይ ከአገር እንዲወጣ ብለው አዘዙ። በራስ ስሁል ምክንያት የተጀመረ ዘመነ መሳፍንት ኢትዮጵያን እንዳልነበረች አደረጋት።

Shifreaw Bekele Kasa And Kasa page 25 The Zamana Masafent was the period when Ethiopia was divied within itself

into several regions with no effective central authority,in other words, the state had collapsed' "ሲሉ ጽፈዋል። ኢትዮጵያ በመሳፍንቱ ግዛት ተሸንሽና የተለያየችበት ወቅት ነበርና። ለኢትዮጵያውያን ብርሃን የሚሆን አንድነት እንጂ መለያየት አይደለም። መለያየት የኢትዮጵያን ሀልውና ያስደፍራል። ታሪኳን ያደበዝዛል። የሕዝቦችዋን ፍቅር ያጠፋል።

ሀገርን ለጠላት አሳልፎ ይሰጣል። ሕዝብን ለጦርነት፤ለረኃብ ለበሽታ ይዳርጋል። ይህ በኢትዮጵያ ዘመነ መሳፍንት ተመሥርቶ ማዕከላዊው መንግሥት ባለመኖሩ አገሪቱ ጤና ያጣችበት ወቅት ነበር። እምቢ ለሀገሬ የሚል ጀግና የጠፋበት ዘመን ሲሆን ሥልጣን አፍቃሪዎችና መኳንንቶች ሀገርን በግላቸው ፍላጎት ብትንትኗ እንዲወጣ አደረጉ። ይህ ሥርዓት የለሽ ዘመነ መሳፍንት የኢትዮጵያን አንድነት ማፍረሱ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ በዘርና በጎሳ ተከፋፍሎ እንዲደባደብ የተደረገበት ሲሆን የኢትዮጵያ ጠላቶች በከፍተኛ ደረጃ ሰላዮቻቸውን ወደ ኢትዮጵያ ያስገቡበት ወቅት ነበር።

ይህ የዘመነ መሳፍንቱ ሥርዓት ዓይነት አሁን በእኛው ዘመን በኢትዮጵያ እየተፈጸመ ይገኛል። አንዳንድ ሆዳቸው ከሞላ ምንም የማይመስላቸው ወገኖቻችን የዛሬውን አስተዳደር "አገር ወዳድ ሕዝብን አፍቃሪ፤ የልማት አባት የሰላም አስከባሪ መንግሥት ኢትዮጵያ አግኝታለች" የሚሉ አሉ። በአጤ ቴዎድሮስ የተመቱት የቱርክ ቡችሎች፤በአጤ ዮሐንስ የተመቱት ግብጾች በአጤ ምኒልክ አድዋ የጠፉት ጣልያኖች ሆኑ ሌሎች ኢትዮጵያን ሲመኙ የነበሩ ሁሉ ዛሬ ዶላር ይዘው ገብተው በቀላድ ሲከፋፈሏት እያየን ነው።

## ምዕራፍ 2

## ቤተ ክርስቲያን በዘመነ መሳፍንት

ገሪማ ታፈረ <u>አባ ታጠቅ ካሣ የቋራው አንበሳ</u> በተባለ መጽሐፍቸው ገጽ 18 "ካህናቱ እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ በመባባል ተዋሕዶ÷ቅባት÷ የጸጋ ልጅ እየተባባሉ ጠብና ክርክር በመፍጠራቸው ቤተ ክርስቲያን የዓመጽ መፈጸሚያ የግፍ አደባባይ ሆነች" ሲሉ ጽፈዋል።



የኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዘመነ መሳፍንቱ ወቅት ከፍተኛ የሆነ ውድቀት ደረሰባት። የቤተ ክርስቲያን ታሪክን ለሚመረምረው በንግሥት ዮዲትና በአጤ ግራኝ አህመድ፤ በአጤ ሱስንዮስ ከደረሰባት ውድቀት ይልቅ የዘመነ መሳፍንቱ የከፋ ነበር። በአብዛኛው የታሪክ ሰነድ ለቤተ ክርስቲያን ውድቀት ከፍ ተብሎ ከተጠቀሱት እንደሆኑ አድርጎ ያቀርባል። ምናልባት ዘመነ መሳፍንቱ ጥፋት አላደረሰባትም ብለው ያስቡ ይመስላሉ።

ቤተ ክርስቲያንን የሚያገለግል ካህን በመጥፋቱ በተለይም በደቡብ ኢትዮጵያ በ330 ዓም የኢትዮጵያ መንግሥት ሃይማኖት ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ነው ከተባለ ጀምሮ በክርስቲያንነት ጸንተው የኖሩ ሕዝቦች በዘመነ መሳፍንቱ ወቅት አስተማሪ በማጣት ክርስቲያን እምነታቸውን ትተው እስልምና ሃይማኖት እንዲቀበሉ ሁነዋል።

አባ ጎርጎርዮስ የሸዋ ሊቀ ጳጳስ <u>የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 73 "ኢትዮጵያ በመሳፍንት በተከፋፈለች ጊዜ ግን የደቡብና የምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን ብዙው ወደ እስልምና ወደ አረማዊነት ተለወጠ። በክርስትናቸው የጸኑትም እስከ አራት ትውልድ ድረስ ካህን አይተው አያውቁም ነበር። ሃይማኖታቸውንም የሚያውቁት ካባቶቻቸው ባገኙት ልማድ ብቻ ነበር። ለምሳሌ በሊሙ (እናርያ) አጠገብ ኖኖ በሚባለው አገርና ባካባቢውም ጥንት ሳይለወጥ የመጣውና የአባቶቻቸውን የክርስትና ሃይማኖት ጠብቀው የኖሩ ክርስቲያኖች ነበሩ።"

"አጽዋማት በዓላትን ሳይቀር ባሕረ ሐሳብ ሳይኖራቸው ራሳቸው በልማድ ያወጧቸው ነበር። በአካባቢዋ ላሉት የክርስቲያን አውራጃዎችና መንደሮች መሪ ብርሃን የነበረችው ኖኖ ለመቶ ዓመታት ያህል ካህን አይታ አታውቅም ነበር። በቄስ ማጣት ምክንያት ብዙዎቹ ክርስቲያኖች እምነት እንጂ ጥምቀት አልነበራቸውም።"

"ከኖኖ ቀጥሎ ብዙ ሕዝበ ክርስቲያን የሚኖርበት አገር ሞቻ የተባለው ነው። በሞቻ ግራኝ እንኳ ያላፈረሳቸው ብዙ አብያተ ክርስቲያንት ነበሩ። የዚህ አገር ክርስቲያኖች በየሳምንቱ እሑድ ወደ ቤተ ክርስቲያን በሚሰበሰቡበት ጊዜ ቀድሶ የሚያቆርብ ቄስ ስላልነበራቸው ልጆቻቸውን አዝለው ቤተ ክርስቲያኑን እየዞሩ ÷

ንስእለኪ ማርያም ፥እያሉ ልመናቸውንና ጸሎታቸውን ለእግዚአብሔር አሰምተው ይመለሱ ነበር። ይህ ዓይነቱ የክርስቲያኖች ችግር በጣም እየባሰበት ሔደ።”

“የዚህ ክፍል ባላባቶችና ታላላቅ ሰዎችም ከሱዳንና ከዓረብ አገሮች የሚመጡ ሽቱና ልዩ ልዩ የጌጥ ዕቃዎችን ለማግኘት ሲሉ ከዓረብ ነጋዴዎች ጋር ወዳጅነት አበጁ በዚህ ሳቢያ ዓረቦች ሃይማኖታቸውንም ቀስ በቀስ አስጠኗቸው፥የእስልምናን ሃይማኖት ያለምንም ችግር ተቀበሉ” ሲሉ ጽፈዋል።

በኢትዮጵያ ዳር በዳር ያሉ ክፍለ ሀገራት በዓረብ ነጋዴዎች እስልምና ሃይማኖትን ሲማሩ በመሐል ኢትዮጵያ እስልምና ሃይማኖት ሲመሠረት ጀምሮ የነበረ ሲሆን በዚህ ወቅት ከፍተኛ እድገት አሳይቷል። ራስ ስሑልን አሮሞውና አማራው ተባብረው ድል ሲያደርጉ የመሳፍንቱን አገዛዝ የተረከቡት የየጁ አሮሞዎች እስላሞች ነበሩ። በዚህ ወቅት ቀደም ሲል ጸረ ኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ናቸው ከተባሉት 3 ጦርነቶች ይልቅ ክርስቲያኑ ሕዝብ የባለገበት ጊዜ ነበር።

መባለግ ማለት ጉልበት ካለኝ አቅም ካለኝ ምን ቸገረኝ ተብሎ ክርስቲያኖች “አንድ ወንድ ላንድ ሴት” ብሎ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረው ትምህርት የተናቀበት ጊዜ ነበር። በተለይም በዚያን ወቅት ቄሶች ሆዳቸው ከሞላ “ በጎቼን ጠብቅ፥ጠቦቶቼን ግልገሎቼን አስማራ ”ተብሎ ለጴጥሮስ የተሰጠውን ትእዛዝ የነሱ አልመሰላቸውም ነበር። በአንዳንድ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ ተቀድሶ ሥጋ ወደሙ የሚቀበል ምእመን እስከመጥፋት ደርሶ ነበር።

ገብረ ዮሐንስ ገብረ ማርያም <u>ክርስትና በኢትዮጵያ ክፍል 2</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 59 “ያለምንም ቁጥጥር በየብስና በባሕር ንግድን እያመካኙ ወዳገር የሚገቡ ዓረቦች የኢትዮጵያ የተቀደሰ ክርስቲያናዊ ጋብቻ እንዲበላሽ አድርገዋል። በጋብቻ ላይ ጋብቻ መፈጸም ከዚያ በፊት እንኳን ድርጊቱ ጨርሶ አይታሰብም ነበር። ዓረቦች የኢትዮጵያን ሕዝብ የጎዱት በጋብቻ ሥርዓት ማበላሸት ብቻ አይደለም።”



“ፋቅራ፥ቃልቻ፥እየተባሉ በየስፈሩ በመስገድ በጥንቆላና በመተተኛነት እንዲመካ አድርገውታል። ብዙዎቹ ኢትዮጵያውያን ሥራዬ ብለው በዚሁ የአታላይነት ተግባር እንዲሰማሩ አድረገዋል። ጠንቋዮች ክርስቲያኑን የኢትዮጵያን ሕዝብ እርስ በርሱ እንዳይተማመን በወንድሙ ላይ በጥላቻ እንዲነሣ እንዲገዳደል ሲያደርጉ ኑረዋል” ሲሉ ጽፈዋል።

በዚያ ወቅት ቅምጥ የሌለው ወንድ ጀግና አይባልም ነበርና አቅም ያለው ይሁን አቅም የሌለው ሁለተኛ ሴት ማስቀመጥ ባህል ተደርጎ ነበር። አጤ ቴዎድሮስ ራሳቸው ሚስትና ቁባት የነበራቸው ሲሆን ከነገሡ በኋላ ቅድሚያ ራሳቸው ቁባቶቻቸውን ሲያሰናብቱ የሕግ ሚስታቸው እቴጌ ተዋበች አሊ አሉላ ጋር በሥጋ ወደሙ ሥርዓት ሲጋቡ ቁባት ከነበሩት የየጁዋ ቆንጆ ወይዘሮ የተመኙ ብቻ “እምነትህ እምነቴ በመሆኑ ብወድህም አልለይህም ከዛሬ ጀምሮ ትልቅ እህትህ ነኝ” ብለው ጸንተዋል።

ወይዘሮ የተመኙ አጤ ቴዎድሮስ ሚያዝያ 6 ቀን 1860 ዓም ራሳቸውን ሲገድሉ ተለያዩ እንጂ ወንድምና እኅት ሁነው ኑረዋል። በዘመነ መሳፍንቱ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ውድቀት የገባችበት እስልምና ሃይማኖት የተስፋፋበትና በጃቸው መጽሐፍ ቅዱስ የያዙ ውስጣቸው ተኩላ የሆኑ የውጭ ሃይማኖት ድርጅቶችም ሰላዮቻቸውን ወደ ኢትዮጵያ ያስገቡበት ወቅት ነበር።

ገና ዘመነ መሳፍንቱ ሲጀመር የስኮትላንድ ተወላጅ ጀምስ ብሩስ ዓባይን ተከትሎ ኢትዮጵያ ገብቶ ከ300 በላይ መጻሕፍት ጭኖ ወደ አገሩ ተመለሰ። እሱን እየተከተሉ ሌሎች አውሮፓውያን ወደ ኢትዮጵያ ፊታቸውን አዞሩ። መሳፍንቱ ከአውሮፓ ሆነ ከዓረብ አገር የሚመጡት ነጋዴዎች ሆነ ሰላዮች የሚሰጡአቸውን የክብር ስጦታ ተቀብለው ያስተናግዱ ነበር እንጂ ለምን መጣችሁ ብለው አይጠይቁም ነበር።

የዘመነ መሳፍንቱ ድክመት ከአገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በኢየሩሳሌም የነበረን ርስት ከ1010 ዓመተ ዓለም ጀምሮ የኢትዮጵያ የነበረውን ዶ.ር ሱልጣን ገዳምን ግብጾች ኢትዮጵያውያን መነኮሳትን አስደብድበው ገድለው ቁልፉን በእጃቸው ያስገቡበት ወቅት ነበር። ዘመነ መሳፍንቱ እንኳን ኢየሩሳሌም ላሉት የገዳም ጠባቂዎች ቀለብ

ሊልክ ቀርቶ መኖራቸውንም ረስቶአቸው ስለነበር ግብጾች በዚያን ወቅት የወሰዱት ዛሬ ድረስ የዓረብና የእስራኤል የሥነ መንግሥት ፖለቲካ መደራደሪያ ሁኖአል። ይህን ገዳም የተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮች፣ብቻ ሳይሆን የእስላሞችና የአሪታውያን ርስት መሆኑ ታውቆ ለወደፊቱ ያላሠለሰ ጥረትና ድርድር የሚያስፈልገው ነው።

በኢየሩሳሌም ነዋሪ የሆኑ ቤተ እስራኤላውያን በእነሱ እጅ የወደቀ መሆኑን ሳስገነዝብ እወዳለሁ። በእስራኤል የሚኖሩ የአሪት አማኝ ኢትዮጵያውያን ዴር ሱልጣን ገዳም በሚፈጠረው ችግር ግንባር ቀደም ታሪክ ተረካቢዎች እንደምትሆኑ አልጠራጠርም። ከኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶ ሃይማኖት ጋር ልዩነታችን ጌታችን መወለዱን በመቀበልና ባለመቀበል እንጂ ሌላ ልዩነት ስለሌለን የታሪክ ቅርሳችን የሁላችን መሆኑን ለማስገንዘብ እሻለሁ።

ይህን የመሰለውን ታሪካዊ ቦታችን እንድናጣው የሆነው በመዘነ መሳፍንቱ ደካማ አስተዳደር ምክንያት ነው። ዘመነ መሳፍንት በአገር የእስልምና ሃይማኖት የተስፋፋበት ወቅት ሲሆን በአንጻሩ ደግሞ ቃልቻና ጠንቋይ በጣም የተስፋፋበት ሲሆን በክርስቲያኑ በኩል ደግሞ ልዩነት የታየበት ዘመን ነበር። ለምሳሌ ቅባትና ካራ ተባብለው የቤተ ክርስቲያን ልጆች እርስ በርሳቸው ተጣልተዋል ተለያይተዋል።

ቃልቻ ጠንቋይ ተስፋፍቶ ሁለት ወይም ሦስት ሴት ማግባት ባህል ሁኖ ሳለ የዚህ መጽሐፍ መነሻ አጤ ቴዎድሮስ ተነሥተው መሳፍንቱን አንድ ባንድ ደብድበው ቃልቻና ጠንቋይን አስወግደው ሁለትና ሦስት ሴት አግብቶ የነበረውን ሁላ ባንድ ሴት መቁረብ እንዳለበት በአዋጅ አስነግረው በማጥፋታቸው እነሆ ዛሬ እንደ ቀድሞው የሃይማኖት መምህራን መፍለቂያ ሁኖ ሲገኝ አንዳንድ ግለሰቦች ደግሞ ምንጩን ማድረቅ ጊዜው አሁን ነው በማለት ከተነሡ ውለው አድረዋል። እንኳን ከፈከረ ከወረወረ የሚያድነው አምላክ ኢትዮጵያን ይጠብቃት።

ዛሬም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ልክ በዘመነ መሳፍንቱ ወቅት እንደደረሰባት ዓይነት ችግር ገጥሟታል። ራስ ስሑል ሚካኤል አጤ ኢዮአስን ጎንደር ላይ ሲገድሉ የቤተ ክህነቱን እጨጌ ሰላማንም አብረው አስገድለዋቸው ነበር። በዚህ ምክንያት በቤተ ክርስቲያኑ



ችግር ገብቶ ነበር። ወያኔ የራስ ስሁል ሚካኤልን ፈረስ ጭኖ አዲስ አበባ ገብቶ የኢትዮጵያን መንግሥት አፍርሶ አገሪቱን ያለ ባሕር በር ያስቀረ ሲሆን በሃይማኖት በኩል ደግሞ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስን ከአገር አስወጥቶ የራሱን አሻንጉሊት ከዚህ ቀደም ስጽፍ "ብፁዕ ወአደናግር አቡነ ጳውሎስ" እያልኩኝ እጽፍ ነበር።

የማደናገራቸው ውጤት ጣዖት አቁመዋል። ከዛሬ ጀምሮ ደግሞ ብፁዕ ወጣዖት አቡነ ጳውሎስ እያልኩኝ እጽፋለሁ። ወያኔ እርሳቸውን ሹሞ ቤተ ክርስቲያን እንድትጠፋ አድርጓል። የብፁዕ ወጣዖት አቡነ ጳውሎስ ልጆች የማይገባችሁ ነገር ቢኖር ከቤተ ክርስቲያን በር ላይ በተለይም ከመድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን በር ላይ የእርሳቸው ጣዖት ቁሞአልና።

በቤተ ክርስቲያን ላይ የደረሰው ችግር ልክ በዘመነ መሳፍንቱ ወቅት እንደነበረው ዓይነት መሆኑን ተገንዘቡ። በዘመነ መሳፍንቱ ወቅት የተዋሕዶ ሃይማኖትን የሚያጠፉ ቃልቻ እና ጠንቋይ ሟርተኛና ሌላም ሌላ መመሥረቱ ብቻ ሳይሆን በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት በአንዲት ሴት ጸንቶ የሚኖር ወንድ አልነበረም። በዚህ በያዝነው ዘመንም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የወደቀችበት ልክ እንደ ዘመነ መሳፍንት ዘመን ነው። ይህ ጉመደው የተባለው ወረርሽኝ በሽታ በዓለም ሲገባ በኢትዮጵያ መብዛቱ አይዘነጋም።

ቤተ ክርስቲያን ጸሎት ማድረግና አንድ ወንድ ላንድ ሴት ብላ ማስተማር ሲገባት ለታመሙት ሕሙማን ጸበል መስጠትና መርዳት ሲገባት መከላከያ ተብሎ ኮንዶም ታድላለች። በዚህ ጉድ ሲባል ዋናው የቤተ ክርስቲያኗ አፍራሽ ምስላቸውን ጣዖት አሠርተው መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ገጭ አደረጉት። የናቡከደኖጾርና የሌሎችም የነአውግስቶስ ቄስሣር ጣዖት ዛሬ በቤተ ክርስቲያናችን በር ላይ ተተከለ።

ብፁዕ ወጣዖት አቡነ ጳውሎስ "የምስሌ ጣዖት ከቤተ ክርስቲያን በር ላይ መተከል አለበት" ካሉ ደግሞ ከሌላ ቤተ ክርስቲያን ማለትም ጊዮርጊስ፤ያሬድ፤አቦ በጻድቃን ስም ከተመሠረተ ቤተ ክርስቲያን በር ቢያቆሙት በተሻለ ነበር። አስገራሚውና አስደናቂ የሆነው ጣዖቱ የቆመው መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን በር ላይ መሆኑ ራሳቸው ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ በላይ መሆናቸውን አስመስክረዋል።

ስለዚህ በቤተ ክርስቲያን ላይ የደረሰው ችግርና ስደት ልዑል እግዚአብሔር አይቶ ብድሩን ይመልስ ይሆናል።

በዘመነ መሳፍንት አገዛዝ የነበረው ቅባትና ካራ የፈጠረው ጭቅጭቅና ንትርክ ለቤተ ክርስቲያን ውድቀትን ያስከተለ እንደነበር ታሪክ ቁልጭ አድርጎ እያሳየ ይገኛል። ዛሬም ቢሆን ይህ የሃይማኖት ልዩነት እንዲበራከት ያደረጉት አባቶቻችንና ገዥዎቻችን ናቸው። ዛሬ የአንድ ሰው ሦስት ልጆች ቢኖሩት በሃይማኖት ግን አንድ አይሆኑም። የሃይማኖት በዓል ሲከበር እንደ አገራችን አብሮ ቤተሰብ መዋል ከቀረ ውሎ አድሯል። ቤተሰብ ከቤተሰብ በሃይማኖት ምክንያት ተለያይቷል።

## ምዕራፍ 3

### የኢትዮጵያ ሕዝብ በዘመነ መሳፍንቱ

ራስ ስሁል ሚካኤል አጤ ኢዮአስን በሻሽ አንቀው ሲገድሉ ብዛት ያላቸው መኳንንቶች በእርሳቸው ላይ መሸፈት ጀመሩ። በዚህ ወቅት ብዙ ሰዎችን ምሕረት እንዲገቡ ካደረጉ በኋላ ፈጅተዋቸዋል። በነገራችን ላይ ወያኔዎች አሁን የሚያደርጉት ቀደም አያታቸው ራስ ስሁል ሚካኤል እንዳደረጉት ነው። ቅድሚያ በርሃ ሲገቡ አዛውንቱን የምክር ቤት አባል ስማቸውን አስቀይረው "ስሁል" ነበር ያሉአቸው። ድርጅቱን በአንድ እግሩ ካቆሙ በኋላ አቶ ገሡሡን ገደሉአቸው። ሌሎችንም እንዲሁ ሌላው በእነሱ ላይ የሸፈቱትን ምሕረት እንዲገቡ ካደረጉ በኋላ ልክ ራስ ስሁል እንዳደረጉት እነሱም እየገደሉአቸው ነው።

ለምሳሌ የጎንደር ተወላጆች የወልቃይት ልጆች "ወልቃይት አማራ ጎንደሬ እንጂ ትግሬ አይደለም" በማለት መዋጋት የጀመሩ ናቸው። ወያኔ የኢትዮጵያን መንግሥት ሲያፈርስ የወልቃይት ልጆች ከፋኝ ብለው በርሃ ገብተው ነበር። የትግራይ ጠቅላይ ገዥ አቶ ገብሩ አሥራት በሽምግልና እንዲገቡ ካደረጉ በኋላ አንድ ባንድ አስረው ገድለዋቸዋል። እንዲያውም ካንዴም ሁለቴ ሽማግሌ ሂዶ ጠይቋቸው "በባርኖሶች አትምጡብኝ ለባርኖሶች ጊዜ የለኝም" በማለት



መልሰዋቸዋል። ባርኖስ ማለት "ተባይ አንበጣ ማለት ነው በትግርኛ" ይህን ማለታቸውን ከአንደበታቸው ራሴ ጠይቄ ተረድቻለሁ።

አቶ ገብሩ አሥራት ሲያትል መድረክ ስብሰባ ላይ ሚያዝያ 2 ቀን 2002 ዓም፤ወይም ሚያዝያ 10 ቀን 2010 ከላይ የተጠቀሰውን በእኔ ተጠይቀው አላልኩም አላሉም። ያሉት ነገር ቢኖር "ባርኖስ ለተባለው በወቅቱ እኔ የትግራይ አስተዳዳሪ ነበርኩኝ፤ጦርነት ነበር፤ ዛሬም ጦርነት አለ፤ጸጥታውን ለማስጠበቅ ሠርቻለሁ" ሲሉ ማሠራቸውንና መግደላቸውን አልካዱም።

ከዚህ ላይ ይህን ተመሳሳይ ታሪክ የጠቀስኩት በዘመነ መሳፍንቱ መሥራች በራስ ስሁል ሚካኤል፤ ምሕረት ተደርጎላቸው ገብተው የሚገደሉ አማሮች ነበሩ። ዛሬም ምሕረት ተደርጎላቸው ገብተው የሚገደሉት አማሮች ናቸው። አገዳደሉ ራስ ስሁል ገድለው ሰውን እንደ ፍየል ገፈው ገለባ ሞልተው ማስፈራሪያ ያደርጉታል። የዛሬው ደግሞ ተገድሎ በርሃ ይጣላል፤ለምሳሌ ራሳቸው ወያኔዎች ያወጡት የምስል ድምጽ ዋቢ ነው።

<u>ንጋት የምስል ድምጽ የቪዲዮን ካሴት</u> አማሮች ሐረር ተገድለው ገደል ተወርውረው አስከሬናቸው ሲወጣ ይታያል። እንዲሁም ደግሞ በዘመነ ኢሕአዴግ ዘመን በደቡብ ኢትዮጵያ የሚኖሩ አማሮች መገደላቸውን ራሳቸው አባ ዱላ ገመዳ በመጽሐፋቸው በምስል አስደግፈው ጽፈውታል።

አባ ዱላ ገመዳ <u>የኦሮሞ ሕዝብ ትግል ከየት ወዴት?</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 148" ሕፃናትንና አሮጊቶችን እንዲሁም ነፍሰ ጡሮችን ሳይቀር ዘግናኝ በሆነ ሁኔታ አረዳቸው። ሽማግሌዎችን ገድሎ ወደ ጉድጓድ ጣላቸው" ይሉና የተገደሉትን በምስል በፎቶ አስደግፈው ገጽ 153 "ኦነግ በበደኖ ሕዝብ ላይ ያደረገው ኢሰብአዊ ድርጊት" ይልና የሚታየው ሕዝብ ከታች ያለው ምስል ሲያሳይ በገጽ 53-55 ያለው ምስል የሕዝብ እልቂት ይታያል።

በነገራችን ላይ አባ ዱላ ገመዳ ኦነግ ገደላቸው ይበሉ እንጂ ኦነግ ደግሞ እርሳቸው መጽሐፍ ከመጻፋቸው አስቀድሞ ከረር ያለ መግለጫ አውጥቶአል። በእርግጥ ኦነግ በበደኖ ወደ ትውልድ አገራቸው እንዲሄዱ ያደረኩኝ የደርግ ሠራዊት አባላትን ነው

ይላል:: የደርግ መንግሥት ሠራዊት ቢሆኑ ከበደኖ መባረር አልነበረባቸውም:: ምክንያቱም የተወለዱበት ቀበሌ ባይሆንም አገራቸው ኢትዮጵያ በመሆኑ መቀመጥ ነበረባቸው::

በካልቻ ኦሮሚያ ጋዜጣ ሰኔ 10 ቀን 1984 ዓም ገጽ 3 "ኦነግ የበደኖን አካባቢ ከደርግ ሠራዊት ሲያፀዳ ከተለያዩ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች የተማረኩት የሠራዊቱ አባላት ያለምንም መንገላታት ወደ ትውልድ አካባቢያቸው እንዲመለሱ እንደተደረገ ራሳቸው ምስክሮች ናቸው" ይልና::

"በአጠቃላይ ኦነግ በበደኖ አካባቢ በነበረባቸው ጊዜያት ሁሉ ሰላምና መግባባት ለመኖሩ ሕዝቡ ምስክርነት እየሰጠ ኦነግ አካባቢውን በለቀቀበት ኢሕአዴግ ሠራዊት በገባበት ትርምስና ምስቅልቅል ውስጥ ለተፈጸመ ሁኔታ አንድ ወገን ብቻ ተጠያቂ ለማድረግ የተካሔደው ርብርቦሽ ሚዛናዊነቱና እውነትነቱ ምን ያህል ነው? ለሚለው ሁኔታውን የተከታተለው ሕዝብ የሚዳኘው ቢሆንም ለበደኖው የበለጠ ሚዛን በመስጠትና በማጥበቅ ተቆርቋሪነትንና ለሰብአዊ መብት ተሟጋችነትን ለማሳየት ተሞክሯል" ሲል ጽፏል::

በኦነግ መግለጫ መሠረት በበደኖ ሕዝብ ላይ ግድያ ያደረሰው ኢሕአዴግ መሆኑን ሙሉ በሙሉ ለመግለጽ ባይፈልግም ሕዝብ መገደሉን ግን አልካደም:: ኦነግ በአካባቢው ባልነበረበት ወቅትና ወራት ብዙ ሕዝብ ተገድሏል:: እንኳን በደቡብ ኢትዮጵያ ቀርቶ አዲስ አበባ ሳይቀር ሰው አልቋል:: ለዚህ ኦነግ ገደላቸው ብሎ መጮኽ ደግሞ ትክክል አይደለም::

ወያኔም የሕዝብ ደም መጣጭ ነው:: ሌላም በ2000 ዓም በደቡብ ኢትዮጵያ ክርስቲያኖች አማሮች በአንገታቸው ታርደው የተቀረጸው የምስል ድምጽ ዋቢ ነው:: ይህን ስል በዘመነ መሳፍንቱ ዘመን ሆነ ዛሬ ባለው መንግሥት የሚገደለው አማራ ብቻ ነው ማለቴ አይደለም:: እንዲያውም በወያኔ ቅድሚያ የተገደለው የትግራይ ሕዝብ ሲሆን ሌሎችም ኢትዮጵያውያን በራስ ስሁል ሚካኤል የልጅ ልጆች በወያኔዎች እየተገደሉ ናቸው:: በዚያን ዘመን ደጃዝማች ፋሲል በራስ ስሁል ሚካኤል ላይ በመሸፈታቸው እርሳቸውን ለመውጋት ራስ ስሑል ሚካኤል ከጎንደር ወደ ጎጃም ሲዘምቱ ያለቀው ሕዝብ ቁጥሩ አይታወቅም::



ከአጤ ልብነ ድንግል እስከ አጤ ቴዎድሮስ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 284 "ፋሲልም የዳሞትን የአገውን ጦር ይዞ ፋጊት ከሚባለው ስፍራ ይጠባበቅ ነበርና በዚሁ ስፍራ ላይ ጦርነቱ ተዠመረ:: ብዙ ሰዓት ሁለቱም ወገኖች በኃይል ሲዋጉ ቆዩ:: ግን ከሁለቱም ወገን 10 ሺህ ሰው ከሞተ በኋላ ፋሲል ድል ሆነና በፈረስ ከጦርነቱ ቦታ አመለጠ:: ፈረሰኞችም ቢከታተሉት ለማግኘት አልቻሉም::"

"ከዚህ በኋላ ከርሱ ጦር ውስጥ የተማረኩትን በራስ ሚካኤል ትእዛዝ ገደሏቸው:: ከነዚህም ዋጩቃ የሚባለው የፋሲል ተከታይ ይምሩኛል ብሎ እጁን ከሰጠ በኋላ ጭፍሮቻቸው እርሱን ገድለው ቆዳውን እንደ ከብት ገፈው እንደ ስልቻ ሰፍተው ገለባ ሞልተው ለራስ ሚካኤል አሳዩዋቸው:: የዚህ ታሪክ በብዙ የውጭ አገር ደራሲዎችና ባገራችንም ጽሑፉ ተጽፎ ይገኛል" ሲሉ ጽፈዋል::

ግርማ ኃይሌ፣ የጎንደር ታሪክ ከኢትዮጵያ ታሪክ አንጻር በተባለው መጽሐፍ ገጽ 233 "ራስ ስሁል ሚካኤል የዳሞትን ገዥ ፋሲልን ለመውጋት ንጉሠ ነገሥቱን ይዞ ሄደ:: ፋሲልም የዳሞትና የአገውን ጦር ይዞ ፍጊት በምትባለው ቦታ ሲጠብቅ ጦርነት ተከፍቶ በኃይለኛ ውጊያ ገጥመው ከግራ ቀኙ ቁጥር 10ሺ የሚደርስ ሰው ካለቀ በኋላ ድል የራስ ስሑል ሚካኤል ሲሆን ፋሲል ሸሽቶ አመለጠ:: ምርኮኞቹንም ራስ ስሑል ሚካኤል በጭካኔ አስፈጇቸው:: ምሕረቱንም በመሻት የገቡትን የፋሲልን ተከታዮች ሁሉ ወታደሮቹ ኢ-ሰብአዊ በሆነ ጭካኔ እንደከብት ቆዳቸውን ገፈው በውስጡ ገለባ በመሙላት ለራስ ሚካኤል አሳዩት:: በዚህ ጭካኔ የአማራ ሳይንት ራስ ጎሹና ደጃዝማች ወንድወሰን ከዱት" ሲሉ ጽፈዋል::

የዘመነ መሳፍንቱ መነሻ ራስ ስሑል ሚካኤል ይሁን እንጂ የእርሳቸውን ሥልጣን ለመንጠቅ በተደረገው ጦርነትና እርስ በራሳቸው እኔ ልግዛ እኔ ልግዛ በመባባል ሕዝቡን ያፋጁት መሆናቸው አይዘነጋም:: ለምሳሌ በየክፍለ ሀገሩ ሳይሆን በየአውራጃው የጎበዝ አለቃ እየተነሣ የተፋጁበት ወቅት ነበር::

የኢትዮጵያ ሕዝብ በመዘነ መሳፍንቱ አገዛዝ የነበረበት ችግር ብዘረዝረው የዛሬው አንባቢ ለማመን ይቸገር ይሆናል:: ቆንጆ ልጅ የወለደ ባላገር ባካባቢው ያለው ፉንጋ በ15 ዓመቷ ቀምቶ

ይጫወትባታል:: የጀግና ልጅ ከሆነች ደግሞ እድሜው ሳይሆን ሥልጣኑ ተገምግሞ ለሥልጣን መቆናጠጫ ትሰጣለች:: ለዚህም ነው አጤ ቴዎድሮስ እንደነገሡ ከፍተኛ የሆነ ሕግና ደንብ ያወጡት ለምሳሌ "ማንም ሰው ሴት ልጁን ለአቅመ ሔዋን ሳትደርስ ለሹመትና ለሥልጣን ተብላ እንዳትዳር ይሁን" ሲሉ ያወጁት ወደው ሳይሆን ብልግናው ሰፍቶ በማየታቸው ነው::

ዘመነ መሳፍንቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የባህል ችግር ሳይሆን ሌላም ሌላ መጥፎ ልማድ አስለምዶት ነበር:: ለሥራና ለንግድ ከአንድ አውራጃ ወደ ሌላው አውራጃ መዛወር ይከለከል ነበር:: ምክንያቱም መሳፍንቶች የራሳቸውን ክብር እንጂ የሕዝቡን ክብር ምን እንደሆነ አያውቁም:: ጦርነት ገጥመው ከተማረከ ወይም ከሚጠሉት መሳፍንት ጋር ግንኙነት አለው ብለው ካመኑ ያንን ግለሰብ ይገድሉታል:: በኢትዮጵያ ታሪክ ብዙ ጨካኞች ኑረዋል:: ብዙ ነፍሰ ገዳዮች ነበሩ ዛሬም አሉ ከጭካኔቸው ብዛት የተተነሣ የተማረከን ሰው ገድለው ቆዳውን ገፈው ገለባ ሞልተው ማስፈራሪያ ያደርጉት ግን ራስ ስሁል ብቻ ናቸው::

<u>አሌፍ መጽሔት</u> ቁ 1 ነሐሴ 1984 ዓም ገጽ 17 "የቀድሞ ነገሥታትና ሹማምንት ፈሪሃ እግዚአብሔር ያደረባቸው ናቸው የተባለላቸውን ያህል ኢሰብአዊም ነበሩ:: ሚካኤል ስሁል ጎጃም ውስጥ በተደረገ ጦርነት ከጠላት ወገን የተማረከ ሰው አስገድለው ቆዳውን አስገፍፈው ቆዳውን አሰፍተው ድርቆሽ ከተው ምስል ማስፈራሪያ ማድረጋቸውን ዜና ስንሰማ ወይም እንደ ተረት ሲነገረን የሚያረጋግጠው ኢሰብአዊነታቸውን ነው" ሲል ጽፎአል መጽሔቱ:: ይህ መጽሔት ጎጃም ውስጥ በጦርነቱ የተማረኩት ሰዎች ተገለው ቆዳቸው ተገፎ ገለባ ሞልቶ ለማስፈራሪያ የተሰቀለ መሆኑን ሥዕል ያሳያል:: ወያኔም በሽሬ ጦርነት የማረካቸውን የኢትዮጵያ ወታደሮች አስከሬናቸውን በእሳት አቃጥሏል::

መንግሥት ደምስሰው የተነሡት መሳፍንት በበኩላቸው ኃይላቸውንና የሠራዊታቸውን ብዛት እየገመቱና እየመዘኑ እኔ እገዛ እኔ እገዛ በመባባል በየጊዜው የእርስ በርስ ጦርነት እያበቀሉ ሕዝቡን ያጋጩትና ያፋጁት ጀመር:: በየለቱ ቆነጃጅት እየተመለመሉ የመሳፍንቱን ፈቃደ ሥጋ እንዲፈጽሙ ተገደዱ አገሪቱ በዝሙት ረከሰች:: እንዲሁም ከመሳፍንቱ ወገን የሆነ ጎጅ የተባለው የየጁ



ባላባት በየጊዜው ጦርነት እያነሣ በሚያደርገው እልቂት በጦርነቱ ተጠቅተው የሚማረኩትን ኃይሉን ለማሳየት ሲል ዓይናቸውን እያወጣ በዕንቅብ ቆልሎ ከምርኮኞቹ አንዱን ሰው ዓይኑን ሳያወጣ መሪ አድርጎ አምሳ ስድሳውን እንደ ግመል እጅ ለእጅ እያያያዘ ወደ አገራቸው ይሰዳቸው ነበር::

የትግራይ ራሶች ባሕረ ነጋሽ ኤርትራን ጨምሮ ይገዙ ነበር:: ለዚህም ነው ዛሬ ሻዕቢያዎች የትግራይን ልጆች "አጋሜ" የሚሉአቸው:: በዘመነ መሳፍንቱ ወቅት ቀጥቅጠው ገዝተዋቸዋል:: ባሕረ ነጋሽ ኤርትራን ምን የትግራይ ልጆች ብቻ ደጃዝማች ውቤ ኃይለ ማርያም ስሜን ሁነው እስከ 1845 ዓም ድረስ ይገዙአቸው ነበር:: በትግራይ የነበሩ ራሶች ራስ ወልደ ሥላሴ፤ ደጃዝማች ሰባጋዲስ፤ ሌሎች ብዙ ደጃዝማቾች ሲኖሩ ከስሜን የሄዱት ደጃዝማች ውቤ ኃይለ ማርያም ትግራይን ብቻ ሳይሆን ባሕረ ነጋሽ ኤርትራን ጭምር እስከ ቀይ ባሕር ያስተዳደሩ መስፍን ነበሩ::

ጎንደር ብዙ ራሶች ወይም ደግሞ ደጃዝማቾች አስተዳድረዋል:: ለምሳሌ ስሜንን ይገዙ የነበሩት ራስ ገብሬ ራስ ኃይለ ማርያም የነራስ ወሌ ብጡል አያት ማለትም የእቴጌ ጣይቱ ብጡል አያት ማለት ሲሆኑ ኋላ ደጃዝማች ውቤ ተተክተዋል:: ራስ ስሑል ሚካኤል፤ ትልቁ ራስ አሊ፤ራስ ወልደ ሥላሴ፤ራስ አሊጋዝ፤ራስ አስራት፤ራስ ወልደ ገብርኤል፤ራስ ጉግሣ፤ራስ ይማም፤ራስ ማርዬ፤ራስ ዶሪ፤ትንሹ ራስ አሊ፤እነዚህ ከዚህ በላይ ስማቸው የተዘረዘረው ራሶች ጎንደር ላይ ግንብ ጠፃቂ አጤ አንግሠው እነሱ ፈላጭ ቆራጭ ሁነው ኑረዋል::

በነዚህ ራሶች ውስጥ ደግሞ ብዙ ደጃዝማቾችና ፊታውራሪዎች ነበሩአቸው:: በጎጃም ራስ ኃይሉ፤ራስ መርድ፤ ሲሆኑ ብዙ ደጃዝማቾች በውስጣቸው ነበሩአቸው:: ደጃዝማች ጎሹ ልጆቻቸው እነ ደጃዝማች ብሩ ሌሎችም ደጃዝማቾች ነበሩ:: በጎጃም ሕዝብ ላይ አጤ ቴዎድሮስ ጨክነውበት ነበር:: በጎጃም ሕዝብ ላይ ምን አጤ ቴዎድሮስ ብቻ አጤ ዮሐንስስ ቢሆን ቤት ሳይሆን ቤተ ክርስቲያን ሳይቀር አፍርሰውበታል::

ወሎን በብዛት የሚገዙት ጎንደር የሚቀመጡት ራሶች ሲሆኑ ባስታን ራስ ወንድ ወሰንና ሌሎችም ሲኖሩ ወደመጨረሻው አካባቢ የአጤ ተክለ ጊዮርጊስ አባት ደጃዝማች ዋግሹም ገብረ መድኅንና ሌሎች

ነበሩ:: በነገራችን ላይ በወሎ የሴት መሳፍንት ነበሩ:: ለምሳሌ ወይዘሮ ወርቂትንና ወይዘሮ መስታይትን ማንሳት ይቻላል:: በሸዋ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን፡ራስ ወሰን ሰገድ፣ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ንጉሥ ኃይለ መለኮትና ሌሎችም ደጃዝማቾችና ፊታውራሪዎች ነበሩ:: እነዚህ ከላይ ጀምሮ እስከ ንጉሥ ኃይለ መለኮት ተከታታይ መሳፍንት ነበሩ::

ሐረር ክፍለ ሀገር ግብጾች የገቡት በዘመነ መሳፍንቱ ወቅት ነው:: መጀመሪያ ሐረር ከከተማው የገባው ባሻ በራኡፍ የሚመራው 1200 ዘመናዊ የታጠቀ ወታደር ሲሆን አትግባ ብሎ የተዋጋው አልነበረም:: ይኸው የቱርክ የግብጽ ጦር ኋላም እንደገና ተጠናክሮ በ1867 ዓም መግባቱ አይዘነጋም:: ግብጾች ይህን ያደረጉት ደግሞ በጉራይ ሽንፈት ከመድረሱ በፊት ዓባይን ለመከበብ ነበር ሕልማቸው::

ፕሮፌሰር ክንፈ አብርሃም <u>የአባይ ጉዳይ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 20"የግብፅ ወታደራዊ ዘመቻዎች መከፈታቸውን ማወቅ ይኖርበታል :: ለምሳሌ ሞሐመድ ዓሊ (1769-1849) የጣና ሐይቅን አካባቢ በመቆጣጠር የግብፅን ደኅንነትና ብልፅግና ለማረጋገጥ ፈልጎ ነበር:: በ1820 ሱዳንን በማሸነፍ መያዙ ግብፅ ዓባይንና የጣናን ሐይቅ ለመቆጣጠር ለነበራት ኢምፔሪያሊስታዊ የመስፋፋት ምኞት እንደመረማመጃ የሚቆጠር ነው" ሲሉ ጽፈዋል::

በዚህ ምክንያት ነበር የአጤ ቴዎድሮስ ታላቅ ወንድም ገፍትረው መደኔ ያደረሱአቸው:: ኋላም ወጣቱ ካሳ ተዋጉአቸው:: ግብጾች ላይ ድል የሆኑት የዓባይን መፍለቂያ ለመያዝ አስበው ነበር የዘመቱት:: ታዲያ በአጤ ቴዎድሮስ የተጀመረው መሠረት በአጤ ተክለ ጊዮርጊስ በኋላም በአጤ ዮሐንስ የተጨመረበት በይበልጥ በአጤ ምኒልክ ጥረት ሐረር ሙሉ በሙሉ ግብሩን ለእርሳቸው ገበረ:: ከዚህ ላይ የአጤ ምኒልክን ተግባቢነት በጥሞና ማየት መልካም ይመስለኛል:: ሐረርን ለማስገበር ሲሄዱ ቅድሚያ ጦር አልከፈቱም:: አስቀድመው የሰላምና የፍቅር ደብዳቤ ታሪካዊነቱን ጠቅሰው ከጻፉ በኋላ ነው::

ጳውሎስ ኞኞ <u>አጤ ምኒልክ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 42 "ቀድሞም ቢሆን ሐረርጌ ከኢትዮጵያ ውጭ ተገዝቶ አያቅውም:: ከኢትዮጵያ



አውራጃዎች አንዱ መሆኑን አንተም በታሪክ ሰምተኸ ይሆናል:: ለአራት መቶ ዓመታት ያህል ያለማቋረጥ ግብሩን ለአያቶቼ ሲገብር ኖርዋል:: አሁንም ነገሩን በሰላምና በወዳጅነት ለመጨረስ ገብርና እንደ አባቶቻችን ወዳጅ እንሁን፥ የሚል ደብዳቤ ለአሚር አብዱላሂ ላኩለት" ሲሉ አቶ ጳውሎስ ኞኞ ጽፈዋል::

አሚር አብዱላሂም ለአጤ ምኒልክ ገብረው አገር ሰፍቶና ተስማምቶ በሰላም እስካለንበት ድረስ ኑረናል:: በዚህ አካባቢ የኦጋዴ ችግር ተሰቦ ሱማሌም በተደጋጋሚ ችግር ፈጠረችበት:: በኢትዮጵያ ሕዝብ ተደቁሳ ብትመለስም የኦጋዴው ችግር ለወደፊቱም ቢሆን ጠላት በር የሚከፍትበት ቦታ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል::

በአፋር ራስ ገዝ ውስጥ ብዙ የማዕረግ ስም ነበራቸው:: አንፋሬ ማለት ደጃዝማች ማለት ሲሆን አንዳንዶም አውሳ ይባሉ ነበር:: እንዲሁም ደግሞ አዳሎች ሡልጣን ተብለው ይጠሩ ነበር:: የሥልጣን ማዕረግ ስም ሲሆን አንዳንዴ የወሎ ራሶች ጠንከር ሲሉባቸው እየገበሩ ደከም ሲሉ ደግሞ ግብር አንከፍልም እያሉ እስከ ቀይ ባሕር አሰብን አልፈው ያስተዳድሩ ነበር::

አውሳዎች፣ አፋሮች ወደ ሸዋም ሆነ ወደ ሐረር እንዲሁ በትግሬም ቢሆን ጉልበታም ሲመጣባቸው እየገበሩ አገራቸውን ሲያስተዳድሩ ኑረዋል:: አፋሮች አልያም ሡልጣኖች ከሌሎች መሳፍንቶች የበለጠ የመሬት ስፋት ነበራቸው:: ያም ማለት የዛሬውን ጅቡቲንም በቁጥጥራቸው ስር አድርገው የሚገዙ ነበሩ:: ይህ ሁሉ ሲሆን ሱልጣኖች ኢትዮጵያን ለመውረር ከውጭ የሚመጣውን ጠላት የሚጋፈጡ ነበሩ::

በአፋሮች ሆነ በሱልጣኖች ወቅት የውጭ ወራሪ ገብቶ አላጠቃም:: በ1862 ዓም ከሱልጣን ኢብራሂም የካቶሊክ ሰላዮች አሰብ ውስጥ የክሰል መጋዘን 12 ጋሻ መሬት የገዙት ካልሆነ በቀር የደፈራቸው አልነበረም:: ይህን ሰነድ መፈረሙን ከሰሙ በኋላ የሙሲጆርን ተከታዮች ባንድቀን ሌሊት መትረዋቸው ያደሩ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን አፋር ናቸው::

ዛሬ ድረስ አፋሮች ኢትዮጵያዊነታቸውን ያልተጠራጠሩ ናቸው:: ወያኔ ኢሕአዴግ" የኤርትራ ዜጎች እንጂ የኢትዮጵያ ዜጎች

አይደላችሁም" እያለ ቢወጋቸውም እነሱ ግን አሜን ብለው አልተቀበሉም:: የሚገርመው ነገር ግን ወያኔ ብቻ ሳይሆን ተቃዋሚ የሚባሉት ድርጅቶች ሳይቀር የአፋርን ሕዝብ እየረሱት የመጡ መሰለኝ::

ከላይ እንደተጠቀሰው የኢትዮጵያን አንድነት ያስደፈረው ዘመነ መሳፍንት በተለያዩ ክፍለ ሀገራት ችግር ማድረሱ ተጠቅሷል:: በአጤ ቴዎድሮስ የተጀመረው የኢትዮጵያ አንድነት መንፈስ ማለትም ከ1845-1983 ዓም ሲገፋ መኖሩ አይዘነጋም:: ለአገሪቱ ለአንድነት ሁሉም መሪዎች ማለት ይቻላል ጥረት አድርገዋል:: ኢትዮጵያ ወደ ዘመነ መሳፍንት አገዛዝ እንድትገባ ያደረጉት ከትግራይ የመጡት ራስ ስሑል ሚካኤል ሲሆኑ ከ1983 ዓም ወዲህ የነተነሡት ኃይሎች ወያኔዎች ልክ እንደ ቅድመ ዓያታቸው ኢትዮጵያን ከፋፍለው በማጥፋት ላይ ይገኛሉ::

አሁንም ዋናው የዚህ መጽሐፍ ዓላማም የአገሪቱ አንድነት ስለተደፈረ ከማንኛውም ጎሳና ከማንኛውም ሃይማኖት ሳይከልለው ልክ እንደ አጤ ቴዎድሮስ ለአንዲት ኢትዮጵያ ብሎ ወንድ እንዲነሣ ጥሪ ለማቅረብና ይህ የዘመነ መሳፍንት ሥርዓት መቅረት እንዳለበት ለማሳሰብ ተብሎ ነው ይህ መጽሐፍ የተጻፈው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ በዘመነ መሳፍንት በጣም ተጎድቷል:: አሁንም እየተጎዳ ነው:: ይህ የሚቀጥለው ምዕራፍ ደግሞ ሊያብራራ የሚሞክረው በዘመነ መሳፍንት ወቅት አገሪቱን ለመከፋፈል ከውጭ መንግሥታት ጋር ያደረጉትን ውል ይሆናል::

## ምዕራፍ 4

### ዘመነ መሳፍንቱ ከውጭ መንግሥታት ጋር!

ለኢትዮጵያ አንድነት ሳይሆን ለግል ጥቅማቸው ሲሉ እነዚህ የመንደር መሳፍንት ከውጭ መንግሥታት ጋር ግንኙነት ፈጠሩ:: በኢትዮጵያ አንድነት ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ሳይሆን ለየራሳቸው ጥቅም ብለው የተነሡ ነበሩ:: አውሮፓውያን በሃይማኖት ሰላዮቻቸው ኢትዮጵያን እያስጠኑ ለመከፋፈል ጥረት ሲያደርጉ አብዛኛዎቹ መኳንንቶች በግል ወዳጅ ለማውጣት ጥረት አድርገዋል::



የውጭ መንግሥታት ደግሞ ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ መኳንንቶችን የሚማርክ ስጦታ ይልኩላቸዋል:: ከሚገርማችሁ ነገር ደግሞ ከአውሮፓ መንግሥታት ለመሳፍንቶች የሚልኩላቸው ሥጋጃ ምጣፍና ሽቶ አልፎ አልፎ ሽጉጥ እንጂ ሌላ አይልኩላቸውም ነበር:: ቅድሚያ ከውጭ መንግሥታት ጋር ግንኙነት ያደረጉት መሳፍንቶች መካከል የትግራዩ::

ራስ ወልደ ሥላሴ ናቸው:: እርሳቸው ከብዙ የውጭ አገር ሰዎች ጋር ግንኙነት ነበራቸው:: ነገር ግን የተዋዋሉት ሰነድ የለም:: ሌሎችም የትግራይ መሳፍንት ቢሆኑ ለሥልጣን መሮጥ እንጂ በዚህ በዘመነ መሳፍንቱ ወቅት ከውጭ አገር ሰዎች ጋር ግንኙነት የነበራቸው መሆኑ ደብዳቤያቸው ዋቢ ስለሆነ ግንኙነት ማድረጋቸውን እንጂ የተዋዋሉት ውል የለም::

የሸዋ መሳፍንት ከእንግሊዝና ከፈረንሳይ መንግሥታት ጋር የተዋዋሉት ውል አለ:: እንዲያውም በጥሞና ለመረመረው የሸዋው መሳፍንት ውስብስብ ውል ተዋዋሉ:: በእርግጥ አንድ የሚያስመሰግናቸው ነገር ቢኖር በኢየሩሳሌም ያለውን የዴር ሡልጣን ገዳም አስመልክቶ ያደረጉት ውይይት ሊመሰገን የሚገባ ነው:: ነገር ግን ከዚህ በፊት የአንድ ክፍለ ሀገር መስፍን ከውጭ አገር መንግሥት ጋር ተዋውሎ አያውቅም::

<u>ንቃ ጋዜጣ</u> ኅዳር 26 ቀን 1988 ዓም ገጽ 5 "በሻለቃ ደብልዩሲ ሀሪስን የተመራ ቡድን የሸዋ ንጉሥ በነበረው ሣህለ ሥላሴ ጋር የወዳጅነትና የንግድ ስምምነት እንዲዋዋል በታጁራና በአፋር አገር በኩል ወደ ኢትዮጵያ ልኮ ነበር:: ዐሪሰንም የሣህለ ሥላሴ መናገሻ ከሆነችው ወደ ነበረችው አንኮበር መጥቶ ኢትዮጵያ ለንግድ ልታቀርባቸው የምትችለውን የንግድ ዓይነቶችና ማዕድናት (ወርቅ የዝሆን ጥርስ ዝባድ፤ቆዳ፤ሰም::"

"ውድ ሙጫ ዝንጅብል፤መዳብ የተፈጥሮ ቡና)ከማጥናቱም በላይ በኢትዮጵያም ውስጥ ተፈላጊነት ያላቸው የውጭ ሸቀጦችንም ዓይነት በዝርዝር አጥንቶአል" ሲል ጋዜጣው ጽፎአል:: ይህ ከሆነ በኋላ የሸዋ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር ሕዳር 10

ቀን 1834 ዓም የተፈራረሙትን ውል አስመልክቶ አቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ አጠር ባለ መልኩ እንዲህ ሲሉ ዘግበውታል::

ከዐጼ ልብነ ድንግል እስከ አጤ ቴዎድሮስ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 367 "የውሉ አሳብ" ይሉና ሲያብራሩ "ካ1-3 ያለው አንቀጽ-የሁለቱ አገሮች ነገሥታት ወይም የነገሥታቱ መልክተኞች የሚወዳጁበትንና በክብር የሚቀበሉበትን አሳብ ይገልጻል:: ካ4-13 ድረስ ያለው አንቀጽ የሁለቱ አገር ነጋዴዎች ከብትና ሌላም ሸቀጥ አንደኛው ባንደኛው አገር እየተለዋወጠ እንዲነግድ የንግዱም ቀረጥ በመቶ አምስት ሆኖ ይኸንኑ በገንዘብ ወይም በከብት ብቻ እንዲከፍልና ከዚያ ወዲያ እንደ ልቡ እየተዘዋወረ ሲነግድ የሁለቱም አገር ነገሥታት በማናቸውም እንዲደግፉትና የነጋዴዎቹን ችግር ለማቃለል የሚቻለውን እንዲያደርጉ ከባሕር አንሥቶ እስከ ማኸል ሸዋ ድረስ መንገድ እንዲከፍቱ የሚገልጽ ነው::"

"ካ14-15 ያለው አንቀጽ የሁለቱ አገር ሰዎች ለንግድ ሳይሆን ለግላቸው ባመጡት ዕቃ ቀረጥ እንዳይጠየቁ የሁለቱ አገር ሕዝቦች ከሸዋ ወደ እንግሊዝ አገር ወደ ሸዋ ቢመጡ ካውራጃ ወደአውራጃ እንደ ልባቸው እየተዘዋወሩ ሲቀመጡ ማናቸውንም በመካከላቸው ጠብና ቂም የሚፈጥረውን ነገር እያስወገዱ በፍቅር ዐይን እየተያዩ እየተደጋገፉ እንዲኖሩ የሚያስጠነቅቅና የሚያስገድድ ነው" ሲሉ ከጻፉ በኋላ የሸዋውንና የፈረንሳዩን ውል በሚመለከት ሲያትቱ ይህን ብለዋል::

"ካ1-3 ያለው አንቀጽ ስለ ሃይማኖት መቃረብ በሸዋ ላይ የሚነሣው ጠላት በፈረንሳይ ዘንድ የተጠላ እንደሚሆን ኢየሩሳሌም በፈረንሳይ ጥላ ውስጥ የምትተዳደር በመሆኗ የሸዋ ሰዎች ኢየሩሳሌም በሄዱ ጊዜ በኢየሩሳሌም ያሉት የፈረንሳይ ሹማምቶች በመልካም እንዲጠብቋቸው እንዲሁም ፈረንሳዮች በሸዋ ሲኖሩ ከሌላው የውጭ አገር ሰው የከፍታ መብት እንዲያገኙ ያረጋግጣል:: ካ4-5 ያለው አንቀጽ የፈረንሳይ ተወላጅ በሸዋ እንደ ልቡ እየተዘዋወረ ሲነግድ ቀረጥ ከመቶ ሶስት መሆኑን ያረጋግጣል::"

"6ኛው አንቀጽ የፈረንሳይ ተወላጅ ቤትም ምድርም በሸዋ ሲገዛ የገዛውንም ቢሸጥ ቢለውጥ ችግር እንዳያገኘው ንጉሡ እንደሚጠብቀት ይናገራል:: 7ኛው አንቀጽ ስለ ውሉ ግልባጭ



መለዋወጥ ብቻ ይናገራል:: በውሉ ግርጌም እንዲሁ እንደ ተለመደው የሙሴ ሮሼ ፊርማና የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ማኅተም ተደርጓል:: ከካፒቴን ሐሪስም ከሙሴ ሮሼም በተዋዋሉት ሰሌዳ በአርእስቱ መካከል የሦስቱ ሥላሴ በቀኝ የአንበሳ በግራ የርግብ ሥዕል አለበት" ሲሉ ጽፈዋል::

የእንግሊዝና የፈረንሳይ መንግሥታት ከንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ጋር ያደረጉት ውል ዋናው የሁለቱ SVEN RUBENSON ACTA ETHIOPICA VOLUM 1 CORREPONDENCE AND TRETIES 1800-1854 በተባለው መጽሐፍ ገጽ 58 እና 59 መካከል ሲኖር የፈረንሳይና የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ውል ደግሞ ከዚሁ መጽሐፍ ገጽ 82 እና 83 መካከል ይገኛል:: የዚህን ውል ሙሉ በሙሉ በአማርኛ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ጽፈውታል::

ብላቴ ጌታን ኅሩይ ወልደሥላሴ የኢትዮጵያ ታሪክ ከንግሥተ ሳባ እስከ ታላቁ የአድዋ ድል በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 77-81 የእንግሊዝንና የሸዋ መሳፍንት የተዋዋሉበትን ሙሉውን አውጥተውታል:: በተለይም የእንግሊዝ መንግሥታት ከሸዋ መሳፍንት ጋር ያደረጉትን ውል ጎንደር ደብረታቦር ላይ ከራስ አሊ አሉላ ጋርም አድርገውታል::

የሁለቱ መሳፍንት ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር ያደረጉት ውል ተመሳሳይ ሲሆን ውሉ ከላይ እንደጠቀስኩት አንድ አይነት ነው:: ሸዋና ጎንደር መሳፍንት ከእንግሊዝ ሆነ ከፈረንሳይ መንግሥት ጋር የተደረገውን ውል በአባሪ ቁጥር አንድ ይመልከቱ::

የጎንደሩ መሳፍን እንዲሁ በ1842 ዓም ራስ አሊ አሉላ ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር የንግድና የወዳጅነት ውል ተዋዋሉ:: ራስ አሊ አሉላ፤ ቀደም ሲል የሸዋ መሳፍንት ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር ሲዋዋሉ ያነሡት ጥያቄ በኢየሩሳሌም ያለው የዴር ሡልጣን ገዳም ጉዳይ አንዱ እንደነበር ኋላም ራስ አሊ አሉላ ማንሣታቸው ተጠቅሶአል::

ምንም እንኳን የእንግሊዝ መንግሥት ጀምሮት የነበረውን መነኮሳቱን መርዳት ግብጾች ለጌታቸው ለቱርክ መንግሥት አመልክተው ቱርኮች ደግሞ ለእንግሊዝ መንግሥት የሰጠው መመሪያ "ሁለተኛ

የዴር ሡልጣንን ገዳም ለኢትዮጵያውያን ይመለስ አትበሉ" ተብለው ከተነገራቸው በኋላ እንግሊዞች ቀደም ከሸዋ መሳፍንትና ኋላም ከጎንደር መሳፍንት ጋር ለመቀራረብ ያደረጉትን ውል ሲሽሩት ታይተዋል። በዚህ በዴር ሡልጣን ገዳም ጉዳይ ጎንደር ላይ ጉባኤ ተደርጎ የተጠየቀ መሆኑን ሌላም የታሪክ መጽሐፍ ዘግቦታል።

ተፈራ ኃይለ ሥላሴ አምባሳደር ኢትዮጵያና ታላቋ ብሪታኒያ የዲፕሎማሲ ታሪክ ከ1778-1967 ዓም በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 21 "የጎንደሩ ራስ አሊና ደጃዝማች ውቤ የይስሙላው ንጉሠ ነገሥት ሣህለ ድንግል፤መሳፍንቱ መኳንንቱና የቤተክርስቲያን መሪዎች በተገኙበት ጎንደር ቤተ መንግሥት መክረው ለንግሥት ቪክቶርያ ይዘታቸው አንድ ዓይነት የሆነ ደብዳቤዎች ጽፈው በቆንስል ፕላውዲን በኩል ለመላክ ተስማሙ።"

"ሁለቱ ኃያላን ገዥዎች ለንግሥት ቪክቶርያ በጻፏቸው ሁለቱ አንድ ዓይነት ደብዳቤዎች፤የዴር ሡልጣንን ንብረት እንዲያስመልሱላቸው ይጠይቃሉ" ይሉና ይህ ደብዳቤ እንግሊዝ አገር ከደረሰ በኋላ ሁለተኛ ጊዜ በእንግሊዝ መንግሥት በኩል አቡነ ሳሙኤል ጎባት ኢትዮጵያውያንን እንዲረዳ ታዞ ሥራ መጀመሩን አስመልክቶ ሲያክሉ እንዲህ ይላሉ" ቆንስሉም ከኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን አቡነ ሳሙኤል ጎባት ጋር በመተባበር ንብረቱን ለኢትዮጵያውያን ምእመናን ለማስመለስና የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን መብት ለማስከበር ጥሯል" ሲሉ ጽፈዋል።

እንግሊዞች ይህን የመሰለ የወዳጅነትና የቃል ማክበር ተግባር ለኢትዮጵያ መፈጸም ሲጀምሩ ግብጾች ደግሞ ለጌታቸው ለቱርክ "አቤት" አሉ። ገዳሙን ለማስመለስ ጥረት ማድረጋቸው ካልሆነ በቀር በሌላ በኩል ለአገር አንድነት ያደረጉት ተግባር አልነበረም። ይህን ካልኩኝ በኋላ ደግሞ የዘመነ መሳፍንትን አገዛዝና የዛሬውን አገዛዝ በጥሞና አስተውሉት።

ዘመነ መሳፍንት ለአገር አንድነት ሳይሆን ለሥልጣን ስግብግብነት የአገርን ጥቅም የሚጎዳ ውል መዋዋላቸውን ያብራራል። የዛሬው የኢትዮጵያ መንግሥት ደግሞ ከዘመነ መሳፍንት የማይሻል የአገሩን ጥቅም አሳልፎ የሰጠ የአገር ክብር የማይሰማው ብቻ ሳይሆን አገሪቱን ያለ ባሕር በር ያስቀረ መንግሥት ነው።



አገሪቱ ለወደፊቱ ለውጭ ወራሪ የተጋለጠች ከመሆንዋም በላይ ለስምንት የውጭ አገር የስላይና የሃይማኖት ድርጅቶች እንጁን የሰጠ መንግሥት ነው። ይህ መንግሥት የአገር አንድነት ሊያስጠብቅ ሳይሆን የመጣው የአገርን አንድነት ሊያስደፍር የመጣ መሆኑ መታወቅ አለበት። ይህ መንግሥት ሙሉ በሙሉ ለውጭ መንግሥታት እጁን የሰጠ በመሆኑ ለወደፊቱ አገራችንን ሊያጠፉ የተነሣ ነው። ስለዚህ አገር ወዳድና ቅን ምሁራን ሆነ ማንኛውም ዜጋ መሬቱ እንዳይሸጥበት ጠንክሮ መከራከር ይገባዋል።

## ምዕራፍ 5

## የኢትዮጵያ ሕዝብ እንባ ፈስሶ አልቀረም!

ትንቢተ ኤር 22፣3 "ፍርድንና ጽድቅን አድርጉ፤የተበዘበዘውንም ከአስጨናቂዎች እጅ አድኑ" ይላል። የኢትዮጵያ ሕዝብ በመዘነ መሳፍንት አዝኖ ስለነበር ደማቸውን የሚመልስ ቴዎድሮስን አወረደባቸው። ይህን ስል ከታችም እንደምጠቅሰው አጤ ቴዎድሮስ የሰው ደም አላፈሰሱም ማለቴ ሳይሆን እርሳቸው ከመንገሣቸው በፊት የፈሰሰውን ደም ግን ተበቅለዋል።

ወደ ሮሜ ሰዎች 1፣18 "እውነትን በዓመፃ በሚከለክሉ ሰዎች በኃጢአተኝነታቸውና በዓመፃቸው ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ከሰማይ ይገለጣልና" ይላል። ዘመነ መሳፍንት እግዚአብሔርንና የኢትዮጵያን ሕዝብ አስቀይሟል።

ፈርዖን እስራኤላውያንን በባርነት ቀንበር በመቅጣቱ ምክንያት ተናዳፊ እባብ እንደላከበት ቅዱስ መጽሐፍ ይነግረናል። የዘመነ መሳፍንት ሥርዓት ደግሞ የኢትዮጵያን ሕዝብ በመቅጣቱ ምክንያት ዘመነ መሳፍንትን የሚቀጣ አጤ ቴዎድሮስን ላከባቸው። ዘመነ መሣፍንት የኢትዮጵያን ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ልዑል እግዚአብሔርን አስቀይሟል። ቃልቻና ጠንቋይ በሀገሪቱ ተስፋፍቶ ነበር። ደብተራና ጋኔን ሳቢ ሳይቀር በዝቶና ችግር እየፈጠረ ነበር።

መኃ 2፤11 "እነሆ ክረምት አለፈ፤ዝናቡም አልፎ ሄደ፤አበቦች በምድር ላይ ተገለጡ፤የዜማም ጊዜ ደረሰ፤የቁርዬውም ቃል በምድራችን ተሰማ፤በለሱ ጎመራ ወይኖችም አበቡ መዐዛቸውንም ሰጡ" ይላል። ዘመነ መሳፍንትን አጤ ቴዎድሮስ ቀጥቅጠው የእግዚአብሔር መንግሥት እንዲከበር አድርገዋል። ዋልጌና ሰነፍ ተቀጥቶ ገበሬው አርሶ እንዲበላ ነጋዴውም ነግዶ እንዲገባ ሕግና ሥርዓት ደነገጉ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በዘመነ መሳፍንቱ እጅግ ብዙ ዓመት እንባውን አፍሶአል። የአገሩ አንድነት ሲናድ አዝኗል። እግዚአብሔር ግን የፈሰሰውን እንባ አስቦ እነሆ ከዚህ የሚቀጥለውን ክፍል እንደምናነበው ልጅ ካሣ ኃይሉን የኋላው ደጃዝማች ካሣን አገርን አንድ ለማድረግ የፈሰሰውን እንባ ለመጥረግ አመጣቸው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ እንባውን አፍሶ ለእግዚአብሔር ተናግሮአል። ለዚህም ወደፊት እንደሚነበበው ደም ያፈሰሱ መኳንንቶች የእነሱን ደም የሚያፈስ ጣለባቸው። የኢትዮጵያ ሕዝብ እምነት ያለው ሕዝብ ነው፡ በግራቀኙ አማኝ ሕዝብ ነው። በክርስትና ሃይማኖት ታሪክ ለሚመረምር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲወለድ የእጅ መንሻ የሰጡት ሰብአ ሰገል ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን በተመለከተ ከዚህ በፊት ብዛት ያላቸው ኢትዮጵያውያን ጽፈዋል። እኔም ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ታሪክ በመጥቀስ መጻፌን አስታውሳለሁ።

አማረ አፈለ ብሻው <u>ኢትዮጵያ የሰው ዘር የተገኘባት የእምነትና የሥልጣኔ ምንጭ ናት</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 128 "ኢትዮጵያውያን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚወለድ ይጠባበቁ ስለነበር መወለዱን ሲያውቁ ከርቤ፤ወርቅና ዕጣን አበርክተው ሰግደውለታል። ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሱ ጀምሮ የዓለም ንጉሥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መወለዱን ለኢትዮጵያ ሕዝብ አብስረዋል" ስል ጽፌ ነበር።

ከፍ ተብሎ በተጠቀሰው መጽሐፍ ሆነ በሌሎች ባሳተምኩአቸው መጻሕፍት ታሪክ እየጠቀስኩኝ መጻፌን አስታውሳለሁ። ገና ቀደም ብሎ ኢትዮጵያውያን ጌታችን እንደሚወለድ ያውቁ ነበር። ይህንም ሀሰት እንዳንለው መዝሙረ ዳዊት 72፤9 "በፊቱም ኢትዮጵያውያን ይሰግዳሉ"ብሎ ጽፎት ይገኛል።



ገብረ ዮሐንስ ገብረ ማርያም <u>ክርስትና በኢትዮጵያ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 52 "ጌታ በቤተ ልሔም በተወለደ ጊዜ ከምሥራቅ መምጣታቸው በሐዲስ ኪዳን የተነገረላቸው ሰብአ ሰገል ከኢትዮጵያ እንደሄዱ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት በትውፊት አባባላቸው ይተርካሉ" ሲሉ ጽፈዋል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኢትዮጵያ መጥቶ አስተምሯል። ይህም በመዝሙረ ዳዊት 67፤31 "የሰላም መልዕክተኞች ከግብጽ ይመጣሉ፤ ኢትዮጵያም እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች" ተብሎአል።

መራሪስ ኤም አማን በላይ <u>ጉግሣ መጽሔት</u> ቅጽ 2 ቁጥር 3 መጋቢት 1993 ዓም ገጽ 17 "የማርቆስ አክስት ማለት የበርናባስና የአርስጦል እኅት ጴጥሮስን አግብታ ነበር። እንዲሁም ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ የቤተ እስራኤል የሌዊና የይሁዳ ነገድ የሆነ ስሙም ስምዖን የሚባል ሰው ወደ ቀሬና ወደ ቤተ መቅደስ ሊሰግድ መጥቶ ነበር። በበነጋታው ከአባቱና ከእናቱ ዘመድ ከስምዖን ጋር ማርቆስ የጌታችንን የክርስቶስን ግርፋትና ሕማማቱን እየተከተለ ተመልክቷል። አጎቱንም የአባቱን ዘመድ ኢትዮጵያዊ ስምዖን የተባለ የቀሬና ሰው የጌታን መስቀል እንዲሸከም አይሁድ ሲያስገድዱት አይቷል" ሲሉ ጽፈዋል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበትን መስቀል የተሸከመው ስምዖን ኢትዮጵያዊ ነው። ይህን እኛ ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳንሆን ሌሎችም የውጭ አገር ሰዎች ጽፈውታል።

Mark Hyman <u>Blacks Who Died For JESUS</u> በተባለው መጽሐፋቸው page 3 " The fact the Simon traveled from the Black land of Cyrene to be with Jesus on this day explains the presence of dynamic movement. Historically" ሲሉ ጽፈዋል። ስለዚህ ስምዖን ኢትዮጵያዊ እንጅ የሌላ የአፍሪካ አገር ሰው አይደለም። ይህን ካልኩኝ በኋላ ወደ ምዕራፉ መነሻ ልመለስ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አማኝ በመሆኑ ለእግዚአብሔር መበደሉን ገልጿል። እነሱን የሚቀጣ ኃይለኛ ሰው እግዚአብሔር የጣለባቸው መሆናቸውን ራሳቸው የመሳፍንቱ ቁንጮ ራስ አሊ አሉላ "ይህን ሰው አንችለውም እግዚአብሔር እኛን ሊቀጣ ያመጣው ነው፤

እርሰዎም ወደ አገርዎት ይመለሱ” በማለት ለንጉሥ ኃይለ መለኮት መክረዋል::

ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ብቻ ሳይሆኑ ኦሪታውያንና እስላሞችም ጸልየዋል ለዓለም እስልምና ሃይማኖትም ኢትዮጵያውያን ተዋግተዋል:: ለዚህም ሌላው የታሪክ መጻሕፍትን መጥቀስ ብቻ ሳይሆን ቅዱስ ቁርአን ዋቢ ነው:: ቅዱስ ቁርአን መቅድም ላይ እንዲህ ይላል::

ቅዱስ ቁርአን “ነቢዩ ሙሐመድም ለተከታዮቻቸው ሐበሾችን (ኢትዮጵያውያኖችን) ካልወጉዋችሁ አትውጉዋቸው ማለታቸው ይነገራል:: ንጉሡም ድርብ ምንዳ ያለው ጻድቅ ንጉሥ መኾኑ በቁርአን በ3ም 199:አንቀጽ 28.52.54.አንቀጽ ተገልጿል” ሲል ጽፏል:: በእስልምና ሃይማኖት በዓመት አንድ ቀን ለኢትዮጵያዊው የአጋሜ አውራጃ ንጉሥ አርማህ ይጸለያል:: እስልምና ሃይማኖት መሥራቹን ነቢዩ ሙሐመድን ጡት አጥብተው ያሳደጉ እሙሐዓይመን አል አሕበሽ አልያም ደግሞ በረከቱል አልአበሽ የተባሉት ኢትዮጵያዊ ናቸው::

ሐጂ ሙሐመድ ሣኒ ሐቢብ እስልምና እና የታላቁ ነቢይ የሙሐመድ ታሪክ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 46-56 ድረስ ጽፈውታል:: ለግንዛቤ ያክል ከተጠቀሰው መጽሐፍ ገጽ 53 “የዚህ ንጉሥ ቀብር በትግራይ ጠቅላይ ግዛት በአጋሜ ቀበሌ ይገኛል:: በየዓመቱ ሙሐረም ዐሥር ቀን ላይ (ቡንሹር) መታሰቢያ ይደረግለታል” በማለት ጽፈዋል:: ይህ ማለት ኢትዮጵያ ስደተኞችን ማስተናገድ የቻለች አገር ስትሆን ከኦሪትና ከክርስትና ሃይማኖት ጎን ለጎን ለእስልምና ሃይማኖት ስደተኞች ረዳት መሆንዋን የሚያብራራ ነው::

ዶ/ር ዐብዱረህማን ረአፈት አልበሻ ሐያቱ ሶሐባ የነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ)ባልደረባዎች አጭር የሕይወት ታሪክ በተባለው መጽሐፍ ገጽ 84 “ስደተኞቹ በሰላም መኖር የእግር እሳት የሆነባቸው የቀረይሽ ባለሥልጣኖች ወደ መካ የሚመልሱባቸውን መንገድ ያውጠነጥኑ ጀመር” ሲሉ ጽፈዋል::

የቀረይሽ ሰዎች ብዙ ወርቅ አሲዘው ወደ ኢትዮጵያ ሲልኩ የአክሱም ንጉሠ ነገሥት አጤ አድርአዝ ከ595-615 ዓም ለነገሡት ነው ደብዳቤ የተላከው ሲሉ ሌሎች ደግሞ ለንጉሠ ነግሥት አጤ አካለ ውድም ከ615-623 ዓም ለነገሡት ነው ነቢዩ ሙሐመድ ደብዳቤ የላኩት ሲሉ አብዛኛው የታሪክ ሰነድ የሚለው ግን ለኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቀጥታ ሳይሆን ለአጋሜ አውራጃ ንጉሥ ለአርማህ ነው ይላሉ:: በእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች የታሪክ ትንታኔ መሠረት ንጉሥ አርማህ ሰልመዋል ይላሉ:: እኔ ግን የአጋሜ አውራጃ ንጉሥ አርማህ አልሰለሙም ነገር ግን ስደተኞችን በሥርዓት አስተናግደዋል የሚል አቅዋም አለኝ::



ዶ/ር አስፋወሰን አስራተ ካሳ ሩሕ መጽሔት ግንቦትና ሰኔ 1985 ዓም ገጽ 10 “የነቢዩ መሀመድም ትእዛዝ መፈጸም አለበት ባይ ነኝ:: በእስላሞች ዘንድ በዛን ጊዜ ኢትዮጵያ የመጀመሪያዎቹን የእስላም ስደተኞች በመቀበል በቁርአኑም እንደተጻፈው ኢትዮጵያውያንን በምንም አይነት አትንኳት ብለው ነቢዩ ሙመድ ተናግረዋል:: ስለዚህ ለማንም እስላማዊ ሰው ኢትዮጵያ ጋራ መፋቀር የመጀመሪያው በነቢዩም የተደነገገ ሕግ መሆኑን ማወቅ ስላለብን ይሂንን እንግፋበት:: የሰላማዊ የወንድማማችነት አኗኗራችንን እንቀጥልበት” ሲሉ ጽፈዋል::

በትክክል መደረግም ያለበት ይህ ነበር:: ነገር ግን ዛሬ ብዙ ችግሮች እየመጡባት ነው:: ስለዚህ ታሪክን በታሪክነቱ ተቀብለን ኅብረታችንን ማጠንከርና ለወደፊቱ ልዩነት የሚፈጥሩትን ሁኔታዎች ለማስወገድ በክርስቲያኑ በኩል ብቻ ሳይሆን መገፋት ያለበት ልክ እንደ ሊቅ ዶ/ር አሕመድ ሙን ዓይነት ወንድሞቻችን ታሪካችንን ልንክንባከበው ይገባል::

ወደነበርኩበት ልመለስና ይህ የጋራ ታሪካችን በታሪክነቱ መታየት ይኖርበታል እላለሁ:: ለክርስትናችን አውሮፓውያን ምስክር ሊሆኑ አይችሉም፤ ለእስላምናችንም የዓረብ አገር ተወላጆች ምስክር ሊሆኑ አይችሉም:: ኢትዮጵያውያን በዘርና በሃይማኖት የተለያየንበት ወቅት ፈጽሞ የለም:: ስለዚህ ለእስልምና ሃይማኖት ከዓለም በፊት ኢትዮጵያውያን የተዋደቁ መሆናቸውን ታሪክ ይመሰክራል:: ምክንያቱም በላይ ገብረ እግዚአብሔርን ኢትዮጵያውያን እስላሞች ሊክዱት አይችሉምና ነው:: በላይ ገብረ እግዚአብሔር የትግራይ ልጅ ኢትዮጵያዊ ነውና::

ሰፍዩ ረህማን አልሙባረክፑረ ረውልደቱል አንዋር የነቢዩ መሐመድ (ሰዐወ)የሕይወት ታሪክ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 133 “ለቢላል ጥሩ ድምፅ ስላለው ለቢላል አዛኑን እንዲነግረው አዘዙት:: ለቢላል ተነገረውና ቢላል አዛን አደረገ” ሲሉ ጽፈዋል:: በእስልምና ሃይማኖት ለጸሎት ተነሡ ብሎ በመጀመሪያ ጥሪ ያደረገውን ሰው እስላሞች ቢላል የሚሉት በላይ ገብረ እግዚአብሔር የተባለውን ኢትዮጵያዊ ነው:: ከዚህ በላይ ያሉትን ሆነ ከዚህ በታች ያሉትን የሃይማኖትና የታሪክ መጻሕፍት የምዘረዝራቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያምነው አምላክ ስላለ ለማብራራት ነው::

ዶ/ር መጂድ አሊ ካን ሦስተኛው ኸሊፋ ዑስማን ዐፉን (ረ.ዐ) በተባለው መጣጥፋቸው ገጽ 9 “መካ ውስጥ ሕይወት በጣም አስቸጋሪ እየሆነች በመጣችበት ጊዜ ሃድረት ዑስማን )ረ.ዐ) ከሌሎች ሙስሊሞች ጋር በሐበሻ (አብሲንያ)ውስጥ በጥገኝነት መኖር” ሲሉ ሰፋ አድርገው ዘርዝረው ጽፈዋል::

አንባብያን ኢትዮጵያውያን አንድ የምንኮራበት ታሪክ አለን:: ያም በዓለም ላይ ቅድሚያ የስደተኞችን መብት ያከበረች ኢትዮጵያ በመሆንዋ ነው:: ያውም በሃይማኖት ተሰደው የመጡትን እምነታቸውን ሳትጋፋ ነጻነታቸውን አስከብረው እንዲኖሩ ያደረገች አገር በመሆንዋ ዛሬ ክርስቲያኑ ሆነ እስላሙ፤አሪታዊው ሆነ የሕገ ልቦናው አማኝ ሁሉም ሊኮራበት ይችላል::

ምናልባት አንዳንድ አንባብያን ግራ እንዳይጋቡ ለማብራራት “ሕገ ልቦና”ማለት ከአሪት መግባት በፊት የኢትዮጵያ ሕዝብ ያመልከው የነበረ ሃይማኖት ሲሆን ዛሬም በጎንደር ክፍለ ሀገር በጎንደር ዙሪያ አውራጃ እና በጭልጋ አውራጃ የሚገኙት ቅማንቶች ጥቂቶች የሕገ ልቦና አማኝ ናቸው:: በሌሎችም አካባቢዎች የተለያዩ አምልኮቶች ያሉ ሲሆን ሁሉም እግዚአብሔር መኖሩን የሚያበስር ሃይማኖት ነው:: መሳፍንቶች እንኳን ለሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሊያዝኑና ሊራሩ ቀርቶ ከአባታቸው ቅምጥ ሳይቀር የወለዱ ነበሩ:: ለምሳሌ የሸዋ መሳፍንት አመሠራረት እንዴት እንደሆነ ክቡር አቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ከጻፉት ታሪክ ጥቅስ ልውሰድ::

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ከአጤ ልብነ ድንግል እስከ አጤ ቴዎድሮስ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 359 “ከጎንደር መጥተው በመንዝ



አውራጃ የሚቀመጡ በወዛን አውራጃ የሚቀመጡ ቤዛነ ወልዱ የሚባሉ የቅኔና የመጻሕፍት ሊቅ ነበሩ:: የርሳቸውም የሊቅነት ዝና እስከ አምኃየስ ጆሮ ደርሶ ተሰምቶ ነበርና አምኃየስ ልጃቸውን አስፋ ወሰንን ቅኔ እንዲማሩ ካራት አሽከሮች ጋር ወደ ቤዛነ ወልዱ ላኳቸው:: አስፋ ወሰን መንዝ ሄደው ከኝሁ መምህር ቅኔ ተምረው ካስመረቁ በኋላ ከመንዝ ተነሥተው ወደ አንኮበር ለመምጣት ወደራ (የጎላ ወደራ ማርያም አይደለም) ላይ ሲደርሱ ጊዜ መሸባቸውና የአምኃየስ ቁባት በሆኑት በወይዘሮ አትሞች ቤት አሳድሩኝ ብለው አደሩ::”

“በዚያም ሳሉ አስፋ ወሰን የአምኃየስ ልጅ መሆናቸውን ሴትዮዋም የአምኃየስ ቁባት መሆናቸውን ሳይገላለጡ በሌላውም ወገን የአስፋ ወሰን የወጣትነት ጊዜና የመልካቸው ቁንጅና ለወይዘሮዬቱ ደስ ስላሰኛቸው የአስፋ ወሰንን ጓደኞች እሌላ ቤት አሳድረው ወይዘሮ አትሞችና ወጣት አስፋ ወሰን ባንድነት አደሩ:: በዚህ ባንድ ሌሊት ግንኙነት ሴትዮዋ ፀንሰው በኋላ ወሰን ሰገድን ወለዱ” ሲሉ ጽፈዋል::

ክቡር አቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ስህተቱን በሴትዮይቱ ለማስመሰል ሞክረዋል:: መልሰው ደግሞ አስፋ ወሰን ያወቁ መሆናቸውን አስመልክቶ ገጽ 359 “አስፋ ወሰን የሠሩትን ሥራ ስለሚያውቁትና ሴትዮዋም ያባታቸው ቁባት መሆናቸውን ስለ ስሙ አባታቸውን ፈርተው ካንኮበር ሸሽተው እንደ መነኩሴ ቆብ ደፍተው ዳባ ደርበው ፍርኩታ ገዳም ገቡ” ሲሉ ጽፈዋል:: ያም ሆነ ይህ አስፋ ወሰን ከአባታቸው እቁባት ወሰን ሰገድን ወልደዋል:: የወሰን ሰገድ ትውልድ ከቀዳማዊ አጤ ኃይለ ሥላሴ ድረስ ዘሩን የሚቆጥረው ትውልድ ነው:: ከአባቱ እቁባት መውለድ ብቻ ሳይሆን አልግባባ በማለታቸው አባትና ልጁም ተዋግተዋል::

የሸዋን መሳፍንት ከላይ በተጠቀሰው ጥቅስ አልፈን ከጎጃም መሳፍንት ስንደርስ ደግሞ በጣም አሳዛኝ የሆነ የግብር ሥርዓት ተጽፎ ይገኛል:: መሳፍንቶች ተደርጎ የማያውቅ ግብር ከሕዝቡ የሰበሰቡ ናቸው:: ዛሬ ይህ ይደረግ ነበር ተብሎ ሲጻፉ ለማመን የሚያስቸግር ተግባር ሲፈጸም ነበር:: ከዚህ በፊት ማንም ነገሥታት አልያም ደግሞ መሳፍንት አድርጎት አያውቅም:: ደጃዝማች ብሩ ጎሹ በጎጃም ሕዝብ ላይ ጥለውት የነበረው ግብር ይህን ይመስላል::

አለቃ ተክለ ኢየሱስ የኢትዮጵያ ታሪክ ሐተታ በተባለው መጽሐፋቸው 98 “ደጃዝማች ብሩ ጉልበት ተሰምቶት ትዕቢት

ተጭኖት በጎጃም ላይ ዳሞትን ደርቦ ሲገዛ አባቱን ደጃች ጎሹን ልቀቅልኝ ዝም ብለህ ተቀመጥ አለና በደገሞና በማቻክል በፌጠጅኝ ሹም ሽር አደረገ። ኤልያስንና ደልማ አማኑኤልን ደበረ። የዚህ ጊዜ አባትና ልጅ ለገላጋይ አስቸገሩ። መኳንንቱም ቢጨንቃቸው እርስዎ ይሸነፉ ጉልበቱ እንደመራው ይያዝ አሉ።"

"ደጃች ጎሹም እርስዎ አልል። ጋሻ አንግቤም አንተ አልል። ያሰበውን ያድርግ ሰው ካልሳቀበት አለ። ከዚህ በኋላ ለጦርነት ተዘጋጁ። ያን ጊዜ የየብራጌው ፊታውራሪ ፊልፊሉ የደጃች ጎሹ መካሪ ነበረ። እንበለው ይህን ዲቃላ ክንዱን ነጥቄ አምጥቼ ሰለባ እሰጥሃለሁ አለና ፎከረ። አንጋጣ ከሚባለው ሜዳ ላይ ገጥመው ደጃች ጎሹ ድል ሆነ" ሲሉ ጽፈዋል። ይህ በአባትና በልጁ መካከል የተደረገውን ጦርነት ሲሆን ደጃዝማች ብሩ ጎሹ በጎጃም ሕዝብ ላይ ያደረጉት ቀረጥ ደግሞ እንዲህ ሲሉ ይገልጹታል።

ከፍ ተብሎ ከተጠቀሰው መጽሐፍ ገጽ 118 "በደረቤ በየወረዳው 10/10 እንሥራ ጉንዳን ለምስጥ ማጥፊያ ብሎ ደሃውን አስጨንቆት ነበረ። ያንን ጊዜ ባላገር ጉንዳን በሣምባ ሥጋ እየሰበሰበ በእንስራ ውስጥ እየከተተ ወደ ሶማ አምባ ሲወስድ ጆሮውን እየነከሰ አስቸገረው። የዚህ ጊዜ በለቅሶ ሲአንጎራጉር እንዲህ አለ።
ከመከራው ሁሉ የጉንዳኑ ባሰ
የተሸካሚውን ጆሮና ትክሻ እየተናከሰ አለ።"

"ደግሞ የሴት ብልት ጠጉር ለበቅሎ መድኃኒት ይበጃል ብሎ 500 ጉንዲ ጠጉር በሚዛን አምጡ ብሎ በየወረዳው ጥሎ ደሃውን አስለቀሰው። በሚዛን ሳይመላለት ጊዜ የራሱን ጠጉር እየጨመረ ቢሰጥ እምቢ እያለ ወርቅ ተገላገለው። ያን ጊዜ የሴት ዘመድ የሌለው ተቸግሮ ነበረ" ሲሉ ጽፈዋል።

ለማጠቃለል ያህል የኢትዮጵያ ሕዝብ አማኝ በመሆኑ ከልቡ እግዚአብሔርን በጸሎት ጠይቋል። ክርስቲያኑ ሆነ እስላሙ አሪታዊው ሆነ በሕገ ልቦና አማኙ ሁሉም ሕዝቡና አገሩ በመበደሉ ምክንያት አልቅሶአል። ከ1761-1845 ዓም ለኢትዮጵያ አንድነት ብሎ የሚነሣ ሰው እንዲያመጣለት ሕዝቡ በየእምነቱ በጸሎት ጠይቋል።



አጤ ቴዎድሮስ ለአንድነት ሲነሡ ከክርስቲያን መምህር አካለ ወልድና ከእስላም ሸህ ሁሴን ጅብሪል "ይበርቱ"በማለት አብረው የቆሙ ናቸው። ለዚህም መሳፍንቱ አገርንና ሕዝብን መበደላቸውን እግዚአብሔር አይቶ የሚቀጣ ማለባቸው። የአጤ ቴዎድሮስ መምጣትና የመሳፍንት ኃይል መድከም ዋናው ምክንያት በሕዝብ ጸሎት ቴዎድሮስ ከመጡ በኋላ እስከ ዛሬም ድረስ ደም ከመፍሰስ ያቆመ ባይሆንም ዘመነ መሳፍንት ከነበረበት ዘመን ግን የተሻለ መሆኑ ጥርጥር የለውም።

<u>የቴዎድሮስ ታሪክ ደብተራ ዘነብ</u> እንደጻፈው ሊትማን ያሳተመው ገጽ 12 "ንጉሥ በጠፋ በ71 ዘመን እግዚአብሔር ንጉሥ ቴዎድሮስን አስነሣ" ሲሉ ጽፈዋል። ተክለ ጻድቅ መኩሪያ <u>አጤ ቴዎድሮስ እና የኢትዮጵያ አንድነት</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 165 "ያን ጊዜም የሸዋው ገዥ ኃይለ መለኮት ወርቂትንና ራስ ዐሊን ለመርዳት መጡ። ንጉሥ ቴዎድሮስ የኃይለ መለኮትን መምጣት በሰሙ ጊዜ አያታ ወጥተው አዋ ሜዳ ላይ ሠፈሩ። ራስ ዐሊም ከኃይለ መለኮት ጋር አንድነት ሆነው መከሩ። እንዲህ ብለው። እርስዎም ሸዋ ይመለሱ፤ ይህነን ሰው አንችለውም አሉ" ሲሉ ጽፈዋል። ከዚህ ቀጥሎ የአጤ ቴዎድሮስን አወላለድና አነሣሥ ከሞላ ጎደል ታሪካቸውን ዘርዝሬ አቅርቤአለሁ።

# ክፍል ሦስት

## ምዕራፍ 1

### የካሣ ኃይሉ ትውልድ!

<u>ለምጩን መጽሔት</u> መስከረም 1991 ዓም ገጽ 15
"የታጠቅ እናት ሆዷ መቻሉ
እሳት አርግዛ ዘጠኝ ወር ሙሉ"

ሲል መጽሔቱ ጽፏል። አጥንት የሚቆጥር ውሻ እንጂ ሰው አልነበረም። ደግሞም የኢትዮጵያ ታሪክ አንዱ ወዳንዱ የተደባለቀ የተዋሕደ ሕዝብ እንጂ ልዩነት ያለው ሕዝብ አይደለም። እንኳን እኛ ኢትዮጵያውያን ቀርተን ሌሎች የሰው ልጆች አፍንጫ ደፍጣጣውና ቆርጣጣው ነጩ ጥቁሩ ሁሉም የዓለም ሕዝብ ከኢትዮጵያ ወደ ሌላው ዓለም የተሰደደ መሆኑን የታሪክ ምርምሮች ያስረዳሉ። ታዲያ ምን ያደርጋል ደጎቹ አልቀው እኛ ተወልደን አንዱን ዘር ገኘ ሌላውን ዘር ተገኘ አድርገን መቁጠር በተጀመረበት ዘመን እኔም ደረስኩና ከመንታ መንገድ ላይ ቆምኩ። የቱን ልያዝ? ያነበብኩትን ወይስ የማየውን?

ሰው ተከፋፍሎ በሰፈር በጎሮ፤
እኔ አይገባኝም የሚባለው ሁሉ አምናና ዘንድሮ፤
በተለይ ምሁሩማ ሁንዋል ደንቆሮ፤
አያነጋግርም፤ ካልነገሩት ዘር ማንዘርን ቆጥሮ፤

አለቃ ኪዳነወልድ ክፍሌ <u>ሃይማኖተ አበው ቀደምት</u> ከተባለው ያልታተመ መጽሐፍ " የካሳ ኃይሉ አባት ትግሬ ነው። ስሙም ገብረ ኪዳን ነው"በማለት ጽፈዋል። የአጤ ቴዎድሮስን አባት ትግራይ ናቸው ብለው ከእውነት የራቀ መላ ምት ጽፈዋል። ይህን በሚመለከት ክፍል 12 ምዕራፍ 8 ስለተጻፈ ከቦታው ስትደርሱ ትመለከቱታላችሁ።



**Taddesse Tamrat <u>Kasa And Kasa</u> በተባለው መጽሐፍ page 117 Haylu and Attijggab decided to marry and lived near Gondar where Ksasa was born.Haylu apparently died quite early and the mother moved to Gondar "ሲሉ ጽፈዋል።**

ዶ/ር ላጽሶ ጌ ድሌቦ <u>የኢትዮጵያዊነት ታሪካዊ መሠረቶችና ማግሪያዎች</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 148 "በ1868 የዚህ ኩሩና ቆራጥ የሰሜን/ፈላሻ ወገን ተወላጅ የቋራው ካሣ ቴዎድሮስ በታላቁ የመቅደላ ጦር ሜዳ እንዳደረገው ጠላት እጅ ከመውደቅ ራሳቸውን በስለት ገደሉ" ሲሉ ጽፈዋል።

እኔም ዶ/ር ላጽሶን ስልክ ደውዬ አነጋግሬአቸው ነበር። የእኔ ጥያቄ "ዶ/ር አጤ ቴዎድሮስ የሰሜን ፈላሻ ወገን ተወላጅ የቋራው ካሣ ቴዎድሮስ" ብለው ከመጽሐፍዎ ላይ ጽፈዋል። ስለዚህ በየትኛው የዘር ሐረግ በኩል ነው ፈላሻ የሆኑት?"በማለት ጠይቄያቸው ነበር።

እርሳቸው ቀጭን በሆነው ድምጻቸው እንግሊዘኛ በሚበዛበት ቋንቋቸው ከዚህ የሚከተለውን መልሰውልኛል "ቅድሚያ እኛ ኢትዮጵያውያን የዓለም ሕዝቦች አባት ስንሆን የሰሜን ፈላሻ ማለት ለእኔ ክርስቲያኑ ሆነ እስላሙ አለዚያም ይሁዲው ሁሉም አንድ ነው። ይህ ከሆነ አጤ ቴዎድሮስ የፈላሻ ዘር ያላቸው ለአገር ግንባታ የተነሡ ጀግና የቋራ ተወላጅ ናቸው" ሲሉ መልሰውልኛል። እንደሚገባኝ የፈላሻ ትውልድ ሊኖራቸው ይችላል ከማለት በቀር የአባታቸውን ትውልድ አስመልክቶ ቋራ መሆናቸውን አሥምረውበታል። ከላይ ከተጠቀሰው ከአለቃ ኪዳነወልድ ክፍሌ ታሪክ ጋር ሊገናኝ አይችልም።

ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ <u>ታሪክ ዘዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 125 "ባጼ ቴዎድሮስ 15 ዓመት ባጼ ተክለ ጊዮርጊስ 3 ዓመት ባጼ ዮሐንስ 18 ዓመት የቆየችው መንግሥት ከዳዊት ከሰሎሞን ከምኒልክ ገባች" ሲሉ ጽፈዋል። የሚገርማችሁ ነገር ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ አጤ ቴዎድሮስን ሆኑ አጤ ተክለ ጊዮርጊስንና አጤ ዮሐንስን የዘር ግንድ ከሰሎሞን እንደማይወለዱ በማድረግ ጽፈዋል።

ታዲያ ዛሬ ሌሎችን ቡድኖች ዘረኞች ስንል ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴን ምን ልንላቸው ነው? የአጤ ምኒልክን የዘር ሐረግ በተመለከተ እርሳቸው ባይጽፉት አለቃ ለማ የተናገሩትን ልጃቸው አቶ መንግሥቱ ለማ ሲጽፉት፤የአጤ ምኒልክ እናት አባታቸው ጎንደር ደብረታቦር አውራጃ አሞራ ገደል ሲሆኑ አንዱ ጎናቸው ወሎ መሆናቸውን ጽፈዋል:: ወይዘሪት እጅጋየሁ አዲያሞ ጉራጌነትም አላቸው::

ጳውሎስ ኞኞ <u>አጤ ምኒልክ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 13 "ወይዘሮ እጅጋየሁ ውብና ከደሀ ቤተሰብ መወለዳቸውን ይገልጻሉ:: የአባታቸውን ስም ግን የሚገልጽ የለም:: ለማ አዲያሞ ይባላሉ:: ይህን ሲተነትኑም አንዳንዶቹ ከጉራጌ አገር የተማረኩ ባርያ ናቸው ይሏቸዋል:: ባርያ ማለት በገንዘብ የሚሸጥ ብቻ ሣይሆን በጦርነት የሚማረክ ሁሉ ባርያ ይባላል:: ይህ ሁሉ ይቅርና ዋናው ቁም ነገር ታሪክ መሥራት እንጂ ትውልድ አይደለም" ሲሉ ከጻፉ በኋላ የወይዘሮ እጅጋየሁ አያት ከጎንደርና ከወሎ የሄዱ መሆናቸውን ዘርዝረው ጽፈዋል::

ታዲያ ይህን ታሪክ ሳይጠቅሱ ሌሎችን አርክሰው የሚጽፉ ለምድን ነው? አጤ ቴዎድሮስ የሚኮሩት በትውልድ ዘራቸው ሳይሆን በእግዚአብሔር ኃይልና በኢትዮጵያዊ ወኔ ነበር:: ሆኖም ግን አጤ ቴዎድሮስ ከተለያዩ ጎሳዎች የተወለዱ የነገሥታት ዘር ያላቸው መሆናቸውን ከተለያዩ የታሪክ መጻሕፍት የለቀምኩትን ታሪክ ለቅምሻ ጀባ ልበል:: አጤ ቴዎድሮስ ጎንደሬ ብቻ ሳይሆኑ ከላይ ከአጤ ልብነ ድንግል ባለቤት ከእቴጌ ሰብለ ወንጌል የትግሬ ዘር ያላቸው ሲሆን ከወሎና ከሸዋ ከጎጃምና ከኦሮሞ፤ከአማራና ከቅማንት ከተለያዩ ጎሳ የተወለዱ ናቸው::

<u>ስማቸው ያልታወቀው የቴዎድሮስን ታሪክ የጻፉት ሊዊጅ ሁፌለአ</u> ካሳተሙት ገጽ 3 "አጤ ቴዎድሮስ ትውልዳቸው ያባታቸው አገር ቋራም ደምቢያም ነው:: ያባታቸው ስም ኃይሉ ወልደ ጊዮርጊስ ይባላሉ" ይሉና "የእናታቸው ስምም ወይዘሮ አትጠገብ ይባላሉ:: ከጎንደርም ከእንፍራዝም ከቤጌምድርም ይወለዳሉ:: ከነገሥታት ወገንም ትውልድ አላቸው" ሲሉ ጽፈዋል::



ይህን መጣጥፍ የጻፉት የትግራይ ተወላጅ አባ ወልዴ ይባላሉ የሚሉ ሲኖሩ ጥቅስ ሲጠቀስ ስማቸው ያልታወቀው ደራሲ ይባላሉ:: ምናልባት የትግራይ ተወላጅ ናቸው ሊባል የቻለው በገጽ 10 ላይ በትግርኛ ግጥም ጽፈዋል:: ለዚህም ይሆናል የትግራይ ልጅ ናቸው የሚባሉት እኔም ብሆን አባ ወልዴ የትግራይ ተወላጅ ለመሆናቸው አልጠራጠርም::

ምክንያቱም ሌሎች ደራስያን በአማርኛ አልያም በግእዝ የተገጠመን ግጥም አብራርተው ይጽፋሉ እንጂ በትግርኛ የተገጠመን ግጥም ጽፈውት አላነበብኩምና:: ስማቸውን ያልጠቀሱበት ምክንያት በትሕትና ነው ልል አልችልም:: አንዳንዴ ጠንከር ያለ ከደብተራ ዘነብ የተለየ ትችት የጻፉ በመሆናቸው ሊሆን ይችላል::

መሪ ራስ ኤ.ኤም አማን በላይ <u>የትናንትናዋ ኢትዮጵያ ነገሥታት ታሪክ</u> በተባለ መጽሐፉ ገጽ "225 አጤ ቴዎድሮስ ከአጤ ልብነ ድንግል ዘር ያላቸው ናቸው" ሲሉ ጽፈዋል፤ በቅርቡ ዘመን የተነሡት ደራስያን የአጤ ቴዎድሮስን የዘር ሐረግ ፈጽሞ ሊጠቅሱ አይፈልጉም:: በነገራችን ላይ አጤ ቴዎድሮስ በሕይወት በነበሩበት ወቅት ዘራቸው ተቆጥሮ የተነበበ መሆኑን ሊቅ ዶ/ር ሔንሪ ብላንክ በጆሮዋቸው የሰሙትን ጽፈዋል:: ለምሳሌ ይህን የሔንሪ ብላንክን መጽሐፍ የጎንደር ክፍለ ሀገር አስተዳዳሪ የነበሩት አቶ ዳኛው ወልደ ሥላሴ ወደ አማርኛ ተርጉመውታል::

ዶ/ር ሔንሪ ብላንክ እንደጻፈው ትርጉም ዳኛው ወልደ ሥላሴ <u>የእሥራት ዘመን በአበሻ አገር</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 113" የአጤ ቴዎድሮስ የትውልድ ሐረግ ታሪክ መነበብ ጀምሮ ከአዳም እስከ ዳዊት ከዚያም ከሰሎሞን እስከ ሱስንዮስ ያለው ዝርዝር ከተነበበ በኋላ የጥቂት ጳጳሳትም ስም ተጠቅሶ ወደ አጤ ቴዎድሮስ አባትና እናት ሲደርሱ ሁኔታው ጠንካራ ሆነ:: አያሌ ዘር ቆጣሪዎች ቀርበው አጤ ቴዎድሮስ ከነገሥታቱ የሚወለዱ መሆናቸውን ከማረጋገጣቸው ሌላ ስለ አጤ ቴዎድሮስ ትውልድ አጤ ዮሐንስ ያረጋገጡበትም መዝገብ ቀረበ" ሲሉ የተመለከቱትን ጽፈዋል::

<u>አባ ታጠቅ ካሳ የቋራው አንበሳ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 21-29 "ቋራ ጌታ ንፋውዝ ያጤ ሰይፈ አርዕድ ልጅ መሃይሞቴን አግብተው ዓመተ መድኅንን ይወልዳሉ:: ወይዘሮ ዓመተ መድኅን አዛዥ

አስፈሬን አግብተው እሜቴ አድራግን ይወልዳሉ እሜቴ አድራግ ፊታውራሪ ክንፌ ሩፋኤልን ፊታውራሪ ክንፌ ሩፋኤል አዛዥ አካሌን ልጅ ሴዴቅያስንም ይወልዳሉ። እሜቴ እዳይት ክንፌ ሩፋኤልን አግብተው ወይዘሮ ወለተ ገብርኤልን ይወልዳሉ።"

"ወይዘሮ ወለተ ገብርኤል ቋራ ደጃዝማች ሕላዌን አግብተው ደጃዝማች እልፍዮስን ይወልዳሉ። ደጃዝማች እልፍዮስ ደጃዝማች ወልደ ጊዮርጊስን፣ደጃዝማች ወልደ ጊዮርጊስ አቶ ኃይሉን፣አቶ ኃይሉ ከእንፍራዝ ተወላጅ ከወይዘሮ አትጠገብ አጤ ቴዎድሮስን ይወልዳሉ። አምባ ጫራ ተክለ ወልድ እበያን አግብቶ ወልደ መጋቢን ይወልዳል። ወልደ መጋቢ መጋቢ አንስጤን፣ መጋቢ አንጤን ሳሙኤልን፣ሳሙኤል ትሻልን ትሻል ወንድ በወሰንን አግብታ ወይዘሮ አትጠገብን ትወልዳለች። ወይዘሮ አትጠገብ ቋራ ከጌታው አቶ ኃይሉ አጤ ቴዎድሮስን ትወልዳለች"።

"ከምከም አገለሃና ወምቦርጌ ሚካኤል አባርዋ ጎጥ ዓመተ ጽዮን ሰበን ከደጃዝማች እልፍዮስ ደጃዝማች ወልደ ጊዮርጊስን ደጃዝማች ወልደ ጊዮርጊስ ነጭትን ነጭት ኃይሉን፣ኃይሉ አጤ ቴዎድሮስን ይወልዳሉ። ሰበን ሥርጉት፣ጎንደሪት ነጮን፣ነጮ ላእኩንና እንዝርትን ይወልዳሉ። ላእኩ ጎሹን፣ጎሹ ብሪቱን፣ብሪቱ ዳግመኛ ሥርጉትን፣ ሥርጉት ሌንጮን፣ሌንጮ አልጣሽን ይወልዳሉ። አልጣሽ አትጠገብን ትወልዳለች። አትጠገብ አጤ ቴዎድሮስን ይወልዳሉ።"

"መቄት ሊቄ ይምራ እሜቴ አባለ ድንግልን፣እሜቴ አባለ ድንግል መቀረት ከተባለው ቦታ አዝማች ዮሐንስን አግብተው ወልደ ሃይማኖትንዓምደ ሃይማኖትን ማሞን፣አውዶክስዮስን ሃይማኖታዊትን እንተ ጊዮርጊስን ወለቴን እሜቴ ዮዲትን ይወልዳሉ እሜቴ ዮዲት ደጃዝማች እልፍዮስን አግብተው ደጃዝማች ወልደ ጊዮርጊስን ይወልዳሉ።"

"ደጃዝማች ወልደ ጊዮርጊስ ነጭትን አግብተው ኃይሉን ይወልዳሉ። ኃይሉ ወይዘሮ አትጠገብን አግብተው አጤ ቴዎድሮስን ይወልዳሉ። አማራ ሳይንት ራስ ጎሹ እሜቴ አስቴርን አግብተው ለባሴ መስቀልን ለባሴ መስቀል ራስ ወዳጆን ራስ ወዳጆ ሌንጮን ሌንጮ ወንድ ወሰንን ወንድ በወሰን ከደብረሰን ትሻልን አግብተው ወይዘሮ



አትጠገብን ይወልዳሉ። ወይዘሮ አትጠገብ ኃይሉን አግብተው አጤ ቴዎድሮስን ይወልዳሉ"።

"ጭልጋ አፅመ ርስት ተጠምቀ መድኅንን ተክለ ጊዮርጊስን ተክለ ጊዮርጊስ ገጻይንና ጸጋ ሥላሴን ይወልዳሉ። ጸጋ ሥላሴ ለባሲትንና እስክንድራዊትን ይወልዳሉ። እስክንድራዊት ባንት ይሁንን ባንት ይሁን ወለተ ሥላሴን ወለተ ሥላሴ ነጭትን ነጭት ደጃዝማች ወልደ ጊዮርጊስን አግብታ አቶ ኃይሉን ትወልዳለች። አቶ ኃይሉ ከእንፍራዝ ባላባት ከወይዘሮ አትጠገብ ወንድበወሰን አጤ ቴዎድሮስን ይወልዳሉ።"

"እንፍራዝ ክንቲባ ገብሩ ከወይዘሮ ወለተ ውዱሳን ቴዎድሮስን ይወልዳሉ። ክንቲባ ቴዎድሮስ ክንቲባ ጊዮርጊስን ክንቲባ ጊዮርጊስ አጋሮን አጋሮ ፊቅጦርን ወለተ እሥራኤልን ይወልዳሉ። ክንቲባ ጊዮርጊስ አቃርዮስን ይወልዳል አቃርዮስ ተክለ ዮሐንስን ተክለ ዮሐንስ ዓመተ ዮሐንስን ዓመተ ዮሐንስ ደብረሳን ኪዳነ ምሕረት ንቡረ ዕድ አፈ ክርስቶስን አግብታ ወለተ ድንግልን ትወልዳለች።"

"ወለተ ድንግል መጋቢ አንስጤን አግብታ ሳሙኤልን ትወልዳለች፣ ሳሙኤል ትሻልን ትሻል ወንድ በወሰንን አግብታ ወይዘሮ አትጠገብን ወይዘሮ አትጠገብ ጌታው አቶ ኃይሉን አግብታ አጤ ቴዎድሮስን ትወልዳለች። አጤ ሰይፈ አርዕድ፣ ገብረ ማርያምን ይንጋን፣ተክለ ሃይማኖትን ገብረ ማርያምን፣ኤላውትሮስ ኤላውትሮስ፣መክፈልቶ አዛዥ ሜላን አዛዥ ሜላ አዛዥ ሳሙኤልን፣አዛዥ ሳሙኤል ሣቁኤልን፣ሳቁኤል፣ አብልሆን አብልሆ አዝማች ስብንቴን አዝማች ስብንቴ፣ ከወይዘሮ ባዝግና ወርቅ ደጃዝማች ህላዌን ይወልዳሉ። ደጃዝማች ህላዌ እልፍዮስን፣እልፍዮስ ወልደ ጊዮርጊስን፣ወልደ ጊዮርጊስ ጌታው አቶ ኃይሉን ጌታው አቶ ኃይሉ አጤ ቴዎድሮስን ይወልዳሉ"።

"አጤ ዓምደ ጽዮን አጤ ሰይፈ አርድን አጤ ሰይፈ አርእድ ደጃዝማች ገብረ ማርያምን ደጃዝማች ገብረ ማርያም ደጃዝማች ኤላውትሮስን ደጃዝማች ኤላውትሮስ መክፈልቶን መክፈልቶ ሳሙኤልን ሳሙኤል ሳቁኤልን ሳቁኤል አብላሆን አብላሆ አዝማች ህላዌ ስብስቱን አዝማች ስብስቱ ባዝግና ወርቅን አግብተው ደጃዝማች ህላዌን ደጃዝማች ሕላዌ ደጃዝማች እልፍዮስን ደጃዝማች

እልፍዮስ ደጃዝማች ወልደ ጊዮርጊስን ደጃዝማች ወልደ ጊዮርጊስ ከወይዘሮ ነጭት ጌታው አቶ ኃይሉን ጌታው ኃይሉ ከእንፍራዝ ባላባት ከወይዘሮ አትጠገብ አጤ ቴዎድሮስን ይወልዳሉ:: አጤ ልብነ ድንግል ወይዘሮ ተወዳድያንን ወይዘሮ ተወዳድያን አዛዥ ኩሉን አግብተው ወይዘሮ ሐመልማለ ወርቅን ወይዘሮ ሐመልማለ ወርቅ ራስ የማነ ክርስቶስን ራስ የማነ ክርስቶስ ራስ ጎሹን ራስ ጎሹ ወይዘሮ አስቴርን አግብተው ለባሴ መስቀልን ለባሴ መስቀል ራስ ወዳጆን ይወልዳሉ::"

"ራስ ወዳጆ ሌንጮን ሌንጮ ወንድ በወሰንን ወንድበወሰን ትሻልን አግብተው ወይዘሮ አትጠገብን ይወልዳሉ:: ወይዘሮ አትጠገብ ቋራ ጌታው አቶ ኃይሉን አግብተው አጤ ቴዎድሮስን ይወልዳሉ:: አጤ ልብነ ድንግል አቤቶ ያዕቆብን ይወልዳሉ:: አቤቶ ያዕቆብ ገራም ፋሲልን፤ገራም ፋሲል አጤ ሱስንዮስን አጤ ሱስንዮስ አጤ ፋሲልን፤ አጤ ፋሲል ከወይዘሮ ዘሊሃ ወይዘሮ ሰብለ ወንጌልን ይወልዳሉ:: ሰብለ ወንጌል ጎጃም ቆለላ ኪዳነ ምሕረት ደጃዝማች ድሜጥሮስን አግብተው አንስጤን ይወልዳሉ::"

"አንስጤ ዕንቁላልን፤ እንቁላል፤ ክንፈ ሩፋኤልን፤ ክንፈ ሩፋኤል፤ ወለተ ገብርኤልን፤ወለተ ገብርኤል ቋራ ደጃዝማች ሀላዊን አግብታ ደጃዝማች እልፍዮስን፤ደጃዝማች እልፍዮስ ደጃዝማች ወልደ ጊዮርጊስን፤ደጃዝማች ወልደ ጊዮርጊስ አቶ ኃይሉን አቶ ኃይሉ አጤ ቴዎድሮስን ይወልዳሉ" ሲሉ ጽፈዋል:: ከዚህ በላይ በመጠኑ የጠቀስኩት አለፍ አለፍ እያልኩ ነው::

ተክለ ጻዲቅ መኩሪያ <u>አጤ ቴዎድሮስ እና የኢትዮጵያ አንድነት</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 51 "የካሣ የአባታቸው አገር ቋራ ነው:: እናታቸው የጎንደር ተወላጅ ናቸው" ይሉና ገጽ 52 "ቋራን በባላባትነት የሚገዙት ደግሞ የካሣ አባት ኃይሉ ወልደ ጊዮርጊስ ናቸው" በማለት ያልፉታል:: ክቡር አቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ከዘር ቆጠራ ላይ አደባብሰው አለፉ:: የሠነድ እጥረት ኑሮባቸው እንዳይባል ሠነዶችን የተጠቀሙባቸው መሆናቸውን ተዘርዝረው ይገኛሉ:: አቶ ነጋ ጌጡ ደግሞ አጤ ቴዎድሮስ ቅማንት ናቸው ብለዋል:: ለዚህ መረጃ አድርገው ያቀረቡት የአጤ ቴዎድሮስ አያት የሞቱትና የተቀበሩት በቅማንት አገር ውስጥ መሆኑን በመጥቀስ እንዲህ ይላሉ::



ነጋ ጌጡ <u>የቅማንት ሕዝብ ታሪክ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ውስጥ ገጽ 58 "አጤ ቴዎድሮስ በትውልዳቸው ቅማንት ናቸው የሚለውን አሉታ አጣርቶ ሃቁን ማውጣት፤በቅማንት ሕዝብ መካከል የቴዎድሮስ ወላጆችም ሆነ የራሳቸው ስም ማን ይባል እንደነበር መርምሮ ሐቁን ማግኘት፤የካሣ የአባቱ አባት ነበሩ የተባሉት የደጃዝማች ጊዮርጊስ ሥርዓተ ቀብር ተፈጸመ የተባለው በቅማንት አገር ውስጥ የሆነበትን ምሥጢር መርምሮ ይፋ ማውጣት፤ የቴዎድሮስን ባለቤት ወ/ሮ ተዋበችን ደብቆ ለማቆየት የቅማንት አገርና አይከል ኮልቦ የተባሉ ቅማንት ሰው የተመረጡበትን ምሥጢር መርምሮ ይፋ ማውጣት::"

"ቴዎድሮስ በሥልጣን ዘመናቸው ሳሉ በዙሪያቸው በጦር አዛዥነትና በሚንስትርነት ተሹመው ያገለግሏቸው የነበሩት በሙሉ ቅማንቶች ነበሩ:: እንዲያውም አጤ ቴዎድሮስ እራሳቸውን ለትግል የአደራጁበት ሥፍራ ከቅማንት ሕዝብ መሀል ጭልጋ ውስጥ የሆነበትን ምሥጢር መርምሮ እንዲሁ ይፋ በማውጣት አጤ ቴዎድሮስ እውነት የእንፍራዝ የደንቢያ የአለፋ ጣቁሳና የቋራ ፊውዳል ራስ ደጃዝማች ልጅ ናቸው? ወይስ የቅማንት ልጅ ናቸው? ለሚለው ጥያቄ መልስ ለማግኘት ይቻላል" ሲሉ ጽፈዋል::

አቶ ነጋ ጌጡ ሁሉንም በጥያቄ መልክ አቀረቡት እንጂ ለአንዱም እንኳን አወንታ መልስ ሳይሰጡ አንጠልጥለው ትተውታል:: በነገራችን ላይ አጤ ቴዎድሮስ ምኒስተሮች አልነበሩአቸውም:: የጦር አበጋዛቸው ፊታውራሪ ገብረዬ፤የጋይንትና የአገው ምድር ተወላጅ ናቸው:: አንድ አዛውንት "ፊታውራሪ ገብርዬ የተዋናይ ታማኝ በየነ በጣም ቅርብ ዘመዱ ናቸው:: ለዚህም ነው ይህ ልጅ በጥቅም እምነቱን የማይሸጥ" በማለት አጫውቱኝ::

ወደነበርኩበት ልመለስና ደጃዝማች ገልሞ ቅማንት ናቸው:: ሌላው ደጃዝማች አለሜ አጤ ቴዎድሮስ ገና ትግል ሲጀምሩ ፊታውራሪ ገብርዬ ከጋይንት፤ራስ እንግዳ ከጎጃም አገው ምድር አውራጃ፤ ደጃዝማች ገልሞ ጭልጋ ቅማንት መግባታቸው የታወቀ ሲሆን በዚህ ምክንያት አጤ ቴዎድሮስ ሙሉ በሙሉ ቅማንት ደጃዝማች ዓለሜ ቋራ፤ ናቸው ብሎ አፍን ሞልቶ መናገር አይቻልም:: ቋራ በጭልጋ አውራጃ ውስጥ በመሆኑ አጤ ቴዎድሮስ ቅማንት ናቸው ማለት

አያስደፍርም:: የአጤ ቴዎድሮስ አያት ቅማንት አገር በመቀበራቸው አጤ ቴዎድሮስ ቅማንት ናቸው ማለት አይደለም::

ነገር ግን የአጤ ቴዎድሮስ ቤተሰቦች ጭልጋ፣ለቋራ ቅርብ ስለሆነ ምናልባት ረጅም ዘመን በፊት የሚመጣ የዘር ግንድ ሊኖር ይችላል:: ከላይ እንደተጠቀሰው በቦታ ስም ጭልጋ የሚለው ስለተጠቀሰ ዘር ሊኖር ይችላል እንጂ አቶ ነጋ ጌጡ እንዳሉት ድፍን አድርጎ ያለ ማብራሪያ ጨርሶ ቅማንት ናቸው ለማለት ለእኔ ያስቸግረኛል:: አጤ ቴዎድሮስ የቅማንት ደም እንደሚኖርባቸው ብገምትም ከላይ በተጠቀሰው ዝርዝር ግን የቅርብ ዘር ሊሆን እንደማይችል አምናለሁ:: ለወደፊቱ ጥሪት ያለ ታሪክ ሊያቀርቡ ካልቻሉ በቀር ይህ ጥናት በቂ አይመስለኝም:: ምናልባት ኢሕአዴግን ለማስደሰት ያደረጉት ለመሆኑ በሌሎች ገጾችና ምክንያቶች መረዳት ይቻላል::

ዓለማየሁ ነሪ ውርጋሶ የባለታሪኮች ዳግም ልደት ኸሰት 2ኛ መጽሐፍ በተባለው ገጽ በኢትዮጵያችን ታሪክ በምሳሌነት ከሚጠቀሱት ከ18ኛው እስከ 20ኛው መቶ ክፍላተ ዘመናት ለረዥም ዓመታት በንጉሠ ነገሥትነት የመሯት ቅማንቱ መይሳው ካሣ አጤ ቴዎድሮስ ን የቋራው" ሲሉ ጽፈዋል:: ይህም ትክክል አይደለም:: አቶ ዓለማየሁ ነሪ ውርጋሶ ምናልባት የአቶ ነጋ ጌጡን መጽሐፍ አንብበው ከሆነ ተሳስተዋል:: ለወዲፊቱ ያስተካክሉ:: የአጤ ቴዎድሮስን የዘር ሐረግ አስመልክቶ ሌሎች ይህን ብቻ ሳይሆን የሚቆጥሩት ቋራ ከቀደም ጀምሮ የኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ መርዌ ያለበት በመሆኑ ከንግሥተ ሣባ ተመዞ የሚወርድ ዘር አላቸው የሚሉም አሉ::

ቤተ መንግሥቱ ከመርዌ ወደ አክሱም ከተዛወረ ከ982 ዓመተ ዓለም ወዲህ ትግራይ ሲቆይ ንግሥት ዮዲት በ842 ዓም ሸዋ ያስገቡት ዘር ሙሉ አድሮ ከዛጉዌ መንግሥቱን በተንኮል ያመጡት ተማሪ ተስፋ ልደት የኋላው አጤ ይኩኖ አምላክ መሆናቸው አይዘነጋም:: ከአጤ ይኩኖ አምላክ ዘር የሚመጡት አጤ ሰይፈ አርዕድ የሚቆጥረው ኋላም አጤ ልብነ ድንግል ዘር ተመዞ ይወርዳል:: አጤ ቴዎድሮስ ከነገሥታቱ ዘር የሚወለዱ መሆናቸውን ራሳቸው ለእንግሊዝ ንግሥት ደብዳቤ ሲጽፉ" አባቶቼ እግዚአብሔርን ቢበድሉ አገራቸውን "ለኦሮሞና) ለእስላም ሰጠባቸው እኔን ከትቢያ አሥነስቶ ዛሬ ለዚህ አድርሶኛል" እያሉ የሚጽፉት ያለ ታሪክ አይደለም::



አጤ ቴዎድሮስ ከነገሥታቱ ዘር ታሪክ ያላቸው ቢሆንም ቅሉ እርሳቸው በነገሥታቱ ግንቦች ማደርና መዋል አይፈልጉም ነበር:: ምክንያቱም በእርሳቸው ግምት ነገሥታቱ ሕንጻ ከመሥራት የጦር መሣሪያ ማምረት ነበረባቸው ብለው ይነቅፏቸዋል::

በእርግጥ የአጤ ቴዎድሮስ አባባል ትክክል መሆኑን የምንረዳው በሰላም ወቅት ሳይሆን አገር ስትወረር መሣሪያ ፍለጋ አንዴ ከአንዱ አገር ሌላ ጊዜ ከሌላው አገር ለግዥና ለልመና የሚኳትኑት ገዥዎቻችን በአገራቸው የጦር መሣሪያ ማምረት የማይችሉ በመሆናቸው ነው:: ታዲያ ከ1860 ዓም ወዲህ እስከ 2003 ዓም ድረስ ኢትዮጵያ ለምን መሣሪያ ማምረት አልቻለችም? በእርግጥ በርእሰ ብሔር ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ዘመን ተጀምሮ ነበር::

ካሳ ኃይሉ ከአባታቸው ከአቶ ኃይሉ ወልደ ጊዮርጊስ ከእናታቸው ከወይዘሮ አትጠገብ ወንድ ወሰን በጎንደር ክፍለ ሀገር በጭልጋ አውራጃ ዳዋ ከምትባል መንደር ጥር 6 ቀን 1811 ዓም ተወለዱ:: የካቲት 16 ቀን 1811 ዓም ክርስትና ተነሡ::

የክርስትና ስማቸው ገብረ ኪዳን ሲሆን አባ ታጠቅ ካሣ የቋራው አምበሳ በተባለው መጽሐፉ ገጽ 19 ጳውሎስ ኞኞ አጤ ቴዎድሮስ በተባለው መጽሐፉ ገጽ 7 ተክለ ጻዲቅ መኩሪያ አጤ ቴዎድሮስ እና የኢትዮጵያ አንድነት በተባለው መጽሐፉ ገጽ 51 "ጥር 6 ቀን 1811 ዓም ተወለዱ በማለት ጽፈዋል::

ከነዚህ መጻሕፍት ላይ ያልጠቀስኳቸው ሌሎችም የተለያዩ መጻሕፍትና መጣጥፎች የተወለዱበት ጥር 6 ቀን 1811 ዓም አድርገው ሲጽፉ ቁጥራቸው አናሳ የሆኑ ደራስያን ደግሞ "መስከረም 10 ቀን 1810 ዓም ተወለዱ" በማለት ጽፈዋል:: መስከረም 10 ቀን 1810 ዓም ተወለዱ በማለት የጻፉት ደራስያን አናሳ ናቸው:: ስለዚህ እኔ በብዙኃኑ የተደገፈውን አጤ ቴዎድሮስ ጥር 6 ቀን 1811 ዓም ተወልደዋል የሚለውን ሙሉ በሙሉ ደግፌአለሁ::